# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲና ስትራተጅ

አሳታሚ
በማስታወቂያ ሚኒስቴር
ፕሬስና ኦዲዮቪዥዋል መምሪያ
ሁለተኛ እትም

ኅዳር 1995 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# ማ ው ጫ

## የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት
## ፖሊሲና ስትራተጅ

ገፅ

IV

መ ግ ቢ ያ ............................................................................ 1

1. የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲያችን መነሻዎች .............

1.1. ልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ እንደፖሊሲ 1

መነሻ ............................................................. 5

1.2. አገራዊ ክብር እንደፖሊሲ መነሻ ................................. 16

1.3. ግሎባላይዜሽን እንደፖሊሲ መነሻ ................................ 21

2. የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲ ግቦች................... 23

3. የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ስትራተጅዎች..................

3.1. ዋናው ትኩረታችን በአገር ውስጥ የሚሰራው 23

እንዲሆን ማድረግ..................................................... 27

3.2. ኢኮኖሚን ማዕከል ያደረገ ስትራተጅ.......................... 29

3.3. በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ ጥቅሞችን አሟጦ መጠቀም. 32

3.4. በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ አደጋዎችን መቀነስ........... 35

3.5. ለአደጋ ተጋላጭነትን መቀነስ...................................... 41

3.6. ብቃት ያለው የመከላከል አቅም መገንባት.................... 43

ሀ. በበቂ የስጋት ትንተና ላይ የተመሰረተ ግንባታ ማካሄድ 45

ለ. በሰው ሃይል ብቃት ላይ ያተኮረ የግንባታ ስራ መስራት 47



ገፅ

ሐ. እያንዳንዷን ብር በቁጠባ የመጠቀም አሰራር............... 49

መ. የመከላከያ ወጭ ከኢኮኖሚ ጋር እንደሚመጋገብ ማድረግ

ሠ. ከልማት እንቅስቃሴያችንና ከወቅታዊ አደጋዎች 50

ጋር ማጣጣም......................................................................... 52

3.7. ጠንካራ የማስፈፀም አቅምን መገንባት............................... 52

ሀ. አንድ የጋራ አገራዊ አመለካከትና እምነት መፍጠር ....... 54

ለ. የዲፕሎማሲ ሙያተኛ አቅም መፍጠር .......................... 56

ሐ.በአፈፃፀሙ ላይ አስተዋፅኦ ያላቸውን ማሳተፍ፣ ማስተባበር

## ክፍል ሁለት
## ከአገሮች ጋር የሚኖረን የግንኙነት ፖሊሲ

61

1. የአፍሪካ ቀንድ አገሮች........................................................ 61

1.1. አጠቃላይ ፖሊሲ........................................................ 62

ሀ. ጎረቤት አገሮች ከልማታችን አኳያ ያላቸው ፋይዳ......

ለ. ጎረቤት አገሮች ከዴሞክራሲያችን ማበብ አኳያ 64

ያላቸው ፋይዳ.........................................................

ሐ. የልማትና የዴሞክራሲ አጀንዳችን በአገሮቹ ላይ 66

ያለው ተፅእኖ......................................................... 69

1.2. ኤርትራን በሚመለከት ልንከተለው የሚገባን ፖሊሲ...... 69

ሀ. የትስስሩ ፋይዳ........................................................ 71

ለ. ለመልካም ወዳጅነት እንቅፋት የሆነው ገዥ ቡድን...... 74

ሐ. በኤርትራ ላይ ሊኖረን የሚገባ ፖሊሲ...................... 79

1.3. በሶማሊያ ላይ የሚኖረን ፖሊሲ................................. 79

ሀ. የግንኙነቱ ታሪካዊ አመጣጥ.................................. 81

ገፅ


ለ. የግንኙነቱ ፋይዳ...................................................... 83

ሐ. ሶማሊያን በሚመለከት ልንከተለው የሚገባን ፖሊሲ... 88

1.4. ሱዳንን በሚመለከት ልንከተለው የሚገባን ፖሊሲ......... 88

ሀ. የግንኙነቱ ታሪካዊ አመጣጥ..................................... 91

ለ. የግንኙነቱ ፋይዳ...................................................... 93

ሐ. ሱዳንን በሚመለከት ልንከተለው የሚገባ ፖሊሲ....... 96

1.5. በጅቡቲ ላይ የሚኖረን ፖሊሲ....................................... 96

ሀ. የግንኙነቱ ታሪካዊ አመጣጥ..................................... 97

ለ. የግንኙነቱ ፋይዳ...................................................... 98

ሐ. የግንኙነት ችግሮች................................................... 100

መ. በጅቡቲ ላይ ልንከተለው የሚገባ ፖሊሲ.................. 104

1.6. በኬንያ ላይ የሚኖረን ፖሊሲ...................................... 104

ሀ. የግንኙነቱ ታሪካዊ አመጣጥ..................................... 105

ለ. የግንኙነቱ ፋይዳ...................................................... 106

ሐ. በግንኙነቱ ላይ የታዩ ችግሮች.................................. 107

መ. ኬንያን በሚመለከት ልንከተለው የሚገባ ፖሊሲ...... 109

1.7. ኢጋድን ማጠናከር ...................................................... 110

2. ሌሎች የአፍሪካ አገሮች................................................ 110

2.1. የግንኙነቱ ታሪካዊ አመጣጥ....................................... 111

2.2. የግንኙነቱ ፋይዳ........................................................ 113

2.3. ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች ጋር ሊኖረን የሚገባ ግንኙነት 115

3. ከመካከለኛው ምስራቅ ጋር የሚኖረን ግንኙነት..................... 115

3.1. አጠቃላይ.................................................................. 120

3.2. ከግብፅ አኳያ የምንከተለው ፖሊሲ.............................. 120




ገፅ


ሀ. የግንኙነቱ ታሪካዊ አመጣጥና ችግሮች....................... 126

ለ. የግንኙነቱ ፋይዳ...................................................... 128

ሐ. ግብፅን በተመለከተ የምንከተለው ፖሊሲ...................... 131

3.3. ከአረብ ባህረ-ሰላጤ አገሮች ጋር የሚኖረን ግንኙነት........ 131

ሀ. የግንኙነቱ ታሪካዊ አመጣጥና ችግሮች....................... 132

ለ. የግንኙነቱ ፋይዳ ...................................................... 133

ሐ. በአረብ ባህረ-ሰላጤ አገሮች ላይ የምንከተለው ፖሊሲ .. 135

3.4. ከሰሜን አፍሪካ አገሮች ጋር የሚኖረን ግንኙነት............ 136

3.5. ከእስራኤል ጋር የሚኖረን ግንኙነት.............................. 139

3.6. ከቱርክና ከኢራን ጋር የሚኖረን ግንኙነት .................. 141

4. አውሮ-......................................................................... 141

4.1. የአውሮ- ህብረት ....................................................... 146

4.2. የሩሲያ ፌዴሬሽን....................................................... 147

5. ከአሜሪካ ጋር የሚኖረን ግንኙነት ................................ 151

6. ኤስያ........................................................................... 151

6.1. አጠቃላይ.................................................................. 153

6.2. ጃ-ን.......................................................................... 154

6.3. ቻይና ....................................................................... 155

6.4. ህንድ ....................................................................... 157

7. አለም አቀፍ ድርጅቶችና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች...... 157

7.1. አለም አቀፍ ድርጅቶች.............................................. 158

7.2. አለም አቀፍ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች................

# መ ግ ቢ ያ

ፈጣን የኢኮኖሚ ልማትን፣ የዴሞክራሲ ግንባታንና ሰላምን ማረጋገጥ በከፍተኛ የኋላቀርነትና የድህነት አዘቅት ውስጥ ለምትገኘው አገራችን የህልውና ጉዳይ መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም፡፡ በመሆኑም መንግሥት ለህልውናችን ቁልፍ ለሆኑት ጉዳዮች ከምንም በላይ ቅድሚያ ይሰጣል፡፡ መንግሥት የሚከተለው አጠቃላይ አገራዊ የፖሊሲ አቅጣጫም ይህንኑ መሠረታዊ እውነታ በሚገባ ያገናዘበ ካልሆነ በስተቀር አገራዊ ህልውናችንና ደህንነታችን ከፍተኛ አደጋ ላይ መውደቁ የማይቀር ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህነነት ፖሊሲና ስትራጅ ለአገራዊ ህልውናችን ፋይዳ  የሚኖረው ድህነትን አስወግዶ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ልማትን፣ ብልፅግናን፣ ዴሞክራሲንና ሰላምን የሚያረጋግጥ ከሆነ ብቻ ነው፡፡ ይህ ካልሆነ ግን አገራችን ለከፍተኛ አለመረጋጋትና መበታተን ተዳርጋ ህልውናችንና ደህንነታችን አስጊ ሁኔታ ላይ መውደቁ የማይቀር ነው፡፡

ያለፉት መንግሥታት ይከተሏቸው የነበሩት የውጭ ግንኙነትና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲዎች ለአገራዊ ህልውናችን ወሳኝ የሆኑትን ውስጣዊ ችግሮቻችንን ወደ ጎን በመተው በውጭ ላይ ትኩረት ያደረጉና ከውጭ ወደ ውስጥ የመመልከት ሁኔታ ጎልቶ የሚታይባቸው ስለነበር አገራዊ ጥቅማችንንና ህልውናችንን በተገቢው ደረጃ ሊያረጋግጡ የቻሉ አልነበሩም፡፡ በመሠረቱ የልማትና የዴሞክራሲ ራዕያችንን እውን ለማድረግ የሚያስችል ርብርብ በአገር ውስጥ ሳናደርግ የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲ የትኩረት አቅጣጫ በውጭ በሚካሄድ



እንቅስቃሴ ላይ ከሆነ ትርጉም ያለው ፋይዳ አይኖረውም፡፡

ከዚህ ጋር ሊጠቀስ የሚገባው ሌላው ጉዳይ ያለፉት መንግሥታት የውጭ ፖሊሲዎች አንዱ መነሻ በውጭ ጠላቶች የመከበብ ስሜት ጎልቶ ይታይበት የነበረና ይህም በሕዝባችን ሥነ-ልቦናና ከውጭው ዓለም ጋር በነበረን ግንኙነት ላይ ያሳደረው አሉታዊ ተፅዕኖ በቀላሉ የሚታይ ያለመሆኑ ነው፡፡ በእርግጥ ይህ ሲባል አገራችን የውጭ ጠላት የላትም ወይም በጠላትነት ጎራ በተሰለፉ ኃይሎች ላይ ተከትለናቸው የነበሩት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ሙሉ ለሙሉ ትክክል አይደሉም ለማለት አይደለም፡፡ ይህን የመሰለው ሁኔታ ቢኖርም የአገራችን የልማትና የዴሞክራሲ ግንባታ ሥራ መሳካት ጥቅማቸውን ሊነካባቸው የሚችሉ ወገኖችን እንዲሁም ጥቅማቸው የማይነካ ሆኖ ሳለ ጥቅማቸው የሚነካ የሚመስላቸውን ወገኖች በበቂ ጥናት ላይ ተመርኩዞ በመለየት አደጋዎችንና ሥጋቶችን ለመቀነስና ፈጣን የኢኮኖሚ ልማትና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ለማረጋገጥ የሚያስችል ፖሊሲና ስትራተጅ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ ያለፉት መንግሥታት ያራምዱት በነበረው የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲ የአገራችን ውስጣዊ ችግሮችና የአደጋ ተጋላጭነታችን ለአገራዊ ደህንነትና ህልውናችን ያላቸው ትርጉም ተገቢውን ትኩረት ሳያገኙ ቆይተዋል፡፡

ከደርግ ውድቀት በኋላ ባለፉት አሥራ ሁለት ዓመታት የውጭ ፖሊሲያችን ወሳኝ መሠረቶች መንግሥት የሚያራምዳቸው የአገር ውስጥ

ፖሊሲዎች መሆናቸውን ከግንዛቤ በማስገባት ልማት ላይ ትኩረትና ርብርቦሽ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ በንድፈ ሀሳብ ደረጃ ተቀባይነት አግኝቶ የነበረ ቢሆንም ውስጣዊ ችግሮች ለአገራዊ ህልውናችን ያላቸው ትርጉም ወጥነት ባለውና በተገቢው ደረጃ ትኩረት አግኝቶ ነበር ማለት አስቸጋሪ ነው፡፡ በመሆኑም የአገራችንን ውስጣዊ ሁኔታ በሚገባ ያገናዘበ የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጅ ማውጣት ለህልውናችንና ለደህንነታችን ወሳኝ መሆኑ ታምኖበታል፡፡

ይህ የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጅ ብሔራዊ ጥቅማችንን የማስጠበቅና አገራዊ ህልውናችንን የማረጋገጥ ተልዕኮ ያለው ሆኖ የተቀረፀ ሲሆን፣ መሠረታዊ ይዘቱ ሥር ነቀል የሆነ በውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲ ላይ የአመለካከት ለውጥ እንዲኖር የሚያስገድድ ነው፡፡ ይህም ርምጃ በአገራችን ታሪክ ውስጥ አዲስ ምዕራፍ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ፖሊሲውም ሆነ ስትራቴጅው በዋነኛነት የሚያጠነጥኑት ሕዝቡ በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበትን ፈጣን ልማትና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታን እውን በማድረግና ለዚሁ የተመቻቸ ሁኔታን በመፍጠር ዙሪያ ነው፡፡ ለዚህም ሲባል የፖሊሲውና የስትራቴጅው መነሻ በአገሪቱ ህልውና ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ የአገሪቱ ውስጣዊ ችግሮችና የአደጋ ተጋላጭነት እንደሆነና ዋነኛ ትኩረቱም በአገር ውስጥ የሚደረገው እንቅስቃሴ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት አካሄዳችንን ከውስጥ ወደ ውጭ በማድረግ የራሳችንን የቤት ሥራ በቅድሚያ እንድንሠራና ውስጣዊ ጉድለቶችን ከለየን በኋላ የውጭ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጅው እነዚህን ክፍተቶች ለማሟላት እንዲያስችል ሆኖ ተቀርጿል፡፡ ውጫዊ ሁኔታዎች የሚቃኙት በአገር



ውስጥ ካለው ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት በመሆኑ ከዚህ በመቀጠል ተዘርዝሮ የቀረበው ፖሊሲና ስትራቴጅ ለአገራዊ ደህንነትና ህልውናችን ከፍተኛ ፋይዳ እንደሚኖረው የሚያጠያይቅ አይደለም፡፡

ይህ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጅ በመጀመሪያው እትም ላይ የተከሰቱ የአርትኦት ግድፈቶችን በማስተካከልና ልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ካካሄዱት ውይይት ጠቃሚ ሆነው የተገኙ አስተያየቶችን በማካተት ተሻሽሎ የቀረበ ነው፡፡

# የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲና ስትራተጂ

## ክፍል I
## መሰረተ-ሀሳቦች፣

## 1. የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲያችን መነሻዎች፣

የደህንነት ፖሊሲ በመሰረቱ አገራዊ ህልውናን የማስጠበቅ ጉዳይ ነው። የደህንነት መጀመሪያም መጨረሻም አገራዊ ህልውና ማረጋገጥ ነው። ሌሎች የአገራዊ ደህንነት ጉዳዮች የሚነሱት ህልውና ከተረጋገጠ በኋላ ነው። ከብሄራዊ ጥቅም አኳያም መነሻውና መድረሻው አገራዊ ህልውናን የማረጋገጥ ጉዳይ ነው። ሌላው ነገር ሁሉ የሚመጣው አገራዊ ህልውና ከተረጋገጠ በኋላ ነው። የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲ ከሁሉም ነገር በፊትና ከሁሉም ነገር በላይ አገራዊ ህልውናን ለማረጋገጥ የሚቀረፁ መሆን ይገባቸዋል። በዚህ መሰረታዊ ጉዳይ ላይ በመመስረት የብልፅግና፣ የተሟላ ሰላምና መረጋጋት የመሳሰሉት ጉዳዮች ይነሳሉ። እነዚህን ጉዳዮች ለማሟላት የሚያስችል ፖሊሲ ለመቅረፅ ለቀረፃ ስራው መነሻ የሚሆኑ ጉዳዮችን በውል መለየት ያስፈልጋል።

### 1.1. ልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ እንደፖሊሲ መነሻ፣

በአገራችን ህዝቡ በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበት ፈጣን



ልማት ማረጋገጥ ህዝቡ ከድህነት፣ ከድንቁርናና ከኋላ ቀርነት ተላቆ የተመቻቸ ኑሮ እንዲኖር ለማድረግ ወሳኝ ነው። የአገራችን ህዝብ እጅግ መሰረታዊ የሆነው ጥቅም ድህነትን፣ በሽታንና ድንቁርናን ማስወገድ ነው። የፈጣን ልማት ጉዳይ የህዝቡን ኑሮ የማሻሻል ጉዳይ ብቻ ሳይሆን አገራዊ ህልውና የማረጋገጥ ጉዳይም እንደሆነ ይታወቃል። ፈጣን እድገትን አረጋግጠን ህዝቡ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ ካልቻልን በስተቀር በአገራችን ከፍተኛ ብጥብጥና መበታተን እንደሚመጣ በፍፁም አያጠራጥርም። በመሆኑም ህዝቡ በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበት ፈጣን ልማት ማረጋገጥ የህዝቡን ኑሮ ደረጃ በማሻሻል፣ አገራችንን ከሚዘገንን እልቂትና ብተና ለማዳን የሚያስችል ወሳኝ ጉዳይ ነው። የመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ጥቅምና ህልውና የሚንጠለጠልበት መሰረታዊ ጉዳይ ነው።

የዴሞክራሲ ስርአት በአገራችን እውን እንዲሆን ማድረግ፣ የህዝቦችና የዜጎች መብቶች ተከብረው፣ መልካም አስተዳደር ሰፍኖ፣ ህዝባችን በተረጋጋ መንፈስ ሰርቶ እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችለን መሳሪያ ነው። ዴሞክራሲ መላው ህዝብ የጋራ አላማና አስተሳሰብ ይዞ አገሩን እንዲያለማና እንዲገነባ ለማድረግ የሚያስችለን ቁልፍ መሳሪያ ነው። የተለያዩ ብሄሮችና እምነቶች ባሉባት አገራችን ሁላችንም ተከባብረንና ተፈቃቅረን ለመኖር የሚያስችለን ዴሞክራሲ ነው። የዴሞክራሲ ስርአት በአገራችን እውን ካልሆነ በብሄርና በእምነት ተነጣጥለን፣ በመብቶች መረገጥ ተቃቅረን መበጣበጣችንና ሰላም መጥፋቱ፣ ልማት ቀርቶ ድህነት መስፋፋቱ ብሎም ለእልቂትና ለብተና መዳረጋችን አይቀርም።

በመሆኑም ዴሞክራሲን በአገራችን እውን የማድረግ ጉዳይ ልማትና መልካም አስተዳደርን የማስፈን ጉዳይ ብቻ ሳይሆን እልቂትና ብተናን የማስቀረት፣ ብሄራዊ ህልውናችንን የማረጋገጥ ጉዳይም ጭምር ነው። የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ጥቅምና ህልውና ብሎም ብሄራዊ ህልውናና ጥቅምን የማስጠበቅ እጅግ መሰረታዊና ወሳኝ ጉዳይ ነው።

የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ፣ የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲ መሰረታዊ አገራዊ ጥቅምን የማስጠበቅና አገራዊ ህልውናን የማረጋገጥ ተልዕኮ ሊኖራቸው ይገባል ተብሎ ከሞላ ጎደል በሁሉም ዘንድ ይታመናል። የአገራችን የደህንነትና የውጭ ጉዳይ ፖሊሲም ከዚህ የተለየ ተልዕኮ ሊኖረው አይችልም። የአገራችን ብሄራዊ ጥቅም ማለት የምልአተ ህዝቡ ጥቅም ከመሆን ውጭ ሌላ ሊሆን አይችልም፣ አይገባምም። እጅግ መሰረታዊ የሆነውና ወሳኝ የሚባለው የምልአተ-ህዝቡ ጥቅም ደግሞ ፈጣን ልማትን ማረጋገጥና ከዚሁ በየደረጃው ተጠቃሚ መሆን ማለት ነው። የምልአተ ህዝቡ ጥቅም በአገራችን ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን ማድረግ ነው። ስለሆነም አገራዊ ጥቅማችንን የሚያስጠብቅ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ መቅረፅ አለብን ካልን፣ በአገራችን ፈጣንና ህዝቡ በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበት ልማትን ለማረጋገጥ፣ ዴሞክራሲ በአገራችን ስር እንዲሰድ ለማድረግ የሚረዳ ፖሊሲ መቅረፅ አለብን ማለት ነው። የአገራዊ ጥቅማችን አልፋና ኦሜጋ ልማትና ዴሞክራሲ ናቸው፣ የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲዎቻችን መነሻና መድረሻም ልማትና ዴሞክራሲ ሊሆኑ ይገባል።



የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲ በቅድሚያ አገራዊ ህልውናን ማረጋገጥ መቻል እንዳለበት እሙን ነው። አገራዊ ደህንነት ማረጋገጥ ማለት ምልአተ-ህዝቡን ከእልቂትና ከብጥብጥ ማዳን ማለት ነው። አገሪቱን ከማያባራ ጦርነትና መበታተን ማዳን ማለት ነው። ፈጣንና ህዝቡ በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበት ልማት ካልተረጋገጠ፣ ዴሞክራሲ በአገራችን እውን ካልሆነ እልቂቱና መበታተኑ እንደማይቀርልን በፍፁም አያጠራጥርም። በመሆኑም አገራዊ ህልውናችንን ማረጋገጥ የሚችለው ወሳኙ ጉዳይ ልማትና ዴሞክራሲን እውን ማድረግ ነው ማለት ይቻላል። የአገራዊ ህልውናችን መነሻና መድረሻም ዴሞክራሲንና ልማትን እውን ማድረግ ነው። የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲያችን መነሻና መድረሻም ከዚህ ውጭ ሌላ ሊሆን አይችልም።

አገራችንን ከእልቂትና ብጥብጥ ለማዳንና ሰላም ለማስፈን የሚቻለው ህዝቡ በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበት ፈጣን ልማት በማረጋገጥና ዴሞክራሲን እውን በማድረግ በመሆኑ የዴሞክራሲና የልማት አጀንዳችን እዚያው ሳለ የሰላም ምንጭና የሰላም አጀንዳም ጭምር ነው። የሰላም ምንጭ ልማትና ዴሞክራሲ የመሆኑን ያህል ሰላም ደግሞ ልማትን ለማረጋገጥ ዴሞክራሲን እውን ለማድረግ እጅግ ተፈላጊ ነው። በመሆኑም የአገራዊ ደህንነታችን መሰረት ልማትና ዴሞክራሲ ነው ስንል የሰላማችን ዋነኛ ምንጭ ልማትና ዴሞክራሲ ነው ስንል ሰላም በፈንታው ልማትንና ዴሞክራሲን እውን ለማድረግ ተፈላጊ እንደሆነ ታሳቢ በማድረግ ጭምር ሊሆን ይገባል።

ህዝቡ በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበት ፈጣን ልማትን ማረጋገጥ፣ ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር በአገራችን እንዲሰፍን ማድረግ የአገራዊ ጥቅማችን፣ የአገራዊ ህልውናችን አልፋና ኦሜጋ ነው፣ ሁሉም ሌሎች ነገሮች ከዚህ ቀጥለው የሚታዮና በዚሁ ላይ የተመሰረቱ ብቻ ናቸው:: አገራዊ ጥቅማችንና ደህንነታችንን ለማረጋገጥ የሚቀረፅ የውጭ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲም አላማው በአገራችን ልማትና ዴሞክራሲ እውን እንዲሆኑ ማገዝ ነው መሆን ያለበት:: ይህንኑ ለማድረግ የሚያስችል የውጭ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲ ትክክለኛና ጠቃሚ ይሆናል:: ምንም አይነት ሌላ ጠንካራ ጎን ቢኖረውም፣ ምንም አይነት የተራቀቀ ይዘት ቢኖረውም፣ ልማትና ዴሞክራሲን እውን ለማድረግ የማያስችል የአገራዊ ደህንነትና የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ፣ ከንቱና አላማ የለሽ ነው:: የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲዎቻችን ወሳኝና መሰረታዊ መነሻም ልማትና ዴሞክራሲያችን ነው::

## 1.2. አገራዊ ክብር እንደፖሊሲ መነሻ፣

አንዳንድ ወገኖች አገራዊ ክብርን ማስጠበቅን እንደአንድ መሰረታዊ የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲ አላማ አድርገው ያስቀምጣሉ:: አገራዊ ክብራችን ተጠበቀ ወይም ተነካ ብለው አገሮችን በወዳጅነት ወይም በጠላትነት የመፈረጅ አዝማሚያም ያሳያሉ:: ሌሎች ወገኖች አገራዊ ክብር የሚባለው ጉዳይ የሌሎች ስራዎች ውጤት ነው፣ በመሆኑም እንደ አላማ መቀመጥ ካለባቸው የአገራዊ ክብሩ ምንጭ የሆኑ ጉዳዮች እንጅ አገራዊ ክብር ራሱን እንደቻለ አላማ ሊቀመጥ አይችልም ይላሉ::



ጥቂቶች የአገራዊ ክብር ጉዳይ የሚያነሱ አገሮች ባለፈው ታሪካቸው የሚኖሩ ቀጣይ ጉዟቸው የጨለመባቸው ወይም ወራሪ አላማን ለማራመድ ሰበብ የሚፈልጉ አገሮች ናቸው ይላሉ:: የአገራችንን ብሄራዊ ክብር የማስጠበቅ ጉዳይ በኛ ሁኔታ ምን አይነት ቦታ ሊሰጠው ይገባዋል የሚለው ጉዳይ በጥሞና መመርመር ያለበት ነው::

ህዝቦቻችን ለውጭ ገዥዎች ሳይንበረከኩ ነፃነታቸውን አስከብረው መቆየታቸው፣ በዚህ ረገድም ለቅኝ ገዥዎች ሳንንበረከክ የቆየን ብቸኛ የአፍሪካ አገር በመሆናችን እንኮራለን፣ ልንኮራም ይገባናል:: በታሪካችን ሂደት ዕፁብ ድንቅ የሚባሉ የፈጠራ ውጤቶችን ማስገኘታችንም ያኮራናል፣ ሊያኮራንም ይገባል:: እነዚህ ሁሉ ያለፉት ትውልዶች በጥረታቸው፣ በላባቸውና በደማቸው ያስገኟቸው የስራ ውጤቶች ናቸው:: ስለሆነም ያሁኑ ትውልድ እየኮራ ያለው ባለፉት ትውልዶች የስራ ውጤት ነው:: የኩራቱ ምንጭ ሌላ ነገር ሳይሆን ተጨባጭ የስራ ውጤት ነው:: ከስራ ውጤትም በወሳኝ መልኩ ያሁኑ ትውልድ የስራ ውጤት ሳይሆን የቀደምት ትውልዶች የስራ ውጤት ነው::

የአሁኑ ትውልድ ሊኮራባቸው የሚገቡ፣ ሊጠብቃቸውና ሊንከባከባቸው የሚገቡ ከላይ የተጠቀሱት እሴቶች የመኖራቸውን ያህል ሊያሳፍሩትና ሊያሸማቅቁት የሚገቡ የአገራዊ ውርደት ገፅታዎችም አሉ:: በአሁኑ ሰአት አገራችን በዋነኛነት ተመፅዋችና ተስፈኛ ነች:: ሌላው ቀርቶ ራሳችንን መመገብ አቅቶን በየአመቱ ምግብ ልመና እንደህዝብ ወደአደባባይ እየወጣን ነው:: ከልመና

በላይ የአንድን ህዝብ ክብር የሚገፍና አንድን ህዝብ ለከፋ ውርደት የሚዳርግ ነገር የለም:: የልማት ስራችን የውጭ ርዳታና ብድር ካልታከለበት መነቃነቅ የሚችል አይደለም:: ስለሆነም ብድሩንና ርዳታውን ለማግኘት ደጅ ጠኝ መሆን አለብን:: ብድርና ርዳታ ለማግኘት የአበዳሪዎቻችንና የረዳቶቻችንን መልካም ፈቃድ ማግኘትና ፍላጎታቸውን ማሟላት አለብን:: በዚህ ደረጃ ላይ እያለን ዳገት የሚወጣ ነፃነት አለን ብሎ መናገር አያስደፍርም:: ይህም የአገራዊ ውርደት፣ የሃፍረትና መሸማቀቃችን አንድ ምንጭ ነው::

በጥቅሉ ሲታይ አገራችን በአፍሪካ ነፃነትዋን አስከብራ የኖረች ብቸኛዋ አገር፣ ረጅምና የሚያኮራ የስልጣኔ ታሪክ ያላት አገር ብትሆንም አሁን በተጨባጭ የአገሮች ሁሉ ጭራ ነች:: በልማቱ ከኛ ኋላ የሚሰለፉት በጣት የሚቆጠሩ አገሮች ናቸው:: በመሆኑም በርካታው ወጣት ምኞቱ አገሩን ለቆ በስደት ለመኖር የሆነበት፣ የብዙው ምኞት እንደምንም ብሎ አውሮፖና አሜሪካ ሄዶ መኖር የሆነበት ደረጃ ላይ ደርሰናል:: ይህ ያልተሳካለት በመካከለኛው ምስራቅ በግርድና መኖርን እንደትልቅ ፀጋ ቆጥሮ ይህንን «ዕድል» ለማግኘት ህገ-ወጥ ተግባራት ሳይቀር የሚፈፅምበት ደረጃ ላይ ደርሰናል:: በጎረቤት አገሮች በግርድና መኖር እንደፀጋ በሚወሰድበት አገር የሚኖር ዜጋ ካላፈረ፣ ካልተሸማቀቀ፣ ውርደቱ ወገቡን ካልቆረጠው ባለፉት ትውልዶች የስራ ውጤት ተኩራርቶ ከተኮፈሰ የህዝብና የአገር ፍቅሩ የቱ ላይ እንደሆነ ለማወቅ አስቸጋሪ ነው::



በመሆኑም ባለፉት ትውልዶች የስራ ውጤት የምንኮራና መኩራት የሚገባንን ያህል አገራችን አሁን ባለችበት ደግሞ እናፍራለን፣ እንሸማቀቃለን:: ያለፉት ትውልዶች የስራ ውጤት የኩራታችን ምንጭ የሆነውን ያህል የአሁኑ ትውልድ ያለበት ሁኔታ የአስከፊ አገራዊ ውርደት ምንጭ መሆኑን በምሬት እናስቀምጣለን:: ባለፉት ትውልዶች የስራ ውጤት መኩራትና ይህንኑ መንከባከብ የሚገባን ቢሆንም አገራዊ ክብራችንን ለመጠበቅ ደግሞ በመጀመሪያ ደረጃና በዋነኛነት የአገራዊ ውርደታችንን ምንጭ ማድረቅ ይኖርብናል:: ይህ የውርደታችን ምንጭ ሳይደርቅ የምናድርባት እያንዳንዷ ሌሊት እሾህ ሆኖ ልትወጋንና እንቅልፍ ልትነሳን ይገባናል::

የአሁኑ የአገራዊ ውርደታችን መሰረታዊ ምንጭ ድህነትና ኋላ ቀርነት ነው:: የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር እጦት ነው:: ህዝባችንን ከዚሁ ውርደት ለማላቀቅ አንድ የጋራ አገራዊ እምነትና አመለካከት ይዘን ተከባብረንና ተፈቃቅደን በአንድነት ለመረባረብ አለመቻላችን ነው:: በአንድ ቃል የአገራዊ ውርደታችን ብቸኛ መፍትሄና ምንጩን ለማድረቅ የሚያስችለን አማራጭ ፈጣን፣ ህዝቡ በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበት ልማትና ዴሞክራሲን እውን ማድረግ ነው:: አገራዊ ክብራችንን ማስጠበቅ እንደፖሊሲ መነሻ መቅረብ ካለበት፣ ለዚሁ ሲባል ጭምር ከምንም ነገር በላይ በልማትና በዴሞክራሲ ላይ በመረባረብ አገራዊ ክብራችንን ማስጠበቅ በሚል መልክ ብቻ ነው ሊወሰድ የሚችለው:: በመሆኑም አገራዊ ክብርን የማስከበር አላማ የፖሊሲ መነሻ ሊሆን የሚችለው ራሱን ችሎ በተናጠል ሳይሆን ከብቸኛው ምንጩ ጋር

ተያይዞ ማለትም ልማትንና ዴሞክራሲን እውን በማድረግ ገፅታው ነው። አገራዊ ክብርን የማስጠበቅ ጉዳይ ከዚህ አኳያ የሚጨምረው ነገር ካለ ለዴሞክራሲና ለልማት የምናደርገው ርብርብ በፍፁም ፋታ የማይሰጥ መሆኑን፣ ከዚህ ውጭ ያለው ነገር በምንም አይነት መንገድ ከዋናው አላማችን ሊያዘናጋን የማይገባ መሆኑ ይበልጥ ግልፅ ሆኖ እንዲቀመጥ በማድረግ መልኩ ነው።

በታሪክ ከባድ አገራዊ ውርደት የደረሰባቸው አገሮች የውርደቱን ምንጭ ለይተው በማወቅ፣ ሁሉም ነገር ይህንን የውርደት ምንጭ ለማድረቅ አላማ ተገዥ እንዲሆን አድርገው በመረባረብ አላማቸውን አሳክተዋል። በዚህ ረገድ አንድ ሁለት ምሳሌዎችን ባጭር ባጭሩ መጥቀስ መርሁን በይበልጥ ግልፅ ለማድረግ ያስችላል።

የጃ-ንና የኢትዮጵያ ታሪክ በአንዳንድ ገፅታው ተመሳሳይነት አለው። ሁለቱም አገሮች በረጅም ታሪካቸው ለውጭ አገዛዝ ሳይንበረከኩ የቆዩ ናቸው። ሁለቱም አገሮች በተመሳሳይ ወቅትና በተመሳሳይ ምክንያት በራቸውን ጥርቅም አድርገው ዘግተው ከውጭ ጋር ላለመነካካት ወስነው የነበሩ ናቸው። ሁለቱም የየራሳቸውን ዘመነ-መሳፍንት ያሳለፉና በሂደትም ጠንከር ያለ ማዕከላዊ መንግስት ለመመስረት የተጣጣሩ ናቸው። ሁለቱም በተለያዩ ምክንያቶች የቀረቀሩትን በር ከፍተው ከውጭ ሃይሎች ጋር ለመገናኘት የተገደዱ ናቸው። ይሁንና ጃ-ን በርዋን ለመክፈት ከተገደደች በኋላ የተከተለችው አቅጣጫ በሂደት እጅግ የላቀ ልማትንና ዴሞክራሲን አጎናፅፎ ከአገራዊ ውርደት ለዘለቄታው



እንድትላቀቅ ያደረጋት ሲሆን የኢትዮጵያ እጣ ፈንታ ግን ከዚሁ በእጅጉ የተለየ ነው።

ጃ-ን ለምዕተ-አመታት የውጭ ዜጎች በተለይም ምዕራባውያን ወደአገርዋ እንዳይገቡባት በርዋን በተሳካ ሁኔታ ቀርቅራ ከቆየች በኋላ በልማት ከርስዋ የላቁ አገሮች ከብረት የተሰሩ መርከቦችን (በወቅቱ ጃ-ናውያን ጥቁር መርከቦች ብለው የጠሩዋቸውን) ይዘው በርዋን በርግደው ገቡ። በዚህ ሳይወሰኑ የራሳቸውን ጥቅም የሚያስጠብቅና ጃ-ንን ክፉኛ የሚያዋርድና የሚጎዳ ስምምነት እንድትፈራረምም አስገደዱዋት። ይህ ከፍተኛ አገራዊ ውርደት በጃ-ን ውስጥ እጅግ መሰረታዊ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ለውጥ አስከተለ። ጃ-ናውያን ይህ ውርደት የደረሰባቸው በእድገት ወደኋላ በመቅረታቸው መሆኑን እንዲገነዘቡ አደረጋቸው። በዘመነ መሳፍንት ተበታትነው በመዳከማቸው መሆኑን እንዲያስተውሉ አደረጋቸው። አርቀው ማሰብ የቻሉት የገዥው መደብ አባላት ይህ ነገር ከስሩ ካልተነቀለ በስተቀር ጃ-ን ህልውናዋን ጭምር እንደምታጣ ግልፅ ሆነላቸው። ሁሉም ነገር የውርደቱን ምንጭ ለማድረቅ አላማ ተገዥ እንዲሆን ማድረግ እንዳለባቸው ተገንዝበው ለዚሁ አላማ ሌት ተቀን መረባረብ ጀመሩ።

በደረሰባቸው ብሄራዊ ውርደት ከልብ የተቆጡት ጃ-ናውያን ሃብታም አገር፣ ጠንካራ መከላከያ የሚል መፈክር አንስተው ውርደቱን ከምንጩ ለማድረቅ ተንቀሳቀሱ። የመጀመሪያው ወሳኝ ርምጃቸው ጠንካራ ማዕከላዊ መንግስትን

ማቋቋም ነበር፡፡ በመሆኑም በዘውዳዊ አገዛዝ ስር የሜጅ ሪስቶሬሽን እየተባለ የሚጠራ ፈፅሞ ጠንካራ ማዕከላዊ መንግስት እ.ኤ.አ. በ1868 አ.ም መሰረቱ፡፡ ከዚያ በኋላ ሃብታም አገርና ጠንካራ መከላከያን ለመፍጠር ከበለፀጉት አገሮች መማር እንዳለባቸው አምነው ይህንኑ ልምድ ለመቅሰም ወደ አውሮ- በስፋት ተሰማሩ፡፡ ከአውሮ- ሙያተኞች ቀጥረው ሌት ተቀን ተማሩ፡፡ ፈጣን ኢኮኖሚያዊ እድገት ለማረጋገጥ፣ የቴክኖሎጂ ደረጃቸውን ለማሻሻል ሌት ተቀን ተረባረቡ፡፡ ከዚህ አላማ የሚያዘናጋቸውን ነገር ሁሉ ወደጎን እያሉ፣ እየተሸከሙ ጥርሳቸውን ነክሰው ሃብታም አገርና ጠንካራ መከላከያን የመመስረት ህልማቸውን እውን ለማድረግ መሰራት ያለበትን ስራ ሁሉ ለመስራት ተረባረቡ፡፡

ሰላሳ አመት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ጃ-ን ከታላላቆቹ የአለም አገሮች አንዷ በመሆን ከሌሎች ጋር እየተወዳደረች ቅኝ ግዛት ወደማስፋፋትም ገባች፡፡ እ.ኤ.አ. በ1904 አ.ም ላይ ከአውሮፖ ታላላቅ አገሮች አንዷ የሆነችውን ሩስያን በጦርነት አሸነፈች፡፡ በመጀመሪያ ታይዋንን ቀጥላም ኮርያን በቅኝ ግዛትነት ያዘች፡፡ ይህ የተሳካ እንቅስቃሴ በሂደት እብሪትን እየፈጠረ በመምጣቱ በ1930ቹ አመታት መጀመርያ መላ ቻይናን በሂደትም መላውን ምስራቅ ኤስያ በቁጥጥር ስር ለማዋል ተንቀሳቀሰች፡፡ በአሜሪካም ላይ ከፍተኛ ጥቃት ሰነዘረች፡፡ እብሪቱ ተመልሶ ጃ-ን አመድ እንድትሆን አደረጋት፡፡ በሁለተኛው አለም ጦርነት ተሸንፋ ኢኮኖሚዋ ደቀቀ፣ አገሪቱ ወደመች፡፡ ለተወሰኑ አመታትም በውጭ ወታደራዊ አገዛዝ ስር ወደቀች፡፡ ግላዊም ሆነ አገራዊ ውርደትን ከመቀበል ሞትን የሚመርጡት ጃ-ናውያን፣ በብዛት



ራሳቸውን ገደሉ፡፡ አገሪቱ በአጠቃላይ ግን ይህንን ዳግመኛ ውርደት በሳሙራይ ባህሏ አሟሟቷን በማሳመር ራስዋን በመግደል ልትቋቋመው አልመረጠችም፡፡ አሟሟትን ከማሳመር አኗኗርን ማሳመር መርጣ ሁለተኛውን ውርደት ከምንጩ ለማድረቅ ነው የወሰነችው፡፡

በላያቸው ላይ የተጫነባቸውን ወታደራዊ አገዛዝ ከአገራቸው በአፋጣኝ ለማላቀቅ ያላቸው ብቸኛ አማራጭ የታዘዙትን መቀበል መሆኑን ተገንዝበው የተባሉትን ሁሉ ፈፀሙ፡፡ ለዳግመኛ ውርደት የዳረጋቸው ፀረ-ዴሞክራሲ አገዛዝና ወታደራዊነት መሆኑን ተገንዝበውና የአሜሪካ ወታደራዊ አገዛዝም ይህንኑ እንዲያስወግዱ ስላዘዘችው ይህንኑ ተቀብለው ፈፀሙ፡፡ በዚሁ መልኩ በአሜሪካው ጄኔራል የሚመራው አገዛዝ ተወግዶላቸው ነፃነታቸውን ተቀዳጅተው የዳግመኛ ውርደታቸውን ምንጭ ለማድረቅ ተረባረቡ፡፡ የዴሞክራሲ አገዛዝን የሚያሰፍን እብሪትና ወታደራዊነትን ለማስወገድ የሚረዳቸው ህገ-መንግስት ቀርፀው በጥብቅ ተግባራዊ ወደማድረግና አገራቸውን መልሰው ወደመገንባት ገቡ፡፡ ከሃያ አመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በአለም በስፋቱ በሁለተኝነት ደረጃ የሚገኝ ኢኮኖሚም ለመገንባት ቻሉ፡፡ ከፀረ-ዴሞክራሲና ከወታደራዊ እብሪት ነፃ የሆነ ስርአትም ገነቡ፡፡

የጃ-ን ልምድ ከጃ-ን ልዩ ሁኔታ ጋር የተያያዘ ስለሆነ እንዳለ በየትኛውም አገር ሊደገም አይችልም፡፡ የሚወሰድ ትምህርት ግን አለ፡፡ ከጃ-ኖች በላይ ለግልና ለአገር ክብር ትኩረት የሚሰጥ የለም፡፡ በጦርነት መማረክ ትልቅ ውርደት ተደርጎ ስለሚቆጠር እንኳን ወታደር ሲቪልም ቢሆን ከመማረክ

መሞትን ይመርጥ የነበረበት አገር ነው:: በጎራዴ ራስን ገድሎ አሚሚትን ማሳመር እንደ ትልቅ ነገር የሚወሰድበት አገር ነው:: እንደህዝብና እንደአገር ትልቅ ውርደት ሲያጋጥማቸው ግን ምርጫቸው አሚሚትን ማሳመር አልነበረም:: የውርደቱን ምንጭ ተረድተው ውርደቱን ከምንጩ ለማድረቅ በአንድነት ሌት ተቀን መረባረብ፣ ይችን ለመፈፀም ሁሉንም ነገር ችለውና ተሸክመው ሌት ተቀን መረባረብ ነበር ምርጫቸው:: ይህን በማድረጋቸው እጅግ የተከበሩ አገርና ህዝብ ለመሆን በቅተዋል:: በተመሳሳይ ሁኔታ የሚገኙ እንደኛ ያሉ አገሮች ከዚህ የሚማሩት መሰረታዊ ትምህርት የአገራዊ ውርደታቸውን ምንጭ ጠንቅቆ በማወቅ ሁሉን ነገር ምንጩን ለማድረቅ አላማ ተገዥና አገልጋይ እንዲሆን በማድረግ ሌት ተቀን የመረባረብ አስፈላጊነት ነው::

በተመሳሳይ ሁኔታ ከጀርመኖች ረጅምና የተወሳሰበ ታሪክ አንድ የተወሰነ ምዕራፍ ቀንጭቦ በመውሰድ ይህንኑ ማረጋገጥ ይቻላል:: ጀርመን በፊውዳል አገዛዝ ተተብትባ ከ300 በማያንሱ የተለያዩ የተቀናጣጠቡ ግዛቶች ተከፋፍላ በነበረችበት ወቅት ናፖልዮን የጀርመንን አካባቢ ወሮ የተቀናጣጠቡትን ግዛቶች በከፍተኛ ደረጃ ቀንሶ ከነዚህ ከተቀናጣጠቡት ግዛቶች ውስጥ ላቅ ያለ ቦታ የነበራትን ፕራሺያ በጦር ድል መቶ ከፍተኛ ውርደት እንዳከናነባት የታሪክ መፃህፍት ይዘግባሉ:: ፕራሺያ በናፖልዮን ከተሸነፈች በኋላ የፈረመችው የሰላም ስምምነት በታሪክ ውስጥ በአዋራጅነታቸው ከሚታወቁት ስምምነቶች አንዱ እንደሆነ የታሪክ ተመራማሪዎች ይመሰክራሉ::



የፕራሺያ መሪዎች ከወደቁ በኋላ መፈራገጥ ለመሳሳጥ መሆኑን በመገንዘብ ከፊውዳል አገዛዝ ነፃ የወጣውን የፈረንሳይ አርሶ አደር ይዞ ድባቅ ከመታቸው ናፖልዮን ጋር እልህ በመጋባት አሚሚታቸውን ለማሳመር አልመረጡም:: የአገራዊ ውርደታቸው ምንጭ ምን እንደሆነ በሚገባ አጢነው ይህንኑ ከምንጩ ለማድረቅ ነው የተረባረቡት:: ችግራቸው ወታደራዊና ኢኮኖሚያዊ እንደሆነ የተገነዘቡት ፕራሺያኖች እነዚህን ለማስተካከል ቅድሚያ ሰጥተው ነው የተረባረቡት::

በወታደራዊው መስክ የፕራሺያ ጭሰኛ ነፃ የወጣውን የፈረንሳይ አርሶ አደር መቋቋም እንደማይችል ተገንዝበው ጭሰኝነትን ለማስወገድ፣ የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ለሁሉም ዜጋ ለማዳረስ ወስነው እጅግ ውስብስብ በሆነ አኳኋን ተግባራዊ አደረጉት:: በነፃ አርሶ አደር ላይ የተገነባውን የናፖልዮን የውጊያ ጥበብ ተወዳዳሪ በሌለው አኳኋን ተንትነው ተጠቀሙበት:: በሂደትም በውጊያ ብቃቱ ተወዳዳሪ የሌለው የመከላከያ ሃይል ለመገንባት ቻሉ:: የአንድ ብሄር ህዝብ የሆነው የጀርመን ህዝብ መበታተኑ ለኢኮኖሚ እድገታቸው ማነቆ ሆኖ በመገኘቱ ደረጃ በደረጃ መጀመሪያ የኢኮኖሚ ህብረት ቀጥሎም የፖለቲካ ህብረት እንዲመሰረት አደረጉ:: ይህንኑ እ.ኤ.አ. በ1871 አ.ም ላይ ፈረንሳይን በጦርነት አሸንፈው የፖለቲካ ህብረታቸውን የፈረንሳይ ነገስታት መናኸሪያ በነበረው ቬርሳይ በተባለ ቦታ ላይ አከበሩ:: ውርደታቸው ተሽሮ በእብሪት ተተካ:: እብሪቱ ሄዶ ሄዶ ለሌላ ውርደት ዳረጋቸው::

ከጀርመኖችም የምንማረው መሰረታዊ ትምህርት አገራዊ ውርደት በመንጠራራት ወይም አሚሚትን በማሳመር እንደማይወገድ ነው፡፡ አገራዊ ውርደት የሚወገደው ምንጩን ለይቶ በማወቅ ምንጩን ለማድረቅ ሌት ተቀን በመረባረብ ብቻ ነው፡፡ አገራዊ ውርደት በሆነ ባልሆነ ነገር ከዋናው ርብርብ በመዘናጋት አይወገድም፡፡ መላውን ህዝብ ለአንድ አላማ፣ የብሄራዊ ውርደቱን ምንጭ ለማድረቅ አላማ አንቀሳቅሶ፣ ከዚህ መሰረታዊ አላማ የሚያዘናጋን ማንኛውንም ነገር አስወግዶ፣ ይህን አላማ ለማሳካት አማራጭ የሌለው ሆኖ እስከተገኘ ድረስ ማንኛውንም ነገር ችሎና ተሸክሞ ከዋናው አላማ ለአንድ አፍታም አይን ሳይነቅሉ በመረባረብ ብቻ ነው የሚወገደው፡፡

እኛም ባለፉት የኢትዮጵያ ትውልዶች የስራ ውጤት እንኮራለን፣ ልንኮራበትና ልንንከባከበውም ይገባል፡፡ ከዚያም በላይ በአገራችን ድህነት ኋላቀርነትና በመልካም አስተዳደር እጦት ምክንያት በየዕለቱ እንደእሾህ ሊወጋን የሚገባ አገራዊ ውርደት ተከናንበናል፡፡ ይህንን የውርደት ምንጭ ከማድረቅ አላማ ለአንድ አፍታም አይናችንን ሳንለቅ፣ ለዚሁ ሲባል ተፈላጊ ሆኖ የተገኘውን ነገር ችለንና ተሸክመን በመረባረብ ልናደርቀው ይገባል፡፡ በልማትና በዴሞክራሲ ውርደታችንን መሻር ይኖርብናል፡፡ አገራዊ ክብርን የውጭ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲ መነሻ አድርጎ መውሰድ ማለት ልማትንና ዴሞክራሲን እውን ለማድረግ የብሄራዊ ውርደታችን ማስወገጃና የአገራዊ ክብራችን ማስጠበቂያ ብቸኛ መሳሪያ አድርጎ መውሰድ ማለት ነው ይቻላል፡፡



## 1.3. ግሎባላይዜሽን እንደፖሊሲ መነሻ፣

በአገራችን ፈጣንና ህዝቡ በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበትን ልማት፣ ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር እውን ለማድረግ የሚካሄደው ርብርብ በአካባቢያችንና በአለም ደረጃ ከሚታየው ሁኔታ ተነጥሎ ተግባራዊ ሊሆን አይችልም፡፡ የአለም ኢኮኖሚ በግሎባላይዜሽን ሂደት በጥብቅ ተሳስሯል፣ አለም አቀፍ የስራ ክፍፍል ተፈጥሯል፡፡ ከዚህ ውጭ የሚሆን ማንም አገር የለም፡፡ ወይ በአምራችነት ወይም በተመፅዋችነትና በተስፈኛነት የግሎባላይዜሽኑ አካል ከመሆን የሚድን አገር የለም፡፡ ተመፅዋችነትንና ተስፈኛነትን አስወግዶ በአምራችነት ከተሰለፈውም ቢሆን ቁንጮው ላይ የተቀመጠና ከስር የሚንደፋደፍ አገር መኖሩ አልቀረም፡፡ ከተመፅዋችነትና ከተስፈኝነት ተላቆ በአለም አቀፉ የኢኮኖሚ ትስስር ውስጥ በአምራችነት ለመሰለፍ ከመጣጣር ውጭ በአገራችን ፈጣን ልማት ከቶ እውን ሊሆን አይችልም፡፡ በአምራችነት በመሰለፍ ማዕቀፍም በአለም አቀፋዊው ትስስር ያለንን የስራ ድርሻ ደረጃ በደረጃ በማሻሻል ከስር ወደላይ ለመረማመድ ከመጣጣር ውጭ ቀጣይነት ያለው ልማት ሊኖረን አይችልም፡፡ የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታችንም እንዲሁ፡፡

በአገራችን ልማትና ዴሞክራሲን ከሌላው አለም ተነጥለን፣ በተራሮቻችን ዙሪያ መሽገን፣ በሮቻችንን ዘግተን ከቶ ልናረጋግጠው አንችልም፡፡ በሙሉ ልብ አለም አቀፋዊው ትስስር ውስጥ ከመግባት ውጭ አማራጭ የለንም ብለን አምነን፣ በዚሁ ትስስር ውስጥ

ከተስፈኛነትና ተመፅዋችነት ተላቀን ወደአምራችነት፣ በአምራችነት ዙሪያም የስራ ድርሻችንን በቀጣይነት የማሻሻል አላማ ይዘን ከተነሳን ብቻ ነው የአገራዊ ጥቅማችንና ህልውናችን መነሻና መዳረሻ የሆኑትን ልማትና ዴሞክራሲን እውን ማድረግ የምንችለው። ግሎባላይዜሽን የሚፈጥርልንን ዕድል በሙሉ አሟጦ በመጠቀም፣ ግሎባላይዜሽን የሚደቅንብንን እንቅፋት በመቀነስ፣ በግሎባላይዜሽን ማዕቀፍ ውስጥ ንቁ ተዋናይ በመሆን ብቻ ነው ጥቅማችንና ደህንነታችንን ማረጋገጥ የምንችለው። ልማትንና ዴሞክራሲን በግሎባላይዜሽን ማዕቀፍ እውን ማድረግ፣ የውጭ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲያችን አንድ መሰረታዊ መነሻ መሆን ያለበትም በዚሁ ምክንያት ነው። ግሎባላይዜሽን ከዚህ አኳያ የሚፈጥርልንን ዕድል አሟጦ የሚጠቀም፣ ዕንቅፋቶቹን የሚቀንስ የውጭ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲ ጠቃሚና ትክክለኛ ነው። ይህንን ለማድረግ የማያስችል ፖሊሲ ምንም ያህል ቢራቀቅና ባሸበረቀ ቃላት ቢገለፅ በመሰረቱ ስህተትና ጎጂ ከመሆን ሊያልፍ አይችልም።

ግሎባላይዜሽን በአገሮች መካከል የጥቅም ግጭትን አላስቀረም፣ ሊያስቀርም አይችልም። ግሎባላይዘሽን በአገሮች መካከል እኩልነትን አላሰፈነም፣ የእኩልነት መደፈቅን መቀነስ አይቻልም ባይባልም ግሎባላይዜሽን እኩልነትን ያሰፍናል ብሎ ማሰብ አይቻልም። ይህ ከግሎባላይዜሽኑ ባህሪ የሚመነጭ እውነታ፣ ነባራዊ እውነታ ነው። የልማትና የዴሞክራሲ አላማችንን በግሎባላይዜሽን ማዕቀፍና በዚሁ ማዕቀፍ ብቻ ለመፈፀም መነሳት፣ የግሎባላይዜሽንን ፍትሃዊነት የመቀበል ወይ ያለመቀበል ጉዳይ



አይደለም። ግሎባላይዜሽን እስከነችግሮቹ የአለማችን ነባራዊ ሁኔታ መሆኑን፣ ችግሮቹን ለመቀነስ እየተጣጣሩ በዚሁ ማዕቀፍ ውስጥ አገራዊ ጥቅምንና ደህንነትን ለማረጋገጥ ከመጣጣር ውጭ ሌላ አማራጭ እንደሌለ በሚገባ የመገንዘብና ነባራዊ ሁኔታን የመቀበል፣ የመዋጥ ጉዳይ ነው።

ግሎባላይዜሽን ፍትሃዊም ባይሆኑ የሚመራባቸው ህጎችና ስርአቶች አሉት። አለም አቀፍ ህግ አለ። በአገሮች መካከል የሚኖረውን የኢኮኖሚና ሌሎች ግንኙነቶች የሚገዙ አለም አቀፍ ስምምነቶችና ተቋሞችም አሉ። እነዚህ ህጎችና አለም አቀፋዊው ስርአት በመሰረቱ በአገሮች መካከል በሚደረጉ ድርድሮች የተፈጠሩ ናቸው። ሰጥቶ በመቀበል፣ ጥቅሞችን በማቻቻል ላይ የተመሰረቱ ናቸው። የተሻለ አቅምና ጉልበት ያላቸው አገሮች በዚሁ ድርድር ወሳኝ ሚና ስላላቸው ስርአቱ በወሳኝነት ጥቅማቸውን የሚያስጠብቅ ይሆናል። ደከም ያሉ አገሮች በዚሁ ነባራዊ ሁኔታ ክልል ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ ተደራድረው የስምምነቶቹን ባህሪ ባይወስኑም ስምምነቶቹ ሊያስከትሉባቸው የሚችሉ ጉዳቶችን መቀነስ ይችላሉ። በግሎባላይዜሽን ማዕቀፍ ልማትንና ዴሞክራሲን እውን ለማድረግ መጣጣር ማለት ከላይ በተጠቀሰው ሁኔታ ውስጥ ጥቅምን ለማስጠበቅ መጣጣር ማለት ነው።

እንደኛ ያሉ አገሮች አቅማቸውና ጉልበታቸው ውሱን በመሆኑ የስርአቱን መሰረታዊ ባህሪ መወሰን ባይችሉም በዚሁ ክልል ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ መጣጣር ይኖርባቸዋል። በአንድ በኩል በድርድርና ሰጥቶ በመቀበል መርህ ስምምነቶቹ በነሱ ላይ

የሚያስከትሉትን ጉዳት ለመቀነስና የሚያስገኙትን ጥቅም ለማሻሻል በጋራና በተናጠል መጣጣር ይኖርባቸዋል፡ በሌላ በኩል ደግሞ ምንም ያህል ፍትሃዊነት የጎደለው ቢሆንም ለደካማ አገሮች በህግና በስርአት የሚመራ ግሎባላይዜሽን ጉልበተኛው ምንም ገደብ ሳይኖርበት እንደፈለገ ከሚሆንበት ግሎባላይዜሽን ይሻላልና ህግና ስምምነቶችን እስካልተቀየሩ ድረስ በጥብቅ በማክበር መርህ ላይ ተመስርተው መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል።

በግሎባላይዜሽን ማዕቀፍ ውስጥ አገራዊ ጥቅማችንና ደህንነታችንን ለማስጠበቅ የሚያስችል የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲ መቅረፅ አለብን ሲባል በድንበራችን ታጥረን ሳይሆን አለም አቀፋዊውን ትስስር ጠበቅ አድርገን ይዘንና አቅፈን የምንሰራበትን አቅጣጫ የሚያሳየን ፖሊሲ መሆን አለበት ማለት ነው። ከዚያም አልፎ ጠቅሞ በመጠቀም፣ ሰጥቶ በመቀበል፣ በድርድርና በመቻቻል ላይ የተመሰረተ እንጅ በተናጠል ጥቅምን ለማስጠበቅ በመሞከር የሚፈፀም ፖሊሲ መሆን የለበትም ማለት ነው። በአንድ በኩል የግሎባላይዜሽን ህግና ስርአትን ጥቅማችንን በሚያስጠብቅ አኳኋን ለማሻሻል በጋራና በተናጠል መደራደር፣ በሌላ በኩልና በዋነኛነት ደግሞ ይኸው ህግና ስርአት በጥብቅ ተግባራዊ እንዲሆንና ከዚሁ የሚያገኘውን ጥቅም አሟጦ ለመጠቀም የሚያስችል ፖሊሲ መሆን አለበት ማለት ነው።

በግሎባላይዜሽን ማዕቀፍ ውስጥ አገራዊ ጥቅማችንና ደህንነታችን ለማስጠበቅ መስራት ማለት ሁሉንም ነገር በተናጠል መስራት ማለት እንዳልሆነ ግልፅ ነው። ለምሳሌ የግሎባላይዘሽንን



ህግና ስርአት ለማሻሻል የሚደረገው ድርድርና ጥረት ያልበለፀጉ አገሮች የጋራ ጥረትን የሚጠይቅ ይሆናል። ከግሎባላይዜሽን የሚገኘውን ጥቅም አሟጦ ለመጠቀም ከተለያዩ ሃይሎች ጋር በጋራና በቅንጅት መስራትን ይጠይቃል። እዚህ ላይ ሊሰመርበት የሚገባው ጉዳይ ከማንም ጋር በጋራና በቅንጅት ስንሰራ መነሻችን አንድና አንድ ብቻ ይኸውም ብሄራዊ ጥቅማችንና ደህንነታችን ማስከበር መሆኑ ነው። ይህንን ለማድረግ እስካስቻለን ድረስ ብቻ በጋራና በቅንጅት እንሰራለን። ከዚህ ውጭ የምንመራበት አላማም የለንም፣ ከዚህ ውጭ የምናስቀምጠው ግብም የለንም። የውጭ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲያችን ሶስተኛ መነሻ በግሎባላይዜሽን ማዕቀፍ አገራዊ ጥቅማችንና ደህንነታችንን ማስከበር ነው ሲባልም ይኸው ነው።

በማጠቃለል የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ መነሻዎቻችን ብሄራዊ ጥቅማችንና ደህንነታችንን ማስጠበቅን ማዕከል ያደረጉ እንደሆኑ፣ ብሄራዊ ጥቅምና ደህንነት ሲባል የምልአተ ህዝቡ ጥቅምና ህልውና መሆኑ፣ ይህም ልማትንና ዴሞክራሲን እውን በማድረግ እንደሚገለፅ ማስቀመጥ ይቻላል። የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲያችን መነሻና መዳረሻ ልማትና ዴሞክራሲን እውን ማድረግ ሲባል ይህንኑ በግሎባላይዜሽን ማዕቀፍ ውስጥ ማስፈፀም ማለት በመሆኑ ግሎባላይዜሽንም አንዱ የፖሊሲ መነሻ መሆኑን ማስቀመጥ ይቻላል። የአገራዊ ውርደታችን ምንጭ የሚደርቀው ሁሉንም ነገር ለልማትና ለዴሞክራሲ ተገዥ በማድረግ በመረባረብ በመሆኑ አገራዊ ክብራችንን የመጠበቅም ጉዳይ ልማትና ዴሞክራሲን እውን ከማድረግ አላማ ጋር አንድና ያው እንደሆነ ማስቀመጥ ይቻላል።

## 2. የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲ ግቦች፣

ደህንነታችን ለከፋ አደጋ የሚጋለጠው፣ ለእልቂትና ብተና የምንዳረገው ልማትና ዴሞክራሲ እውን ሳይሆኑ ሲቀሩ በመሆኑ፣ አገራዊ ውርደት ተሸክመን በተመፅዋችነትና በተስፈኝነት የምንኖረው ዴሞክራሲና ልማት እውን ሳይሆኑ ሲቀሩ በመሆኑ፣ ከውጭ ጉዳይና ከአገራዊ ደህንነትም አኳያ አላማችን ፈጣን፣ ህዝቡ በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበት ልማትና ዴሞክራሲን እውን ማድረግ ይሆናል። ይህንን አላማ እውን በማድረግ ህልውናችንን አረጋግጠን ክብራችንን ማስጠበቅ እንችላለን። በመሆኑም የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲዎቻችን አላማ ልማትንና ዴሞክራሲን እውን ለማድረግ የሚያስችል የተመቻቸ የውጭና የደህንነት ሁኔታ መፍጠር ይሆናል። የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት መነሻም መዳረሻም ልማትና ዴሞክራሲን እውን ማድረግ ይሆናል።

ልማትን እውን ለማድረግ፣ ይህንኑ በግሎባላይዜሽን ማዕቀፍ ለመፈፀም ሰፊ የገበያ ዕድል፣ ኢንቨስትመንትና ቴክኒካዊ ድጋፍ ማግኘት ያስፈልገናል። ቢያንስ እስከተወሰነ ጊዜ ድረስ የልማት ፋይናንስ ጥረታችንን የሚያግዝ የብድርና ርዳታ ድጋፍም ያስፈልገናል። ዴሞክራሲን በአገራችን እውን ለማድረግ የዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ተቋሞችን ለመፍጠርና ለማጠናከር ሰፊ የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ ያስፈልገናል። የውጭ ጉዳይ ፖሊሲያችን ዋነኛ ግብ፣ ዋነኛ ማጠንጠኛም ይህ ይሆናል። ለልማትና ለዴሞክራሲ እውን መሆን የተመቻቸ ሁኔታ መፍጠር በዚህም ክልል የገበያ፣ የኢንቨስትመንት፣ የብድርና ርዳታ፣ የቴክኒክ ድጋፍ ለማግኘትና



ይህንኑ በይበልጥ ጥቅም ላይ ለማዋል መቻል ይሆናል ዋነኛ ግባችን። ዲፕሎማሲያችን በዋናነት የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ መሆን ይኖርበታል።

ዲፕሎማሲያችን የውጭ ፖሊሲያችን ከውጭ አገራዊ ደህንነታችን ሰላማችንን የሚፈታተን ነገር ከተቻለ ለማስወገድ ካልተቻለም የመቀነስ ግብ ሊኖረው ይገባል። ከዚህም አኳያ ሰላማችንና ደህንነታችንን የሚደግፍ አለማዊና ከባቢያዊ ሁኔታ እንዲፈጠር፣ በዚህ ረገድ የሚተባበሩን ወዳጆች እንዲበዙ የማድረግ ግብ አለው። አደጋዎችን አስቀድሞ የመተንበይና በውይይትና በድርድር እንዲፈቱ ወይም እንዲቃለሉ የማድረግ ግብ አለው። መቃለልና መወገድ የማይችሉትን ለመቋቋም የሚረዳን ወዳጅና አጠቃላይ ሁኔታ እንዲኖረን የማድረግም ግብ አለው።

የውጭ ጉዳይ ፖሊሲያችን ለልማታችን የሚሆን ምቹ ሁኔታ ከመፍጠር በተጨማሪ ግሎባላይዜሽን በልማታችን ላይ የሚፈጥረውን እንቅፋት በግልና በጋራ ጥረት የመቀነስና የማቃለል ግብም አለው። ይህም የዲፕሎማሲያችን ማዕከል የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ እንዲሆን የሚያደርግ ተጨማሪ ምክንያት ነው።

የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲያችን ከራሳችን ከውስጣችን የሚመጣውን የእልቂትና የመበታተን አደጋ ለማስወገድ በሚሰራው ስራ ላይ ተመስርቶ ከውጭ በህልውናችን ላይ የሚመጣን አደጋ የመመከትና ለዚሁ አደጋ ተጋላጭነታችንን የመቀነስ ብቃት የመፍጠር ግብም ይኖረዋል።

## 3. የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ስትራተጅዎች፣

የውጭ ጉዳይንና አገራዊ ደህንነትን በተመለከተ የምናስቀምጣቸውን አላማዎችና ግቦች ከዳር ለማድረስ በግልፅ የተቀመጠና ትክክለኛ ስትራተጅ መንደፍ ያስፈልገናል። ይህንኑ መሰረት በማድረግ የሚዘረዘሩ ስልቶችንና ዝርዝር ፖሊሲዎችም ማስቀመጥ ያስፈልገናል። በዚህ ረገድ ልንከተላቸው የሚገቡ ስትራተጅዎች እንደሚከተለው ሊቀመጡ ይችላሉ።

### 3.1. ዋናው ትኩረታችን በአገር ውስጥ የሚሰራው እንዲሆን ማድረግ፣

የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲያችን የልማትና የዴሞክራሲ ራዕያችንን የማሳካት፣ ለዚሁ የተመቻቸ ሁኔታ የመፍጠር አላማ ያለው ነው። የልማት ራዕያችን፣ የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ስራችን የተሳካ ሊሆን የሚችለው የአገራችንን ነባራዊ ሁኔታ በጥሞና መርምረን፣ በግሎባላይዜሽን ማዕቀፍ ውስጥ አላማችንን እንዴት ማሳካት እንደምንችል በትክክል አስቀምጠን መረባረብ ከቻልን ብቻ ነው። ልማትንና ዴሞክራሲን እውን ለማድረግ ምን እንዴት መቼ እንደምንሰራ እኛው ራሳችን ለይተን ካላስቀመጥን ከውጭ በተቀየሰ አቅጣጫ የተሳካ ስራ መስራት አይቻልም። አቅጣጫችንን እኛው ራሳችን ቀይሰን በጉዳዩ ላይ አንድ የጋራ አመለካከትና እምነት ይዘን እንደህዝብ ለተግባራዊነቱ የተረባረብን እንደሆነ ብቻ ነው የተሳካ ስራ መስራት የምንችለው።



የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲያችን ለልማትና ዴሞክራሲ ራዕያችን መሳካት የተመቻቸ ሁኔታ ሊፈጥር የሚችለው በርግጥም ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ትክክለኛ የልማትና የዴሞክራሲ ጎዳና ተቀይሶ መላው ህዝብ ተረባርቦ የሚያስፈፅመውና ሊያስፈፅመው የሚችል ሲሆን ነው። ዳገት የማይወጣ ራዕይ ተይዞ፣ ህዝቡ ከዳር ሆኖ ተመልካች በሆነበት ሁኔታ ምንም አይነት የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲ ቢቀየስ ለማይሰራ አላማ የተመቻቸ ሁኔታ ከመፍጠር የሚያልፍ ውጤት ሊኖረው አይችልም። ለማይሰራ ነገር የተመቻቸ ሁኔታ ከመፍጠር የሚገኝ ፋይዳ ሊኖር አይችልም። ስለሆነም የተሳካ የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ስራ ለመስራት ዋናው ትኩረት በአገር ወስጥ የልማትና የዴሞክራሲ ራዕያችንን እውን ለማድረግ የሚያስችል የተሟላ ስራ መስራት፣ በአገር ውስጥ በሚካሄድ ርብርብ ላይ ማተኮር ያስፈልጋል። ይህ ስራ ሳይሰራ በውጭ በሚካሄድ ስራ ላይ መንደፋደፍ ከንቱ ድካም ከመሆን አያልፍም።

እኛው ራሳችን የልማትና የዴሞክራሲ አቅጣጫችንን ቀይሰን፣ መላውን ህዝብና ያለንን ሃብትና ንብረት ሁሉ በዚህ አላማ ላይ ማረባረብ ስንጀምር የሚጎድለንንና ከውጭ ቢጨመርልን ስራችንን የሚያፋጥንልን ነገር ምን እንደሆነ ለይተን ማወቅ እንችላለን። ከውጭ የሚመቻችልንን ነገር እንዴት ብንጠቀምበት የተሻለ ውጤት ሊያስገኝ እንደሚያስችል በትክክል ማስቀመጥ እንችላለን። የውጭውን የጎደለውን ለመሙላት ብቻ ልንጠቀምበት ስለሚገባ የራሳችንን የቤት ስራ ስንሰራ ምን እንደጎደለ፣ ምን

እንደሚያስፈልግ፣ እንዴት ጥቅም ላይ ሊውል እንደሚችል ለይተን ከውጭ የሚፈጠርልንን የተመቻቸ ሁኔታ በላቀ አኳኋን አሟጠን ልንጠቀምበት እንችላለን። የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነትም ለልማታችንና ለዴሞክራሲ የተመቻቸ የውጭ ሁኔታ መፍጠር አለበት ሲባል በተጨባጭ ምን እንደጎደለ፣ ምን ሊሟላ እንደሚችልና፣ እንዴትስ ጥቅም ላይ ሊውል እንደሚችል በውል የተገነዘበና ውጤታማ ለመሆን የሚችልም ይሆናል። ይህ ባልሆነበት ሁኔታ የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲ ከውጭ የሚገኘውን ምፅዋት ይጠቀምም አይጠቀምም ለማግበስበስ ከመሞከር የተሻለ ስራ ለመስራት የሚያስችል አይሆንም። ስለሆነም ትኩረታችን የራሳችንን የቤት ስራ በትክክል በመስራት ላይ መሆን ይኖርበታል።

የውጭው ሁኔታ ለልማታችንና ለዴሞክራሲ የተመቻቸ እንዲሆን ለማደረግ የሚካሄደው ርብርብ ውጤታማ ሊሆን የሚችለው እኛው ራሳችን ልማትንና ዴሞክራሲን እውን ለማድረግ የሚያስችል የተሳካ ርብርብ ያካሄድን እንደሆነ ብቻ ነው። የተሳካ የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ስራ ስንሰራ የውጭው ህብረተሰብ ከዚሁ ተጠቃሚ እሆናለሁ ብሎ የተመቻቸ ሁኔታ ሊፈጥርልን ይችላል፣ የውጭው ርዳታ ከንቱ ሆኖ እንደማይቀር ተገንዝቦ ርዳታውን ሊያጠናክር ይችላል፣ በውስጣችን ልማትንና ዴሞክራሲን እውን ለማድረግ የሚካሄደው ርብርብ የተልፈሰፈሰ እንደሆነ ግን ከኛ የተሳካ ስራ እጠቀማለሁ ብሎ የሚያስብ አይኖርም፣ የማበርከተው ርዳታ ውጤታማ እየሆነ ነው ብሎ ርዳታውን ለማጠናከር የሚነሳሳም አይኖርም። ስለሆነም የውጭው



ሁኔታ ለልማታችንና ለዴሞክራሲያችን የተመቻቸ እንዲሆን ከማድረግ አኳያም ወሳኙ ነገር በአገር ውስጥ የምናካሄደው ጥረት ነው።

በማጠቃለል፣ የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት አላማ የሆነው ልማትንና ዴሞክራሲን እውን የማድረግ ስራ የሚሳካው በዋነኛነት በራሳችን ጥረትና ርብርብ በመሆኑ፣ ከውጭ የሚያስፈልገንንና የጎደለንን ነገር በትክክል ለይተን አላማችንን ለማሳካት በሚያስችል አኳኋን ጥቅም ላይ ልናውለው የምንችለው በራሳችን ጥረት መሄድ የምንችለውን ርቀት ስንጓዝ ብቻ በመሆኑ፣ የውጭው ህብረተሰብ ለአላማችን የተመቻቸ ሁኔታ ለመፍጠር የሚደፋፈረው አላማችን እንደሚሳካ በተግባር ማሳየት ስንችል በመሆኑ የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲያችን የሚሳካው በዋነኛነት በአገር ውስጥ በሚደረግ ጥረት ነው። ዋናው ትኩረታችንም በዚህ ላይ መሆን አለበት። አካሄዳችን ከውጭ ወደ ውስጥ ሳይሆን ከውስጥ ወደ ውጭ መሆን አለበት።

አካሄዳችን ከውጭ ወደ ውስጥ ከሆነ የመጀመሪያው ጥያቄያችን ማን? ምን ብናደርግ? ምን አይነት የተመቻቸ ሁኔታን ይፈጥርልናል? የሚለው ይሆናል። አካሄዳችን ሁሉ ከውጭ ድጋፍ በማግኘት ላይ የተመሰረተ፣ ፖሊሲያችንም ይህንኑ አላማ ለማሳካት ተብሎ የተቃኘ ይሆናል። በዚህ መልክ አጥጋቢ ድጋፍ ለማግኘትም የሚቻል አይሆንም፣ የሚገኘውም የውጭውን ህብረተሰብ ፍላጎት በማሳካት ላይ የሚውል ስለሚሆን በምንም አይነት ሁኔታ አገራዊ ጥቅማችንና ህልውናችንን ሊያረጋግጥ አይችልም። አካሄዳችን

ከውስጥ ወደ ውጭ ከሆነ ግን በመጀመሪያ እኛው ራሳችን የራሳችንን የቤት ስራ እንሰራለን፣ የሚጎድለንን ለይተን እናስቀምጣለን፣ የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲያችን ይህንን ክፍተት የመሙላት አላማን ይዞ፣ የራሳችን የተሳካ የቤት ስራ የሚፈጥርለትን ዕድል ተጠቅሞ የሚቀየስና ተግባራዊ የሚሆን ይሆናል፡፡ መነሻው የራሳችንን አላማና ራዕይ ማሳካት ስለሚሆን ውጤታማ ሊሆን ይችላል፡፡

ስለሆነም የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ግቦቻችንን ለማሳካት የምንከተለው አንድ መሰረታዊ ስትራተጅ ከውጭ ወደውስጥ ሳይሆን ከውስጥ ወደውጭ የሚወረወር ስትራተጅ ነው፡፡ ዋናው ጉዳይና ትኩረት በአገር ውስጥ የሚሰራው ስራ መሆኑን የተገነዘበ፣ በአገር ውስጥ በሚደረገው ርብርብና በዚሁ ርብርብ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ፣ ይኸው ርብርብ የሚፈጥርለትን ዕድል የሚጠቀም ስትራተጅ ነው፡፡

## 3.2. ኢኮኖሚን ማዕከል ያደረገ ስትራተጅ፣

የውጭ ጉዳይም ሆነ የደህንነት ፖሊሲያችን ማጠንጠኛ ፈጣን ህዝቡ በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበት ልማት ማረጋገጥና ለዚሁ የተመቻቸ ሁኔታን መፍጠር ነው፡፡ በተደጋጋሚ እንደተገለፀው አገራዊ ጥቅማችንም ሆነ ህልውናችን የሚረጋገጠው ህዝቡ በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበት ፈጣን ልማት ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡ ዋናው የደህንነታችን ስጋት የውስጥ ስጋት ነው፡፡ ድህነት ተስፋፍቶ እንዳንበታተንና እንዳንተላለቅ፣ ዴሞክራሲና



መልካም አስተዳደር ጠፍቶ ለእልቂት እንዳንዳረግ ነው፡፡ ይህንን ዋነኛ ስጋት ማስወገድ የሚቻለው ድህነትን በማስወገድ፣ በኢኮኖሚያዊ ርብርብና ልማት ነው፡፡ ከውጭ የሚመጣ የደህንነት ስጋትንም በብቃት ለመቋቋም የምንችለው ጠንካራ ኢኮኖሚ ሲኖረን ብቻ ነው፡፡ ኢኮኖሚያችን በትንሽ የነፋስ ሽውታ ተንገራግጮ የሚቆም መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ ስለሆነም ለብሄራዊ ጥቅሙም ለደህንነቱም ወሳኙ ጉዳይ ፈጣን ልማት ነው፡፡ ብሄራዊ ጥቅማችንና አገራዊ ደህንነትና ህልውናችንን ለማረጋገጥ የተመቻቸ ሁኔታ እንዲፈጥር ተብሎ የሚቀየስ ፖሊሲ ማዕከሉን ኢኮኖሚ ማድረግ አለበት የምንለውም ለዚሁ ነው፡፡

ኢኮኖሚን ማዕከል ያደረገ ስትራተጅ ልንከተል ይገባናል ስንል በመጀመሪያ ደረጃ ከአገሮች ጋር ለሚኖረን ወዳጅነትም ሆነ ጠላትነት ዋነኛ መነሻው ይኸው መሆን አለበት ማለት ነው፡፡ ለልማታችን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ፋይዳ በሌለው ጉዳይ ላይ የሚመሰረት ወዳጅነትም ሆነ ጠላትነት ሊኖረን አይገባም ማለት ነው፡፡ በተጨማሪ በውጭ የምናደርገው እንቅስቃሴ ሁሉ የንግድ ዕድልን፣ የኢንቨስትመንት ዕድልን፣ የብድርና ርዳታ ምንጭም በማፈላለግ ላይ ያተኮረ መሆን አለበት ማለት ነው፡፡ የውጭ ፖሊሲያችንን በማስፈፀም ረገድ የሚሰማሩት ሁሉ ከሁሉም በፊትና ከሁሉም ነገር በላይ የኢኮኖሚ ልማታችን መልዕክተኞች መሆናቸውን እንዲገነዘቡ፣ ይህንኑ ስራ በሚገባ ለመፈፀም የሚያስችላቸው አቅም እንዲኖራቸው ማድረግ ማለት ነው፡፡ የኢኮ ኖሚ ልማት ስራው በውጭ ፖሊሲ አፈፃፀም እንቅስቃሴያችን ከሌ ሎች ስራዎች ጋር ተዳምሮ የሚታይ ተደራቢ ስራ ሳይሆን

የውጭ ሰራችን ዋነኛ ክፍልና ማጠንጠኛው እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡

ከደህንነትም አንፃር የስትራተጅያችን ማዕከል ኢኮኖሚው መሆን አለበት ሲባል የውስጡንም ሆነ የውጭው የደህንነት ስጋታችንን በብቃት ለመመከት የምንችለው ፈጣን የኢኮኖሚ ልማት በማረጋገጥ መሆኑን ተገንዝበን፣ ይህንን እድገት የሚያጓትት ነገር በሙሉ የዋነኛ የደህንነት ስጋት ምንጭ እንደሆነ አስምረንበት ልማትን እንደዋነኛ የደህንነት መሳሪያ ወስደን ደህንነታችንን ለማረጋገጥ ሲባል በፈጣን ልማት ላይ መረባረብና ይህንን ሊያደናቅፉ የሚችሉ ነገሮችን በሙሉ ማስወገድ ማለት ነው፡፡ በተጨማሪም የኢኮኖሚ ልማታችንን ክፉኛ የሚያደናቅፍና አንቆ የሚይዝ ካልሆነ በስተቀር ከዚህ ውጭ የሆነ ነገርን ሁሉ ከማዘናግያነት እንደማያልፍ ወስደን ወደጎን ማለት፣ በመቻቻል መፍታት አለብን ማለት ነው፡፡ ኢኮኖሚያችንን አንቆ የሚይዝ ስለሆነም በርግጥም ከፍተኛ የደህንነት ስጋት የሆነውን ጉዳይም ቢሆን በኢኮኖሚያዊ ልማታችን ላይ ከፍተኛ ጉዳት በማያስከትል አኳኋን በዲፕሎማሲ፣ በድርድር በፖለቲካዊ ተፅእኖ ወዘተ. ለመፍታት መጣጣር አለብን ማለት ነው፡፡ ከዚያ አልፈን ለመከላከል ልንገደድ ስለምንችል የመከላከል አቅማችንን በተቻለ መጠን በኢኮኖሚያችን ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ በሚያሳርፍ አኳኋን መገንባት አለብን ማለት ነው፡፡

## 3.3. በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ ጥቅሞችን አሟጦ መጠቀም፣



ከውጭ ጉዳይ እንቅስቃሴያችን ብሄራዊ ጥቅማችንንና አገራዊ ደህንነታችንን ለማስጠበቅ የምንፈልጋቸው ነገሮች ምን እንደሆኑ ቀደም ሲል ተጠቅሷል፡፡ ከሁሉም በላይ የምንፈልገው ጥቅም ኢኮኖሚያዊ ነው፡፡ ለልማት የሚያስፈልገን የገበያ ዕድል፣ ኢንቨስትመንትና ፋይናንስ፣ ለልማታችንና ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ የሚያስፈልገን የቴክኒክ ድጋፍ ከሁሉም ቅድሚያ የሚሰጣቸው ነገሮች ናቸው፡፡ ከዚያ ቀጥሎ ደህንነታችንን ለማስከበር የሚያስፈልገን ፖለቲካዊ፣ ዲፕሎማሲያዊ፣ ወታደራዊና ቴክኒካዊ ድጋፍና ትብብር እንፈልጋለን፡፡ እነዚህን ርዳታዎችና ትብብሮች ማግኘት በምንችለው የላቀ ደረጃ አግኝተን በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ ይኖርብናል፡፡

ሊገኙ የሚችሉ ትብብሮች ምን እንደሆኑና እንዴት ሊገኙ እንደሚችሉ በተሟላ ሁኔታ ሊታወቅ የሚችለው በዝርዝርና በተሟላ ጥናት አማካኝነት ነው፡፡ ከየትኛው አገር ምን አይነት ትብብርና ድጋፍ እንደሚገኝ ለማወቅ የእያንዳንዱን አገር ፖሊሲና ሁኔታ በዝርዝር ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ልናገኝ የምንችለውን ትብብር በሙሉ አሟጠን መውሰድ ያለብን ቢሆንም በቅደም ተከተል መስራት ያስፈልጋል፡፡ ለልማታችንና ለዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ የላቀ አስተዋፅኦ ያላቸው ትብብሮችን ማድረግ የሚችሉትን መለስተኛ ትብብር ከሚያደርጉት መለየት ያስፈልጋል፡፡ ይህንን ማድረግ የሚቻለው ዝርዝርና የተሟላ ጥናት በማካሄድ ነው፡፡ ከማን ምን አይነት ትብብር ማግኘት እንደሚቻል ታውቆ ቅደም ተከተል ከወጣ በኋላም ትብብሩን ለማግኘት ውጤታማ እንቅስቃሴ ማካሄድ ያስፈልጋል፡፡ ይህ እንቅስቃሴ በበቂ ጥናት ላይ በተመሰረተ

እቅድ ካልተፈፀመ በደመ-ነብስ የሚደረግ መፍጨርጨር ትብብሮችን በወቅቱና በተሟላ ሁኔታ ለመጠቀም የሚያስችል አይሆንም። ስለሆነም እንቅስቃሴው ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ዝርዝርና በቂ ጥናትን የሚጠይቅ፣ ይህንኑ የማከናወን ብቃትን የሚሻ ስራ እንደሆነ ሊሰመርበት ይገባል።

ከላይ የተጠቀሱት ጥናቶች ራሳቸው በሌላ ጥናት ላይ የሚመሰረቱ ናቸው። ከውጭ ምን አይነት ትብብር ያስፈልገናል የሚለው ቀዳሚ ጥያቄ ራሱ እኛው በራሳችን ጥረት የምንሰራውን ስራ እየሰራን የሚጎድለንና ከውጭ ልናገኝ የምንችለውን መለየት ይጠይቀናል። ከውጭ የምናገኘውን ማሟያ በእንዴት አኳኋን ብንጠቀምበት የበለጠ ውጤት እንደሚሰጥም አስቀድሞ መለየት ያስፈልጋል። እነዚህ ሁሉ የተሟሉ ጥናቶችን የሚጠይቁ ናቸው። በዚህ ደረጃ የሚከናወነው ጥናት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ አካል አይደለም ቢባልም የውጭው ስራ በዚሁ ጥናት ላይ መመስረቱ ስለማይቀር በሁለቱ መካከል ጥብቅ ትስስርና ቅንጅት መጠየቁ አይቀርም።

በመሆኑም የምንከተለው ስትራተጅ በግምት ወይም ጥልቀትና ዝርዝርነት በሚጎድለው ዝግጅት ላይ ሳይሆን ከላይ በተጠቀሰው አኳኋን በዝርዝርና ትክክለኛ ጥናት ላይ መመስረት ይኖርበታል። ውጤታማ የስራ አፈፃፀም በዝርዝርና ትክክለኛ ጥናት ላይ የተመሰረተ መሆኑን በሚገባ የተገነዘበ በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ ጥቅሞችን አሟጦ ለመጠቀም የሚያስችል ስትራተጅ ልንከተል ይገባል።



ጥቅሞችን አሟጦ ከመጠቀም አኳያ ሌላው ሊተኮርበት የሚገባው ጉዳይ የቅደም-ተከተል ጉዳይ ነው። ያገኘናት ትብብር ትንሽም ብትሆን ከማንኛውም ወገን ትምጣ ሳንንቅ ማሰባሰብና መጠቀም እንዳለብን ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው። ትንሽ ነች ብለን የምናልፋት ምንም ነገር አትኖርም፣ መኖርም የለባትም። ይሁንና ትብብሩን ለማስፈፀም ጊዜ፣ ገንዘብና የሰው ሃይል መጠየቁ አይቀርም። ሁሉንም የትብብር እድሎች በእኩልነት ለማስተናገድ የሚያስችል አቅም አይኖረንም። ቅደም ተከተል አውጥተን በቅደም ተከተሉ መሰረት መስራት ይኖርብናል። የላቀ ተፈላጊነት ላለው ትብብር የላቀ ትኩረት የሚሰጥ ነገር ግን ምንም ነገር ንቆ የማይተው አካሄድ መከተል አለብን። ጥቅሞችን አሟጦ የመጠቀም ስራ እውን ሊሆን የሚችለው በዚህ መልኩ ብቻ ነው።

## 3.4. በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ አደጋዎችን መቀነስ፣

ለልማታችንና ለዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ የተመቻቸ ሁኔታን መፍጠር ሲባል አንዱና ዋናው ገፅታ ለዚሁ አላማ የሚጠቅሙ ትብብሮችን ማፈላለግ፣ ማሰባሰብና ጥቅም ላይ እንዲውሉ የማድረግ ጉዳይ ነው። ጥቅሞችን አሟጦ የመጠቀም ጉዳይ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ጉዳቶችን የመከላከልና የመቀነስ ጉዳይም አብሮ ሊታይ የሚገባው ጉዳይ ነው። በብሄራዊ ጥቅማችንና በደህንነታችን የሚቃጡ አደጋዎችን መቀነስ የሚያስችል ስትራተጅ ያስፈልገናል።

አደጋዎችን ለመቀነስ መጀመሪያ የአደጋ ምንጭ

የሚሆኑትን ነገሮች መለየት ይገባል፡፡ ዋናው መፍትሄያችን ልማትና ዴሞክራሲ በመሆኑ አደጋ ብለን የምንለው ይህንን አላማ የሚያሰናክልብን ነገር ነው፡፡ ስለሆነም አደጋ ከየት ሊመጣብን ይችላል የሚለውን ጥያቄ በጥናት ለመመለስ መነሻችን በዋነኛነት የኛ ልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ስራ መሳካት ጥቅማቸውን ሊነካባቸው የሚችሉ ወገኖች እነማን ናቸው ብሎ የማጥናት ጉዳይ ነው፡፡ ጥቅማቸው በርግጥም የማይነካ ሆኖ ሳለ ግን የሚነካባቸው መስሎ የሚሰማቸው ወገኖችም ይኖራሉ፡፡ እነዚህንም ደርቦ ማጥናት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም አደጋዎችን ለመቀነስ የምንከተለው ስትራተጅ በመጀመሪያ በልማታችንና በዴሞክራሲያችን የሚጎዱ ወይም የተጎዱ መስሎ ሊሰማቸው የሚችል ወገኖች እናማን ናቸው ብሎ የማጥናትና ይህንኑ በየጊዜው መከለስና ማዳበርን መሰረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡

በኛ ልማትና ዴሞክራሲ ጥቅማቸው የሚነካ ወይም የሚነካ መስሎ የሚታያቸው ወገኖችን መለየት የመጀመሪያው ርምጃ ቢሆንም፣ ይህ ብቻውን የትም ሊያደርሰን አይችልም፡፡ ጥቅማቸው የማይነካ ሆኖ ሳለ ጥቅማቸው የሚነካ የሚመስላቸው ወገኖች ይህንን የሚሉበት ምክንያት ምን እንደሆነ በዝርዝር ለይቶ ማጥናት ያስፈልጋል፡፡ ጥቅማቸው የሚነካባቸውም ወገኖች ጥቅማቸው በምን ደረጃ እንደሚነካና እንደሚጠበቅ፣ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ ምን ማድረግ እንደሚያስቡ፣ ምንስ ለማድረግ ችሎታ እንዳላቸው ወዘተ… በዝርዝር ማጥናት ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ላይ ተመስርቶ በስህተት ጥቅማቸው የሚነካ የሚመስላቸውን ለማስረዳት፣ ጥቅማቸው የሚነካባቸውን ጥቅሞችን ለማቻቻል ምን ሊደረግ



እንደሚችል፣ ከዚህ አኳያ ማን ምን ሊያግዝ እንደሚችል ማጥናት ያስፈልጋል፡፡ ጉዳዮቹን በሰላምና በመቻቻል ለማለፍ የሚደረገው ጥረት ካልተሳካ የሚከተለው ችግር ምን እንደሆነና ይህንኑ ለመቋቋም ምን አይነት ዝግጅት ማድረግ እንደሚያስፈልግም ማጥናትና መለየት ያስፈልጋል፡፡

በመሆኑም አደጋዎችንና ስጋቶችን ለመቀነስ የሚቀየሰው ስትራተጅም የመጀመሪያውና ቁልፉ ርምጃ ከላይ በተጠቀሱትና በመሳሰሉት ላይ ዝርዝርና ትክክለኛ ጥናት ማካሄድ ይሆናል፡፡ በጥናት ላይ ተመስርቶ የሚከናወን ስጋቶችን የመቀነስ ስራ የተሳካ የመሆን ዕድሉ የሰፋ ይሆናል፡፡ ይሁንና ብቃት ባለው ጥናት ላይ የተመሰረተ ዕቅድ ተዐይዞም አፈፃፀም ላይ ችግር ካጋጠመ ውጤቱ ያማረ ላይሆን ይችላል፡፡

በዚህ መሰረት በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ አደጋዎችን የመቀነስ ስትራተጅያችን ጥናቶቹን በሰከነ አእምሮ መመርመርና መጠቀምን የሚያካትት መሆን አለበት፡፡ ጥናቶቹን በሰከነ አእምሮ ከመመርመር አኳያ ወሳኙ ጉዳይ አይናችንን ከዋናው አላማችን ለአንድ አፍታም ቢሆን ያለመንቀል ጉዳይ ነው፡፡ አላማችን ልማትና ዴሞክራሲን እውን ማድረግ ነው፡፡ ይህንን የሚያደናቅፍ ማንኛውንም ነገር መቀበል የለብንም፡፡ ስለሆነም በጥናቱ ላይ ተመስርተን በመግባባት፣ ነገሮችን በማስረዳትና በትእግስት ሊወገዱ የሚችሉትን በዚሁ አኳኋን የምንፈታበትና በእብሪት ተወጣጥረን መሰረታዊ ጥቅማችንን የሚነካ ስራ ላለመስራት መጠንቀቅን ያካተተ መሆን አለበት፡፡ በግሎባላይዜሽን ማዕቀፍ

መስራት ማለት መደራደር፣ ሰጥቶ መቀበልን መልመድ ማለት መሆኑን የተገነዘበ፣ ነገሮችን በድርድርና ጥቅሞችን በማቻቻል ለመፍታት ከምንም ነገር በላይ ቅድሚያ የሚሰጥ አፈፃፀም እንዲኖር ማድረግ ማለት ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ነገሮችን በዚህ መልኩ ለማቃለል ሊረዱ የሚችሉ ወገኖችን በሙሉ ለዚሁ አላማ ለማሰለፍ መቻልን የሚጨምር መሆን አለበት፡፡ በመጨረሻም ከዚህ ሁሉ አልፎ ልማታችንና ዴሞክራሲን አንቆ የሚይዝ አደጋ የሚመጣ ከሆነ፣ ሲሆን እንደማያዋጣው ተገንዝቦ ካልሆነ እርምጃው እንዲቆጠብ ለመግታት፣ ካልሆነም በዋናው አላማችን ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሳናስከትል ሊመከት የሚችልበትን የተቀናጀ የውስጥና የውጭ ዝግጅት ማድረግን የሚጨምር መሆን አለበት፡፡

በመሆኑም የውጭ ጉዳይና የደህንነት ግቦቻችንን ለማሳካት የምንጠቀምበት አንድ ስትራቴጅ በተሟላ ብቃት ላይ የተመሰረተ፣ አደጋዎችና ስጋቶችን ለመቀነስ የሚያስችል ትክክለኛ አፈፃፀምን ያካተተ ስትራቴጅ መከተል ይሆናል፡፡

## 3.5. ለአደጋ ተጋላጭነትን መቀነስ፣

ለአገራዊ ጥቅማችንና ህልውናችን ዋነኛው አደጋ ድህነታችን፣ ኋላ ቀርነታችንና የዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ስርአት ስር አለመስደድ እንደሆነ በተደጋጋሚ ተገልጿል፡፡ አገራዊ ጥቅማችንና ህልውናችንን ለማስጠበቅ በዋነኛነት በአገር ውስጥ በሚካሄድ ርብርብ እነዚህን የስጋት ምንጮች ማድረቅ



እንደሚገባንም ግልፅ ነው፡፡ ከውጭ የሚመጣ አደጋም በዚሁ በዋናው የስጋት ምንጭ ላይ የተመሰረተ መሆኑ አይቀርም፡፡ ከውጭ የሚመጣ አደጋ አንድም ከውስጥ አደጋ ጋር ተሳስሮና ተቀናጅቶ ተፈፃሚ የሚሆን ነው፣ አለያም የውስጥ ድክመትንና ለአደጋ ተጋላጭነትን ታሳቢ በማድረግ የሚፈፀም ነው፡፡ እስከዛሬ ድረስ በአገራችን ላይ የተቃጡ የውጭ አደጋዎችን በምንመረምርበት ወቅት የምናረጋግጠው ጉዳይ ይህንኑ ነው፡፡

በዚህ ረገድ አገራችን ድሃና ኋላ ቀር በመሆንዋ የኢኮኖሚና ሌሎች ተፅእኖዎችን በማሳረፍ ማንበረከክ ይቻላል በሚል ግምት አገሮች ሃይሎች አገራዊ ጥቅማችንና ደህንነታችንን የሚፈታተን ነገር በላያችን ላይ ለመጫን ሊደፋፈሩ ይችላሉ፡፡ ህዝቡ በአንድነት ለጋራ አላማ አይረባረብም፣ እርስ በርሱ በቀላሉ ሊናከስ ይችላል በሚል ግምት በአገራችን ላይ በቀላሉ ተፅእኖ ማሳረፍ ይቻላል በሚል መሰረታዊ ጥቅማችን ላይ ስጋት የሚያሳድር ነገር ለመስራት ሊደፋፈሩ ይችላሉ፡፡ የአገራችን የመከላከልና የደህንነት አቅም በኢኮኖሚው፣ በፖለቲካና በቴክኒካዊ ምክንያቶች ደካማ ነው ብለው ተፅእኗቸውን ለማሳረፍ ሊደፋፈሩ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ግምቶች ሁሉ መሰረተ-ቢስ ናቸው ማለት አይቻልም፡፡ ለአደጋ የሚያጋልጠን ድህነትና ኋላ ቀርነት አለን፡፡ ህዝቡ በመሰረታዊ ጉዳዮች ላይ አንድ ጠንካራና የጋራ አገራዊ እምነትና አመለካከት በተሟላ ሁኔታ አለመያዙም ለአደጋ የሚያጋልጠን ችግር ነው፡፡ በአጭሩ ጠላቶች ይህንን ለጥጠው የሚወስዱበት ሁኔታ ቢኖርም ለአደጋ ተጋላጭ መሆናችን

የሚካድና መካድም ያለበት ጉዳይ አይደለም፡፡

ለአደጋ የሚያጋልጡን ውሱንነቶች መኖራቸው ብሄራዊ ጥቅማችንና ደህንነታችንን በሁለት መልኩ ይፈታተናል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ እነዚህ አደጋዎች እንዳይከሰቱ ከውጭ የሚመነጩ ስጋቶች በእንጭጩ እንዳይቀጩ እንቅፋት ይሆናል፡፡ ስለዚህም ለአደጋው ተጋላጭ ባንሆን ኖሮ ሊኖር ይችል ከነበረው በላይ ለግጭትና ለጦርነት የተጋለጥን እንሆናለን፡፡ በዚህ መሰረት ለምሳሌ ዚያድ ባሬ ኢትዮጵያ በቀላሉ ልትበታተን ትችላለች፣ ለአደጋ የተጋለጠች ነች ብሎ በመገመቱ ሰራዊቱን አሰማራ፡፡ ሻዕቢያም በቅርቡ የውጭ ጥቃት ከፈፀምኩ ተባብሮ የሚመክተኝ አቅም አይኖርም፣ ይበታተናል ብሎ በማሰቡ ጭምር ነው ወረራውን የፈፀመው፡፡ በርግጥ የሁለቱም ግምት የተሳሳተ ስለነበረ ሁለቱም ክፉኛ ተመተዋል፡፡ ይሁንና ይህ እስኪሆን ድረስ በጦርነት ጠምደውናል፣ ከፍተኛ ጉዳትም አድርሰውብናል፡፡ ለአደጋ የተጋለጥን ባንሆን ኑሮ እነዚህ ሃይሎች በኛ ላይ ጦር ከሰበቁ እንደሚጠፉ በቀላሉ በተረዱ ነበር፣ ስለሆነም ለጦርነት ሳንዳረግ አደጋውን በእንጭጩ ለመቅጨት በቻልን ነበር፡፡ ለአደጋ ተጋላጭ (ቫልነረብል) መሆናችን ከመንደር ጎረምሳ ጀምሮ ወደላይ ያሉ ወገኖች ለተፅእኖ አልፎም ለግጭትና ጦርነት ሊዳርጉን ይችላሉ፡፡

ለአደጋ ተጋላጭ (ቫልነረብል) መሆናችን መሆን ይችል ከነበረው በላይ ግጭትና ጦርነት እንዲያጋጥመን ምክንያት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ሌላም ጉዳት አስከትሏል፡፡ ግጭትና ጦርነቱ ከተፈጠረም በኋላ ይህንኑ ለመቋቋም የምንከፍለው ዋጋ እጅግ ከባድ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ እስካሁን ድረስ ህልውናችንን



ለማጥፋት ያስቻለ ጥቃት ባይደርስብንም በድህነት አዘቅት ውስጥ እንድንንፏቀቅ ለማድረግ ግን ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡ ለአደጋ ተጋላጭነታችንን በተቻለ ፍጥነት ካላስወገድንና ካልቀነስን በስተቀር ከውስጥ ለሚመነጭ አደጋ ብቻ ሳይሆን ከውጭ በሚመጣ አደጋም ከላይ በተጠቀሰው አኳኋን መሆን ከሚገባው በላይ ተጠቂ ሆነን መቆየታችን የማይቀር ነው፡፡

የአደጋ ተጋላጭነታችን ዋነኛ ምንጭ ድህነታችንና ኋላ ቀርነታችን ነው፡፡ ለውስጡም ለውጭውም አደጋ በዋነኛነት የሚያጋልጠን ይኸው ነው፡፡ በመሆኑም ከሁሉም ነገር በላይ ይህንኑ በፍጥነት በመቅረፍና በሂደትም ለማስወገድ መስራት አለብን፡፡ ሁሉም ነገር ወደ ፈጣንና ህዝቡ በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበት ልማት ብለን፣ ከዚሁ ውጭ የሆኑ ነገሮችን በሙሉ ለዚሁ አላማ ተገዥ እንዲሆኑ አድርገን መረባረብ አለብን፡፡

ከኢኮኖሚው ቀጥሎ የአደጋ ምንጭ የሚሆነው የዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር እጦት ነው፡፡ አገራችን የብዙ ብሄሮችና እምነቶች አገር መሆንዋን ተገንዝበን በእኩልነትና በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ ጠንካራ ህዝባዊ አንድነት ካልገነባን፣ በዚህ ረገድ ህገ-መንግስቱ በሚያስቀምጣቸው መርሆዎች ዙሪያ ጠንካራ የጋራ አመለካከት ፈጥረን ተግባራዊ ካላደረግን ለውስጥ ብጥብጥና ብተና ብቻ ሳይሆን ለውጭ አደጋና ግጭትም እጅግ የተጋለጥን ሆነን መቆየታችን አይቀርም፡፡ ጠንካራ የዴሞክራሲ ተቋማት ገንብተን በዴሞክራሲ መርሆዎች ዙሪያ አንድ የጋራ አገራዊ እምነት ፈጥረን፣ የህግ ልዕልናን ማስፈንና ከዚህ ውጭ

የሚሆኑ ወገኖችን በህዝቡ ርብርብ በአስተማማኝና ዘላቂ መንገድ በቁጥጥር ስር ማስገባት ካልቻልን መቼም ቢሆን ለውስጥና ለውጭ አደጋ፣ ለአደገኛ ግጭቶችና ጦርነቶች የተጋለጥን መሆናችን አይቀርም።

ያለፉት መንግስታት ቀደምት ትውልዶች ባስገኙት የስራ ውጤት ላይ በተመሰረተ ብሄራዊ ክብር ላይ አተኩረው ሰፊ ቅስቀሳ አካሂደዋል። ይህ ስራ በአሁኑ ትውልድ አስተሳሰብ ላይ የራሱን ተፅእኖ ማሳደሩ አልቀረም። ይህ የራሱ በጎም መጥፎም ገፅታዎች ያሉት ነው። ያለፉት መንግስታት አሁን ያለንበት ሁኔታ ከፍተኛ አገራዊ ውርደት ያከናነበን እንደሆነ ሊገነዘቡም ሆነ በዚህ ላይ በተገቢው ደረጃ ሊያተኩሩ፣ ይህ ውርደት ህዝቡን በየዕለቱ እንደ እሾህ እየወጋው ይህንን ውርደት ለማድረቅ በሚያስችል መንገድ እንዲረባረብ አላደረጉም። ይልቁንም በአገራዊ ክብር ስም ሲደነፉ፣ ሲያቅራሩና በእብሪት ሲወጣጠሩ የሚሸከማቸው አመለካከት እንዲኖር ነው ጥረት ያደረጉት። ይህ ክስተት በሁለት መልኩ ለአደጋ ተጋላጭነታችንን አባብሶታል።

በመጀመሪያ ደረጃ የአገራዊ ውርደታችን ምንጭ ድህነታችንና የመልካም አስተዳደርና የዴሞክራሲ እጦት መሆኑን ተገንዝበን ሁሉም ነገር ለዚሁ አላማ መሳካት ተገዥ አድርገን፣ ይህንን ለማሳካት የሚያስችል መስመር ነድፈን በዚህ ዙሪያ ጠንካራ የጋራ አመለካከት ፈጥረን ለመረባረብና ለአደጋ ተጋላጭነታችንን በመሰረቱ ለማስወገድ እንዳንችል አድርጎናል። ያለፉት መንግስታት



በዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር፣ ህዝቡ በየደረጃው ተጠቃሚ በሚሆንበት ፈጣን ልማት ዙሪያ ህዝቡን ለማሰባሰብ ባህሪያቸው ስለማይፈቅድላቸው ጭምር ነው በባዶ ሆድ ለሚከናወን ድንፋታና ቀረርቶ ሲያጋልጡን፣ ስለሆነም እጅግ የከፋ የአደጋ ተጋላጭነታችን እንዲቀጥል ያደረጉት።

ድንፋታው ቀረርቶው እብሪቱ በሌላ መልኩም ለአደጋ አጋልጦናል። በዋናው ጉዳይ ላይ አተኩረን፣ ሁሉን ነገር ለመሰረታዊ አላማችን መሳካት ተገዥ መሆን እንዳለበት አምነን፣ ይህንኑ የሚያደናቅፉ ነገሮች ሲከሰቱ በድርድር፣ በመቻቻል፣ ሰጥቶ በመቀበል ከመፍታት ይልቅ ወደ ድንፋታ እንድናመራ ስለሆነም ማስወገድ የሚገቡን ግጭቶች ሳይቀሩ እንዲፈጠሩ ወይም የሚያስከትሉት ጉዳት በከፍተኛ ደረጃ እንዲጨምር አድርገዋል። ከላይ ከተጠቀሰው የጃ-ንና የጀርመን ልምድ ተምረን አይናችንን ከዋናው ግባችን ለአንድ አፍታም ቢሆን ሳንነቅል ካልተረባረብን፣ ከድንፋታና ከቀረርቶ ነፃ ወጥተን ነገሮችን በሰከነ አእምሮ እየመዘንን በመሰረታዊ ጥቅማችን ላይ አተኩረን ካልተረባረብን አሁንም ከአደጋ ተጋላጭነት ነፃ የምንወጣበት ሁኔታ አይፈጠርም።

ለአደጋ ተጋላጭ የሚያደርገን ሌላው ጉዳይ ገፍቶ የሚመጣን አደጋ አስቀድሞ ለማወቅና ለመቋቋም የሚያስችል ጠንካራ የደህንነት አቅም፣ በደረጃችን ብቃት ያለው የመከላከል አቅምና ለዚሁ ድጋፍ የሚሆን የውጭ ሁኔታ አለመፍጠራችን ነው። ይህ በወሳኝነት የድህነታችንና የፖለቲካ ችግራችን ውጤት ነው። እነዚህ ሁለት ችግሮች ከተቀረፉ ጠንካራ የመከላከልና

የደህንነት አቅም መፍጠር፣ በኛ ላይ ግጭት ለመቀስቀስ የሚከጅላቸው ወገኖች አንዴም ሁለቴ እንዲያስቡ ለማስገደድ ይቻላል። የዚሁ አቅም መዳከም በሁለተኛ ደረጃ በጥራትና በውጤታማነት ላይ የተመሰረተ ስራ አለመሰራቱን የሚያመለክት ነው። በመጠነኛ ወጭ ሊገነባ የሚችለውን የላቀ አቅም መገንባት ተችሎ ነበር ማለት አይቻልም። ስለሆነም ከዚህም አኳያ ለአደጋ ተጋላጭነታችንን ለመቀነስ መስተካከል የሚገባቸው ጉዳዮች እንዳሉ ሊሰመርበት ይገባል። በመጨረሻም ራሳችንን ከጥቃት ለመከላከል የሚያግዘን አጠቃላይ አለማዊና አካባቢያዊ ሁኔታ ለመፍጠር፣ ወዳጆችን ለማብዛትና በዚሁ አላማ ዙሪያ እንዲተባበሩን ብቃት ያለው ስራ ተሰርቷል ማለት አይቻልም። ይህ ጉድለት ለአደጋ ተጋላጭነታችንን እያባባሰ የነበረ በመሆኑ መስተካከል እንደሚኖርበት ሊሰመርበት ይገባል።

በአጠቃላይ የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ግቦቻችንን ለማሳካት የምንከተለው አንዱ መሰረታዊ ስትራተጅ ለአደጋ ተጋላጭነታችንን (ቫልነራቢሊቲ) መቀነስ፣ የተጋላጭነታችን ምንጭ የሆኑትን ነገሮች ለይተን ለማስወገድ መረባረብ መሆን ይኖርበታል።

### 3.6. ብቃት ያለው የመከላከል አቅምን መገንባት፣

ደህንነታችንን ለማስጠበቅ የሚያስችለን ዋናው መሳሪያ ልማትና ዴሞክራሲ እንደሆነ በተደጋጋሚ ተገልጿል። በዚህ ላይ በመመስረት ዲፕሎማሲያችን በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ



አደጋዎችን ለመቀነስ፣ ግጭቶች ሳይፈጠሩ በድርድር እንዲፈቱ በማድረግ፣ በዚሁ መልክ ሊፈቱ ያልቻሉትን በመቋቋም ረገድ ደጋፊ የሆነ አለም አቀፋዊና አካባቢያዊ ሁኔታ የመፍጠር ተልዕኮ እንዳለውና ደህንነታችንን በማስጠበቅ ረገድ ከፍተኛ ሚና እንዳለውም ተወስቷል። በዚሁ ክልል ብቃት ያለው የመከላከል አቅምም ተኪ የሌለው ሚና እንደሚጫወት ሊሰመርበት ይገባል።

የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ ሁኔታዎችን በቅርብ እየተከታተለ አገራዊ ደህንነታችንን ለአደጋ የሚያጋልጡ ክስተቶችን አስቀድሞ እየለየ ጥራት ያለው መረጃ በማቅረብ ለዲፕሎማሲያችንም ሆነ ለወታደራዊ ጥረታችን መሰረት የሚሆን ጠንካራና ዘመናዊ የመረጃ ስርአት መዘርጋት ጠንካራ የመከላከል ሃይል በመፍጠር ረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። ብቃት ያለው ወታደራዊ አቅም የመፍጠር ጉዳይም በተመሳሳይ መልኩ ደህንነታችን በማስጠበቅ ረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። በአንድ በኩል ብቃት ያለው ወታደራዊ ሃይል ሲኖርና ሲታወቅ በላያችን ላይ ግጭት ለመቀስቀስ የሚከጅሉ ወገኖች እንደገና እንዲያስቡ ሊገደዱ ይችላሉ። ዲፕሎማሲ ይህንኑ ተጠቅሞ ጉዳዩ በሰላም እልባት እንዲያገኝ የሚያደርግበት የተመቻቸ ሁኔታ ይፈጠርለታል። በሌላ አነጋገር ብቃት ያለው ወታደራዊ አቅም መኖሩ ዋናው ጥቅሙ ግጭቶችን መግታትና (ዲተረንስ) ለዲፕሎማሲ የተመቻቸ ሁኔታ መፍጠር ይሆናል። ግጭት መግታት ባልተቻለበትም ሁኔታ በልማትና በዴሞክራሲ እንቅስቃሴያችን ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሳያስከትል በድል ለመወጣት በር ይከፍታል። ስለሆነም ጥራት ያለው የመረጃ ስርአት

በመዘርጋትና ወታደራዊ አቅምን በማጠናከር ብቃት ያለው የመከላከል አቅምን መገንባት የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ግባችንን ለማሳካት የምንጠቀምበት አንድ መሰረታዊ ስትራተጅ ይሆናል፡፡

ብቃት ያለው የመከላከል አቅምን ለመገንባት በሚደረገው ርብርብ የሚያጋጥሙ የተለያዩ ችግሮች መኖራቸው አይቀርም፡፡ በአንድ በኩል ያለንን አቅም በሙሉ በልማት ላይ ማረባረብ አለብን ብለናል፣ ይህን ማለታችንም ተገቢ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ብቃት ያለው የመከላከል አቅም መገንባት አለብን ብለናል፣ ይህም በኢኮኖሚ ልማታችን ሊውል ይችል የነበረውን ገንዘብና የሰው ሃይል ከልማት ውጭ እንዲሆን ያደርግብናል፡፡ በነዚህ መካከል ግጭት እንደሚኖር መገንዘብና ሁለቱን አቻችሎና አጣጥሞ መሄድ ያስፈልጋል፡፡ ብቃት ያለው የመከላከያ አቅም ግንባታ ጉዳይ ላይ የሚያጋጥም ቁልፍ ችግር ከላይ የተጠቀሰውን ቅራኔ የማጣጣም ጉዳይ ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ ትኩረት ልንሰጣቸው የሚገቡ ስልቶችን እንደሚከተለው ማስቀመጥ ይቻላል፡፡

**(ሀ) በበቂ የስጋት ትንተና ላይ የተመሰረተ ግንባታ ማካሄድ፣**

ምን ያህል ጥራትና ስፋት ያለው ወታደራዊ አቅም መገንባት አለብን የሚለውን ጉዳይ በትክክል መመለስ በሰራዊት ግንባታና በኢኮኖሚ ልማት መካከል ያለውን ቅራኔ ለማጣጣም



ከፍተኛ ተፈላጊነት ያለው ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ጉዳይ በጥቅሉ ለማንምና ለምንም የማይበገር የመከላከያ ሃይል እንገነባለን በሚል ድንፋታ ሊመለስ አይችልም፡፡ ቢሞከርም ይህንን መፈክር እንዳነገበው ደርግ መንኮታኮት ካልሆነ በስተቀር የተለየ ውጤት አያስገኝም፡፡ ምን አይነት ሰራዊት እንገንባ የሚለው ጉዳይ መነሳት ያለበት ካሉብን ስጋቶችና እነዚህን ስጋቶች ለመቋቋም ካለን ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊ ወዘተ. አቅም ነው፡፡

በመሆኑም የሰራዊት ግንባታ ስራችን ካሉብን የአገራዊ ደህንነት ስጋቶች ትንተና መነሳት አለበት፡፡ የልማትና የዴሞክራሲ አላማን እውን ስናደርግ ጥቅማቸው የሚነካባቸው ወይም የተነካባቸው መስሎ የሚሰማቸው የትኞቹ ናቸው? እነዚህ ሃይሎች በኛ ላይ ግጭት ለመቀስቀስ ያላቸው ችሎታ ምን ያህል ነው? በምን መልክስ ሊፈፀም ይችላል? የነዚህ ሃይሎች ግጭት የመቀስቀስ ችሎታ በአጭር፣ በመካከለኛና በረጅም ጊዜ ምን ይመስላል? የነዚህን ሃይሎች ግጭት የመቀስቀስ ሙከራ በልማታችንና በዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ሂደታችን ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ በማይፈጥር መልኩና በአስተማማኝ ሁኔታ እንዴት መመከት ይቻላል? ከዚህ አኳያ ምን ጠንካራና ደካማ ጎኖች አሉን? ብሎ መጠየቅና ትክክለኛ መልስ ማግኘት ያስፈልጋል፡፡ በዚህ መልክ የሚካሄደውን ጥናትና የአደጋ ትንተና በየጊዜው መከለስና ማሻሻል ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ላይ በመመስረት ያሉንን ጠንካራ ጎኖች አሟጦ በመጠቀም ላይ ያተኮረ፣ ግጭትን ለመግታት ካልሆነም በአስተማማኝ መልኩ ለመቋቋም የሚችል ሰራዊት መገንባት ያስፈልጋል፡፡ ስጋቱ ከሚጠይቀው ወይም

አቅማችን ከሚፈቅደው በላይ ሳንንጠራራ፣ ደህንነታችንን በከፍተኛ አደጋ ሳናጋልጥ ሁለቱን አጣጥመን ለመሄድ የሚያስችለን አንዱ መሰረታዊ መሳሪያ ይኸው መሆኑን ተገንዝበን በብቃት መፈፀም ይኖርብናል።

**(ለ) በሰው ሃይል ብቃት ላይ ያተኮረ የግንባታ ስራ መስራት፣**

ፈረስ ያደርሳል እንጅ አይዋጋም ይላል ያገራችን ተረት። ይህ አባባል ዞሮ ዞሮ በጦርነት በተለይም እጅግ የተራቀቀ የውጊያ ቴክኖሎጅ በሌላቸው ሰራዊቶች መካከል በሚካሄድ ጦርነት ወሳኙ ነገር ሰው መሆኑን የሚያመለክት በተግባር በተደጋጋሚ የተረጋገጠ ትክክለኛ አባባል ነው። የጦር መሳሪያና ቁሳቁስ ከዚህ አኳያ የሚኖራቸውን አስተዋፅኦ በምንም አይነት መልኩ አሳንሶ ማየት የማይቻልና የማይገባ ቢሆንም በራሱ በጦር መሳሪያውና በቁሳቁሱ በአግባቡ መጠቀም የሚችለው ሰው ነው። ብቃት ያለው ሰው ከሌለ ምርጥ መሳሪያ ተሸክሞም ለድል ላይበቃ ይችላል። በመሆኑም በኛ ሁኔታ ብቃት ያለው የመከላከያ ሃይል መገንባት ማለት በወሳኝነት ብቃት ያለው ወታደር መፍጠር፣ ብቃት ያለው የሰው ሃይል መፍጠር ማለት ነው።

በሰራዊት ግንባታ ስራችን በዋናነት ብቃት ያለው የሰው ሃይል በመፍጠር ላይ የምናተኩረው በጦርነት ወሳኙ ተዋጊው ሰው ነው በሚል ብቻ አይደለም። በተራቀቀና ከፍተኛ የመሳሪያ ክምችት ላይ የተመሰረተ የሰራዊት ግንባታ ስራ እንስራ ብንል ኢኮኖሚያችን ደቆ በሂደት ከልማቱም ከመከላከያ ሃይል



ግንባታውም ሳንሆን እንደምንቀር ስለምንገነዘብ ጭምር ነው። በሌለን ገንዘብ ላይ ለማንም የማይበገር ሰራዊት እንገነባለን ብለን መሳሪያ ለመከመር ብንጠቀምበት፣ በመቶ ሺዎች ቋሚ ሰራዊት ብናግተለትል በሂደት ኢኮኖሚው መሸከም አቅቶት መንኮታኮቱ የማይቀር ይሆናል። ስለሆነም በልማትና በዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ሂደታችን ላይ ከፍተኛ እንቅፋት ፈጥሮ ደህንነታችንን ለባሰ አደጋ በማያጋልጥ አኳኋን ሰራዊት እንገንባ ካልን እንደዚህ አይነቱን ተፅእኖ በማያሳርፍብን በሰው ሃይል ጥራትና ብቃት ላይ ባተኮረ አኳኋን መፈፀም አለብን።

የሰራዊት ግንባታችን በሰው ሃይል ብቃት ላይ ያተኮረ እንዲሆን ማድረግ የምንፈልግበት ሌላው ምክንያት በዚህ ረገድ ጠንካራ ጎን አለን ብለን ስለምናምንና የሰራዊት ግንባታችን ጠንካራ ጎናችንን አሟጦ በመጠቀም ላይ መመስረት ስላለበት ነው። የአንድ ሰራዊት ብቃት የሚወሰነው ዋናው ነገር የአላማ ቁርጠኝነት ነው። የአላማ ቁርጠኝነት የሚመነጨው እያንዳንዱ ወታደር በስርአቱ አላማዎች ላይ ጠንካራ እምነት ሲኖረውና ለዚሁ ተፈላጊውን መስዋእትነት ለመክፈል ዝግጁ ሲሆን ነው። ህገ-መንግስታዊ ስርአታችን፣ የልማትና የዴሞክራሲ ግንባታ ራዕያችን የህዝባችንን መሰረታዊ ፍላጎትና ጥቅም የሚያስጠብቅ ነው። ህዝቡ በዚህ ዙሪያ አንድ የጋራ አገራዊ እምነትና አመለካከት ከያዘ መላው ህዝብ በልበ-ሙሉነት አገሩንና ደህንነቱን ሊከላከል ይችላል። ከህዝብ የተገኘው ሰራዊትም ልበ-ሙሉና ቁርጠኛ ሆኖ ሊዋጋ ይችላል። በዚህ ላይ በመመስረት የሰራዊቱን የአላማ ፅናት ለማጠናከር ሰፊ የፖለቲካ ስራ ከተሰራም አስተማማኝ የአላማ

ዕናት መፍጠር ይቻላል፡፡

በሌላ አነጋገር የያዝነው የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ርብርብ፣ በዚህ ዙሪያ የምንፈጥረው አገራዊ የጋራ እምነትና አመለካከት፣ በዚህ መስክ የምናስመዘግባቸው የልማትና የዴሞክራሲ ድሎች፣ ከድሎቹ ተጠቃሚ የሆነና እነዚህን ድሎች ለመጠበቅ ቆርጦ የተነሳ ዜጋን ይፈጥርልናል፡፡ ከዚሁ የተቀዳና ተጨማሪ የፖለቲካ ስራ ተሰርቶበት የማይበገር መንፈስ ያለው ሰራዊት ለመገንባት ያስችለናል፡፡ ዋነኛው ጠንካራ ጎናችን ፍትሃዊና ህዝባዊ አላማችን በመሆኑ ይህንኑ አሚጠን በመጠቀም ከፍተኛ ብቃት ያለው ሰራዊት መገንባት እንችላለን፡፡

በአገራችን ሰፊ የትምህርትና የአቅም ግንባታ ስራ እየተሰራ ነው፡፡ የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ለዜጎች በሞላ ለማዳረስ ከፍተኛ ውጤት የተገኘበት ስራ እየተሰራ ሲሆን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትም በከፍተኛ ደረጃ እየተስፋፋ ነው፡፡ ከዚሁ የሚቀዳ ሰራዊት በዚህ ላይ ተመስርቶ የሚሰጥ ወታደራዊ ስልጠና በወታደራዊ ቴክኒክና ንድፈ-ሃሳብ የተካነ ብቃት ያለው ሰራዊት ሊሆን ይችላል፡፡ አሰራርና አደረጃጀቱ ዘመናዊና ቀልጣፋ እንዲሆን ማድረግ ይችላል፡፡ እነዚህን በማጣመር ቁርጠኛ፣ በወታደራዊ ቴክኒክና ንድፈ-ሃሳብ የተካነ፣ ዘመናዊና ቀልጣፋ አደረጃጀትና አሰራር ያለው ሰራዊት መፍጠር ይቻላል፡፡ ጠንካራ ጎናችንን አሚጠን በመጠቀም በኢኮኖሚያችን ላይ ከባድ ተፅእኖ በማይፈጥር መልኩ ብቃት ያለው የመከላከያ ሃይል መፍጠር ይቻላል፡፡



**(ሐ) እያንዳንዷን ብር በቁጠባ የመጠቀም አሰራር፣**

አገሮች ሁሉ ለመከላከያ ግንባታ ከሚያወጡት ወጭ የላቀ የመከላከያ አገልግሎት ማግኘታቸውን ማረጋገጥ ይፈልጋሉ፣ ይሞክራሉም፡፡ በኛ ሁኔታ ይህ አሰራር መሰረታዊ የህልውና ጉዳይም ጭምር ነው፡፡ ለመከላከያ የምናወጣት እያንዳንዷ ብርና ሳንቲም አገራዊ ደህንነታችንን ከማስጠበቅ አኳያ የተሻለ ውጤት በሚያመጣ አኳኋን ጥቅም ላይ እየዋለች መሆንዋን ካላረጋገጥን አንድም ለመከላከያ የምናወጣው ወጭ ከባድ እየሆነ ኢኮኖሚያዊ እድገታችን ተሰናክሎ መከላከያውም ሌላውም ተያይዞ የሚጠፋበት ሁኔታ ይፈጠራል፣ አለያም ኢኮኖሚያችን እንዳይጎዳ ብለን ወጭውን ብንገድብ፣ የተመደበው በአግባቡ በጥቅም ላይ ባለመዋሉ የመከላከያ አቅማችን ደካማ ሆኖ ለከፍተኛ አደጋ ልንጋለጥ እንችላለን፡፡ ስለሆነም የልማትና የመከላከያ ግንባታ ፍላጎታችንን ለማጣጣም የምንችለው ለመከላከያ የምናውላት እያንዳንዷ ሳንቲም የላቀ የመከላከል አገልግሎት በሚያስገኝ አኳኋን ጥቅም ላይ መዋሏን በማረጋገጥ ነው፡፡

ብቃት ያለው የሰው ሃይል በመፍጠር ላይ ያተኮረ የሰራዊት ግንባታ ስልት ማስቀመጣችን ራሱ እያንዳንዷ ሳንቲም የላቀ የመከላከያ አገልግሎት በሚያስገኝ አኳኋን እንድንጠቀምባት በር የሚከፍትልን ነው፡፡ ዘመናዊና ቀልጣፋ አሰራርና አደረጃጀት መፍጠርም ተመሳሳይ ውጤት ይኖረዋል፡፡ የተወሰነ የላቀ ብቃት ያለው ቋሚ ሰራዊት አደራጅተን አስፈላጊ ሲሆን የሚዘምት ሰፊ

ተጠባባቂ ሃይል የመፍጠር እንቅስቃሴያችንም በመለስተኛ ወጭ የላቀ የመከላከል አቅም የሚፈጥርልን ነው። እያንዳንዷ ለጦር መሳሪያና ለቁሳቁስ የምትወጣው ወጭም በተመሳሳይ መልክ እየተመዘነች ጥቅም ላይ መዋል ይኖርባታል። የሰራዊቱን ጉልበትና የስራ ችሎታ በመጠቀም ወጭን ለመቀነስ የመሞከር አሰራር (ለምሳሌ በካምፕ ግንባታ ላይ) ተመሳሳይ ውጤት ያለውና በተቻለ መጠን በስፋት ተግባራዊ ሊሆን የሚገባው ነው።

### (መ) የመከላከያ ወጭ ከኢኮኖሚው ጋር እንዲመጋገብ ማድረግ፣

ወጭን ቀንሰን የተሻለ የመከላከል አቅም ከመፍጠር አልፈን ምንም ብናደርግ የመከላከያ ወጭያችንን ዜሮ ልናደርገው አንችልም። በግድ መውጣት ያለበት ወጭ ከልማታችን የሚቀነስ መሆኑም አይቀርም። ይሁንና የመከላከያ ወጭያችን በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ከኢኮኖሚው ጋር እንዲመጋገብ በማድረግ በኢኮኖሚው ላይ የሚያሳድረውን ተፅእኖ መቀነስ ይቻላል። በዚህ መሰረት ለምሳሌ የሰራዊቱ አልባሳት፣ ምግብ ጫማ ወዘተ. በአገር ወስጥ ፋብሪካዎች እንዲመረት በማድረግ፣ ፋብሪካዎችን በዚሁ ገበያ በዋጋና በጥራት በከፍተኛ ደረጃ እንዲፎካከሩ በማድረግ ወጭው ከኢኮኖሚያችን ጋር እንዲመጋገብ ማድረግ ይቻላል። በተመሳሳይ መልኩ የመከላከያ ሃይላችን የሚጠቀምባቸውን መሳሪያዎች ለመፈብረክና ለመጠገን የሚገነባውን አቅም በተወሰነ ደረጃ የሲቪል ኢኮኖሚው የሚፈልጋቸውን ሸቀጦችና አገልግሎቶች እንዲያመርት በማድረግ፣ በዚህ ዘርፍ የተገኘው እውቀትና ልምድ



ወደ ሲቪል ኢኮኖሚው በተደራጀ አኳኋን እንዲሸጋገር በማድረግ መመጋገቡን ማጠናከር ይቻላል። እነዚህንና መሰል አግባቦችን በመከተል የመከላከያ ወጭ ከኢኮኖሚው ጋር እንዲመጋገብ የማድረግ ስልትን መከተልና በኢኮኖሚያችን ላይ የሚያስከትለውን አሉታዊ ተፅእኖ መቀነስ ይቻላል።

### (ሠ) ከልማት እንቅስቃሴያችንና ከወቅታዊ አደጋዎች ጋር ማጣጣም፣

ብዙ ኢኮኖሚስቶች አንድ አገር ከብሄራዊ ምርቱ ከሁለት ከመቶ በላይ ለመከላከያ ወጪ ካደረገ በእድገቱ ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ ያሳድራል ይላሉ። ይህ አባባል ብዙዎች የሚስማሙበት ሲሆን ወጪው ከሁለት ከመቶ በላይ እስካልሆነ ድረስ በኢኮኖሚው ላይ ምንም አይነት አሉታዊ ተፅእኖ የለውም ማለት እንዳልሆነ ግን ሊሰመርበት ይገባል። ከዚህ በመነሳት በዚህ መስክ የምናወጣው ወጪ ከብሄራዊ ገቢያችን ከሁለት በመቶ እንዳይበልጥ ብለን መነሳት እንችላለን፣ ይገባናልም። ከሁለት በመቶ እንዳይበልጥ ስንል እድገታችን ፈጣን ከሆነ ብሄራዊ ገቢያችን በፍጥነት እያደገ የዚሁ ሁለት በመቶም ከፍተኛ እየሆነ እንደሚመጣና በተጨባጭ ለዚሁ ተግባር የምናውለው ገንዘብ እየጨመረ እንደሚሄድ መገንዘብ ይቻላል። ስለሆነም የሁለት ከመቶ ጣርያ በማስቀመጥ ኢኮኖሚያዊ እድገታችን ሲፈጥን በዚያው መጠን ለመከላከያ የምናወጣውን ወጪ እየጨመርን በመሄድ በኢኮኖሚያችን ላይ ከባድ ተፅእኖ በማይፈጥር አኳኋን አስተማማኝ ሃይል የመገንባት

አሰራር ልንከተል እንችላለን፣ ይገባናል፡፡

የመከላከያ ወጪያችን ከኢኮኖሚ እድገታችን ጋር እንዲቆራኝ ማድረጉ ተገቢና ትክክለኛ ቢሆንም እንደ እድገቱ መጠንና እንደአደጋው ወቅታዊነት ከተቀመጠው ጣርያ ከፍና ዝቅ ሊል እንደሚችልም መታሰብ አለበት፡፡ ረጅም ባልሆነ ጊዜ ውስጥ ይከሰታል ተብሎ የሚገመት አደጋ ካለ በረጅም ጊዜ ውስጥ የሚገነባ የመከላከያ አቅም ሊገታው አይችልም፡፡ አደጋው ይከሰታል ተብሎ በሚገመትበት ወቅት ነው ዝግጁ መሆን ያለበት፡፡ በዚህን ጊዜ ከጣርያውም በላይ ወጪ ማውጣት አማራጭ የሌለው ይሆናል፡፡ ሊከሰት ይችላል ተብሎ የሚገመተው አደጋ ጊዜ የሚሰጥ ከሆነ ደግሞ የኢኮኖሚ እድገቱን በማፋጠን ለዘለቄታው የተሻለ የመከላከያ አቅም መፍጠር ስለሚቻል ከጣርያው በታች ዝቅ እንዲል ማድረግ የተሻለ አማራጭ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለሆነም ለመከላከያ ወጪ አጠቃላይ ጣርያ አስቀምጦ እንደስጋት ደረጃው ከፍና ዝቅ እንዲል የማድረግ ስልት በኢኮኖሚ እድገትና በሰራዊት ግንባታ መካከል ያለውን ቅራኔ ለማጣጣም የምንጠቀምበት አንድ ስልት ይሆናል፡፡

የመረጃ ስርአት የመፍጠር ስራችንም በዋነኛነት ለሰራዊት ግንባታ ባስቀመጥነው አቅጣጫና ከዚሁ ጋር ተቀናጅቶ መፈፀም የሚችልና የሚገባው ነው፡፡ እዚህ ላይ በድጋሚ ሊሰመርበት የሚገባው ጉዳይ የምንገነባው የመከላከያ አቅም ዋነኛ ተልእኮ ግጭትን መግታት (ዲተረንስ) መሆን እንዳለበት ነው፡፡ ርብርባችን ልማትና ዴሞክራሲ እንጂ ጦርነት ላይ መሆን



የለበትም፡፡ ግባችን መበልፀግ እንጅ ወታደራዊ እብሪትና ጀብደኝነት መሆን የለበትም፡፡ ግጭት ከመግታት አልፌን ወደ ጦርነት የምንገባው በአንድና በአንድ ምክንያት ብቻ መሆን አለበት፡፡ ወደ ጦርነት የምንገባው ጉዳዩ ለልማትና ለዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ አጀንዳችን በፍፁም የማይታለፍ ማነቆ ሲሆንና በድርድርና ሰጥቶ በመቀበል መርህ ለመፍታት የሚያስችሉ አማራጮች በሙሉ ተዳሰው ሳይሳኩ ሲቀሩ ብቻ ነው፡፡ በዚሁ አኳኋን ተገደን ወደ ጦርነት ከገባንም ግባችን በልማትና ዴሞክራሲ አጀንዳችን ላይ የሚያስከትለውን ተፅእኖ በሚቀንስና የተፈጠረውን ማነቆ በሚያስወግድ አኳኋን ተከላክለን ለማሸነፍ መሆን ይኖርበታል፡፡

### 3.7. ጠንካራ የማስፈፀም አቅምን መገንባት፣

የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት አላማችንን፣ ግቦቻችንና ስትራተጅዎችን ነድፈን፣ ፖሊሲዎችን ዘርዝረን ትክክለኛ እቅዶች ነድፈን አፈፃፀም ላይ ካልፈሰፈስነው ታጥቦ ጭቃ ከመሆን ልንድን አንችልም፡፡ ስለሆነም ጠንካራ የማስፈፀም አቅምን መገንባት እንደ አንድ መሰረታዊ ስትራተጅ መወሰድ ይኖርበታል፡፡

#### (ሀ) አንድ የጋራ አገራዊ አመለካከትና እምነት መፍጠር፣

የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት አላማችን ዞሮ ዞሮ

የልማት፣ የዴሞክራሲ፣ የህልውና ጉዳይ ነው:: በመሆኑም ጉዳዩ የጥቂት ሙያተኞች ወይም የፖለቲካ ሃላፊዎች ስራ ተደርጎ መወሰድ የለበትም:: የተሳካ አፈፃፀም ሊኖር የሚችለውም መላው ህዝብ እንደ ሁኔታው ሲሳተፍበት ነው:: ከዚህ ጋር በተያያዘ ከአገሮች ጋር የሚኖረን የግንኙነት ፖሊሲ መሰረታዊ የደህንነት ፖሊሲ ስትራተጅ ወዘተ. ለህዝብ መገለፅ አለበት:: ህዝቡ ተወያይቶ ተከራክሮ የሚሻሻለውን አሻሽሎ የጋራ አቋም ሊይዝበት ይገባል::

አንዳንድ ተንታኞች በዚሁ መልኩ የውጭ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲዎችንና ስትራተጅዎችን በአደባባይ መዘርገፍ ምስጢር ማባከን፣ ለጠላት የተመቻቸ ሁኔታ መፍጠር ነው ይላሉ:: ይሁንና እነዚህን ጉዳዮች በይፋ መድረክ በመወያየት የሚገኘው ጥቅምና ጉዳት መመዛዘን አለበት:: በይፋ መድረክ በመወያየት ህዝቡ የመንግስትን ፖሊሲ ለማወቅ፣ ለማስተካከልና ለመቆጣጠር ዕድል ያገኛል:: ግልፅነትና ተጠያቂነትን ብሎም ዴሞክራሲን በትክክል ተግባራዊ ማድረግ ያስችላል:: ህዝቡ አላማዎቹን፣ ግቦቹን፣ ስትራተጅዎቹንና ፖሊሲዎቹን በትክክል በመገንዘብ በሙሉ ልብ ተቀብሎ ለተግባራዊነታቸው በመረባረብ የተሳካ አፈፃፀም እንዲኖር ወሳኝ ተፅእኖውን ማሳረፍ ይችላል:: እነዚህን ጉዳዮች በይፋ መድረክ ማቅረብ የአገራችን ፖሊሲ በስህተት ጥቅማቸውን የሚነካባቸው መስሎ የሚታያቸው ወገኖች የተሳሳተ አመለካከታቸውን እንዲያስተካክሉ በከፍተኛ ደረጃ ሊረዳ ይችላል:: በጉዳዩ ላይ አንድ የጋራ አገራዊ አመለካከትና እምነት በመፍጠር ቀጣይነት ያለው፣ በየጊዜው የማይገላበጥ የውጭ ጉዳይና የአገራዊ



ደህንነት ፖሊሲ እንዲኖር ለማድረግ ያስችላል:: እነዚህ በጣም ከፍተኛ ግምት የሚሰጣቸው ጥቅሞች ናቸው::

በሌላ በኩል አላማችን ጥቅማቸውን የሚነካባቸው ወገኖች አላማችንን፣ ስትራተጅያችንና ፖሊሲያችንን ወዘተ. በትክክል ለማወቅ ዕድል ያገኛሉ፣ ይህንንም እኛን ለመጉዳት ሊጠቀሙበት ይችላሉ:: ይሁንና እዚህ ላይ ታሳቢ ሊሆን የሚገባው እነዚህን መሰረታዊ አቅጣጫዎች እንደብቅ ብንልስ አፈፃፀማችንን በመከታተል ሊገምቷቸውና ሊያውቋቸው አይችሉም ወይ? የሚለው ጉዳይ መነሳት አለበት:: በመሆኑም እንደብቅ ብንል በተሳካ መልኩ መደበቅ የምንችለው ከጠላቶች ነው ወይስ ከህዝባችን የሚለው ታሳቢ መሆን ይኖርበታል:: መደበቅ የሚገባቸውና የሚችሉ ዝርዝር ጉዳዮች ቢኖሩም መሰረታዊ ጉዳዮችን በቂ የመረጃ አውታር ካላቸው ጠላቶች በአስተማማኝ መልኩ መሰወር አይቻልም:: ቢሞከርም ውጤቱ ነገሩን ከህዝብ ደብቆ ከጠላት ግን ሳይደብቁ መቅረት ነው የሚሆነው::

በድምር ሲታይ በመሰረታዊ ፖሊሲዎችና አቅጣጫዎች ላይ በይፋ ህዝቡ እንዲወያይ በጉዳዩ ላይ አንድ አገራዊ የጋራ አመለካከትና እምነት እንዲያዝ ማድረግ ከጉዳቱ ጥቅሙ እጅግ የላቀ ሆኖ ይገኛል:: በመሆኑም ህዝቡ በጉዳዩ ላይ የጋራ ግንዛቤ እንዲይዝና በያለበት ለአፈፃፀሙ የየበኩሉን አስተዋፅኦ ለማበረከት የሚችልበት ሁኔታ እንዲፈጠር ማድረግ ጠንካራ የማስፈፀም አቅምን ከመገንባት አኳያ የቅድሚያ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ

ነው።

**(ለ) የዲፕሎማሲ ሙያተኛ አቅም መፍጠር፣**

የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲያችንን በሚመለከት ምልአተ-ህዝቡ የጋራ ግንዛቤ እንዲኖረው፣ በያለበት እንደአቅሙ ለተግባራዊነቱ እንዲንቀሳቀስ ማድረግ የአፈፃፀም እንቅስቃሴያችን መሰረት ቢሆንም ስራውን የሚያንቀሳቅስ ሙያተኛ የሰው ሃይል ባልተፈጠረበት፣ በአግባቡ ተደራጅቶ በማይንቀሳቀስበት ሁኔታ የተሳካ አፈፃፀም ሊኖር ይችላል ማለት አይደለም። በመሆኑም ጠንካራ ሙያተኛ የሰው ሃይል መፍጠርና በአግባቡ አደራጅቶ ማንቀሳቀስ ያስፈልጋል።

ሙያተኛው የሰው ሃይል የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ስትራተጅያችንና ፖሊሲዎቻችን የግድ የሚሏቸውን ጥናቶች በብቃት ለማካሄድ የሚችል መሆን አለበት። ሙያተኛው የሰው ሃይል ፖሊሲዎቹንና ስትራተጅዎችን በብቃት ለመፈፀም የሚያስችል እቅድ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ የሚችል መሆን አለበት። እንደዚህ አይነቱን ሙያተኛ ለመፍጠር የመጀመሪያው ርምጃ በወሳኝ የአገራዊ ጥቅምና የአገራዊ ደህንነት ጉዳዮች ላይ የጋራ ግንዛቤ መያዝ ነው። እንደዚህ አይነቱ የጋራ ግንዛቤ ባልተያዘበት ሁኔታ በተለያዩ ሙያዎች የተካነ ተመራማሪና ዲፕሎማት ቢበራከትም ብሄራዊ ጥቅማችንና አገራዊ ደህንነታችንን ለማስጠበቅ የሚያስችል የተቀናጀ ስራ መስራት አይቻልም።



ስለሆነም ሙያተኛ አቅም የመገንባቱ ጉዳይ መሰረቱ የጋራ አገራዊ እምነትና አመለካከት መፍጠር እንደሆነ ተገንዝበን በዚህ ላይ በቂ ስራ መስራት ይኖርብናል።

የጋራ አገራዊ እምነትና አመለካከት መያዙ የመጀመሪያው ወሳኝ ርምጃ ቢሆንም ይህንን እምነት የያዘ ሁሉ የተዋጣለት ዲፕሎማት ወይም ተመራማሪ መሆን ይችላል ማለት አይደለም። በእምነቱ ላይ ጥልቀት ያለው ሙያ፣ እውቀትና ክህሎት እንዲኖረው ያስፈልጋል። እንደዚህ አይነቱን ሙያተኛ በአገር ውስጥና በውጭ ማሰልጠን፣ በአግባቡ አደራጅቶ ማንቀሳቀስ፣ የተለያዩ የምርምርና ጥናት፣ የትምህርትና ስልጠና ተቋማትን ማቋቋም አቀናጅቶ ማንቀሳቀስ ያስፈልጋል።

በውጭ ጉዳይና በአገራዊ ደህንነት ጉዳይ ላይ አስተዋፅኦ ያላቸው የመንግስት አካላት እጅግ በርካታ ናቸው። የውጭ ጉዳይ፣ የመከላከያ፣ የደህንነት ሚኒስቴር መሥሪያቤቶችና ተቋሞች ተቀናጅተው የሚሰሩበት ሁኔታ መፍጠር አንድ ጉዳይ ነው። የዲፕሎማሲያችን ማዕከል ኢኮኖሚ መሆን ያለበት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በልማት ስራ ላይ የተሰማሩ ሚኒስቴር መሥሪያቤቶችና ሌሎች ተቋሞችም ቁልፍ አስፈፃሚ አካላት ናቸው። እነዚህ ተቋሞች ስራቸውን፣ በውጭ ጉዳይና በደህንነት ዘርፍ ያላቸውን ስራ ጭምር በብቃት ለመፈፀም የሚያስችላቸው የሰው ሃይል፣ አደረጃጀትና አሰራር እንዲኖራቸው ማድረግ የመጀመሪያው እጅግ ተፈላጊ የሆነ ጉዳይ ነው። እያንዳንዳቸው በተናጠል የሚሰሩት ስራ የሚፈለገውን ውጤት ሊያስገኝ እንደማይችል ተገንዝቦ ሁሉም

በተቀናጀ አኳኋን የሚረባረቡበት አደረጃጀትና አሰራር እንዲኖር ማድረግ ደግሞ ሌላው ልዩ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው፡፡

**(ሐ) በአፈፃፀም ላይ አስተዋፅኦ ያላቸውን ወገኖች ማሳተፍ፣ ማስተባበር፣**

ህዝቡ በአገራዊ ጥቅምና ደህንነትና ይህንን ለማስጠበቅ በውጭ ጉዳይና በደህንነት ዘርፍ ልንከተል የሚገባን አቅጣጫ ላይ የጋራ ግንዛቤ እንዲይዝ፣ በዚህ ላይ ተመስርቶ በተለይም በአገር ውስጥ በሚደረግ የአፈፃፀም እንቅስቃሴ ላይ በብቃት እንዲሳተፍ ማድረግ፣ ስራውን በባለቤትነት የሚያስፈፅም አካል በአግባቡ አደራጅቶ ብቃት ባለው ሙያተኛ የሰው ሃይል ማጠናከር ጠንካራ የአፈፃፀም አቅምን ለመገንባት እጅግ ወሳኝ ቢሆኑም ብቻቸውን የሚፈለገውን ውጤት ሊያስገኙ አይችሉም፡፡ በዚህ መስክ በውጭ በሚካሄደው ሁሉን አቀፍ እንቅስቃሴ የላቀ አስተዋፅኦ ለማበርከት የሚችሉትን ወገኖች በሙሉ ማሳተፍና በተቻለ መጠንም ማስተባበር ይገባል፡፡ ከዚህ አኳያ ልዩ ግምት የሚሰጣቸው ክፍሎች እንደሚከተለው ማስቀመጥ ይቻላል፡፡

ምሁራንና የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች አንድ የጋራ አገራዊ እምነትና አመለካከት በመፍጠር ረገድ ካለባቸው አጠቃላይ ሃላፊነት በተጨማሪ በዚሁ መስክ ከፍተኛ ሚና መጫወት ይችላሉ፣ ይገባቸዋልም፡፡ ለፖሊሲያችንና ስትራተጂያችን ተፈላጊ የሆኑ ጥራት ያላቸው ጥናቶችና ምርምሮች በማካሄድ ረገድ የመንግስት የምርምርና ጥናት ተቋሞች የራሳቸው ሚና ያላቸው ቢሆንም



ከዚህ ውጭ ያሉ ምሁራንና የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞችም የላቀ ሚና መጫወት ይገባቸዋል፡፡ በዚህ ላይ በመመስረትም አማራጭ ሃሳቦች እንዲቀርቡ፣ ክርክር እንዲደረግባቸውና እንዲብላሉ ማድረግ ይገባቸዋል፡፡ የሰው ሃይል በማሰልጠን ረገድም ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማበርከት ይገባቸዋል፡፡ መንግስት ይህንኑ ተገንዝቦ ምሁራንና የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች ሚናቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ማደፋፈርና በተቻለ መጠንም ማስተባበር ይኖርበታል፡፡

በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በጥናትና ምርምር ሊያበረክቱ ከሚችሉትና በአገራቸው ልማት ላይ ኢንቨስት በማድረግ ከሚያደርጉት አስተዋፅኦ በተጨማሪ፣ ለአገራችን በሚኖሩበት አገር ወዳጆችን በማፍራት፣ የሚኖሩባቸው አገሮች ከኢትዮጵያ ጋር እንዲ ተባበሩ በመጎትጎት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማበርከት ይችላሉ፡፡ በሚኖሩ ባቸው አገሮች በሚገኙ ኩባንያዎችና በአገራችን ኩባንያዎች መካከል መገናኛ ድልድይ በመሆን የኢንቨስትመንትና የንግድ ትስስሮች እንዲጠናከሩና የኢትዮጵያ ምርቶች በሚኖሩባቸው አገሮች ገበያ እንዲያገኙ በማድረግም በጣም ከፍተኛ ሚና መጫወት ይችላሉ፡፡ በተለይም በኢኮኖሚው መስክ ሊጫወቱ የሚችሉት ሚና የላቀ ነው፡፡ መንግስት ይህንን ተገንዝቦ በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጅ የሆኑ ግለሰቦች በዚሁ መስክ ሚናቸውን በአግባቡ እንዲጫወቱ ለማበረታታትና በተቻለ መጠንም ለማስተባበር ጥረት ማድረግ አለበት፡፡

የዲፕሎማሲያችን ማዕከል ኢኮኖሚው መሆን እንዳለበት አስቀድሞ የተወሳ ጉዳይ ነው:: የግል ባለሃብቱ በኢኮኖሚ ልማታችን ላይ የላቀ አስተዋፅኦ እንዳለውና ሊኖረውም እንደሚገባ የሚታወቅ ጉዳይ ነው:: በመሆኑም የግል ባለሃብቱም በዲፕሎማሲያችን ላይ እጅግ ቁልፍ የሆነ ሚና መጫወት አለበት:: ለልማታችን የተመቻቸ ሁኔታ መፍጠር ማለት ለግል ባለሃብቱ የተመቻቸ ሁኔታ መፍጠር ማለት ጭምር ስለሆነ በውጭው ሁኔታ ለልማታችን የተመቻቸ ሁኔታ እንዲፈጠር ባለው አቅም ሁሉ መረባረብ የምርት ተቋሙን ከማሻሻል ተነጥሎ የማይታይ የትርፍና ኪሳራ ጉዳይም ጨምር ነው:: ለልማታችን የላቀ አስተዋፅኦ ያለው የንግድና ኢንቨስትመንት ስራ በዋነኛነት በአገራችን ባለሃብቶችና በውጭ ባለሃብቶች መካከል በሚፈጠር ትስስር የሚፈፀም ነው:: ስለሆነም የግል ባለሃብቱ ቁልፍ ሚናውን ሊጫወትበት የሚገባ የስራ መስክ ነው:: መንግስት ይህንን ተገንዝቦ የግል ባለሃብቱ በዚህ መስክ በስፋትና በብቃት እንዲሰማራ መደገፍ ማበረታታትና በተቻለም መጠን ማስተባበር አለበት::

በግሎባላይዜሽን በጥብቅ በተሳሰረችው አለም የሲቪል ማህበረሰብ በአገሮች መካከል በሚደረግ ግንኙነት ላይ እየተጠናከረ በመሄድ ላይ የሚገኝ ሚና እየተጫወተ ነው:: የሃይማኖት ድርጅቶች፣ የብዙሃንና የሙያ ማህበራት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በመ ላው አለም ከሚገኙ መሰል ድርጅቶች ጋር የተለያዩ ትስስሮችን በመፍጠር የግሎባላይዜሽን ትሩፋት ለሁሉም እንዲሆን ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ጥረት እያደረጉ ነው::



በመካከላቸው በሚፈጠር ትብብር ለልማትና ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ የሚጠቅሙ ስራዎችን ይሰራሉ:: አገሮች እርስ በርሳቸው እንዲቀራረቡና እንዲተባበሩ ለማድረግ የሚያስችሉ ተጨማሪ የትስስር ገመዶች እየሆኑ ነው:: መንግስት ይህንን እጅግ መሰረታዊ የሆነውን የግሎ ባላይዜሽንን ውጤት በአንክሮ ሊገነዘበው ይገባል:: ከዚህ በመነሳትም የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ በግሎባላይዜሽን ማዕቀፍ የአገራችንን አገራዊ ጥቅምና

ደህንነት ለማስጠበቅ በሚደረገው ርብርብ ሚናውን በአግባቡ እንዲጫወት መደገፍ፣ ማደፋፈርና በተቻለ መጠን ማስተባበር አለበት።

ጠንካራ የማስፈፀም አቅም ገንብተን አገራዊ ጥቅማችንና ደህንነታችንን ለማስጠበቅ የሚያስችል አስተማማኝ ስራ መስራት የምንችለው ከላይ የተጠቀሱትን የማስፈፀም አቅሞች በማብቃት፣ በሰፊው በማሳተፍና በተቻለ መጠን በማስተባበር ብቻ ነው።

# ክፍል II

# ከአገሮች ጋር የሚኖረን የግንኙነት ፖሊሲ፣

## 1. የአፍሪካ ቀንድ አገሮች፣

ከአገሮች ጋር ስለሚኖረን ግንኙነት ስናነሳ ጎረቤቶቻችን ከሆኑት የአፍሪካ ቀንድ አገሮች ማለትም ስለሱዳን፣ ኤርትራ፣ ጅቡቲ፣ ሶማሊያና ኬንያ አስቀድመን ማንሳታችን ተገቢ ነው። እነዚን አገሮች የቅርብ ጎረቤቶቻችን እንደመሆናቸው መጠን ከአገራችን ጋር የቋንቋ፣ የባህል፣ የታሪክ፣ የተፈጥሮ ሃብት ወዘተ. ግንኙነት አላቸው። በአገራችን የሚካሄደው ለውጥ እነሱን በቀጥታ ይነካል፣ በነሱ ውስጥ የሚከናወኑ ሁኔታዎችም እኛን በቀጥታ ይመለከታሉ። እኛን ከነሱ ጋር የሚያገናኙንና በልማታችን ላይ የራሳቸው አስተዋፅኦ ያላቸው ወንዞች አሉ። ይህ ሁሉንም ጎረቤቶቻችን የሚመለከት ሲሆን በተለይም ሱዳንንና ሶማሊያን ከዚያም አልፎ ኬንያን ይመለከታል። አገራችን



በአሁኑ ወቅት ወደብ አልባ ስትሆን ሁሉም ጎረቤቶቻችን ወደብ ያላቸውና የወደብ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ናቸው። ከዚህ በመነሳት ከጎረቤት አገሮች ጋር ጥብቅ ትስስር እንዳለን ተገንዝበን ከነዚህ አገሮች ጋር የሚያገናኘንን ትክክለኛ ፖሊሲ መቀየስ ይገባናል።

### 1.1. አጠቃላይ ፖሊሲ፣

ከማንኛውም አገር ወይም የአገሮች ስብስብ ጋር የሚኖረን ግንኙነት በመሰረታዊ አገራዊ ጥቅማችንና ደህንነታችን ላይ የተመሰረተ፣ ስለሆነም የልማትና የዴሞክራሲ አላማችንን እውን ከማድረግ ጋር የተያያዘ ነው። በዚህ ረገድ ከአፍሪካ ቀንድ አገሮች ጋር የሚኖረን የግንኙነት ፖሊሲም አገሮቹ በአገራችን ልማትና ዴሞክራሲ ካላቸው ፋይዳ መነሳት ይኖርብናል። ምን ጊዜም ቢሆን አይናችንን ከመሰረታዊ አገራዊ ጥቅማችን ሳንነቅል በሰከነ አእምሮ አገሮቹ ከዚህ አኳያ የሚጫወቱትን ፋይዳ መተንተንና በዚህ ላይ የተመሰረተ ፖሊሲ መንደፍ አለብን።

ከአገሮቹ ጋር የተለያየ የፍቅርም የጠብም ግንኙነት የነበረን በመሆኑ የነዚህን አገሮች ፋይዳ በምንተነትንበት ወቅት በስሜት የመነሳት አደጋ ከፍተኛ ነው። በአንድ በኩል በዋነኛነት አገሮቹ በልማታችንና በዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ትግላችን ላይ ያላቸውን በጎም ሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ በተለያዩ ምክንያቶች አጋኖ የማየት፣ በሌላ በኩል ደግሞ በተለያዩ ምክንያቶች ፋይዳቸውን አሳንሶ የማየት አዝማሚያዎች አሉ። ስለዚህም ከተጠቀሱት

ስሜቶች ሁሉ ነፃ በመሆን ነገሮችን መተንተን እጅግ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

**(ሀ) ጎረቤት አገሮች ከልማታችን አኳያ ያላቸው ፋይዳ፣**

ከኢኮኖሚያዊ ልማት አኳያ ሲታይ ጎረቤት አገሮች ራሳቸው ከፍተኛ የካፒታልና የፋይናንስ እጥረት ያለባቸው ስለሆኑ የኢንቨስትመንትና የልማት ፋይናንስ ምንጭ ተደርገው የሚወሰዱ አይደሉም፡፡ ከንግድም አንፃር ምርቶቻችን ተመሳሳይ፣ ገበያዎቻችንም ጠባብ በመሆናቸው በአሁኑ ወቅት በልማታችን ላይ ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ አይችሉም፡፡ በርግጥ ያለውን የንግድ ዕድል አሟጠን ስላልተጠቀምን፣ አካባቢው እየለማ ሲሄድ የንግድ ዕድሉ እየጨመረ ስለሚሄድ ከጎረቤት አገሮች ጋር የንግድ ትስስርን ለማጠናከር መጣጣር ያስፈልጋል፡፡ ይሁንና አሁን ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ በምንመለከትበት ወቅት ከኢንቨስትመንት፣ ከልማት ፋይናንስና ከንግድ አኳያ በልማታችን ላይ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ሚና የላቸውም፡፡

ከተፈጥሮ ሃብት አኳያ ሲታይ በውሃ አጠቃቀም ረገድ ከሱዳን፣ ከሶማሊያና ከኬንያ ጋር በተለያየ ደረጃ አለመጣጣም ሊፈጠር ይችላል፡፡ ይሁንና የአፍሪካ ቀንድ አገሮች በውሃው ሃብት የመጠቀም አቅማቸው ውሱን በመሆኑ፣ በዚህ ረገድ አለ የሚባለው የጥቅም ግጭትም በጥልቀት ሲመረመር ጠንካራ መሰረት የሌለው ስለሆነ የጎረቤት አገሮች የውሃ ሃብታችንን በአግባቡ እንዳንጠቀም ከባድ እንቅፋት የሚሆኑ አይደሉም፣ ይህንኑ



በይበልጥ ለመጠቀም የሚያስፈልግ ከፍተኛ እገዛ ሊያደርጉልን የሚችሉ አይደሉም፡፡ ከዚህም አኳያ ሲታይ በአሁኑ ወቅት በልማታችን ላይ ያላቸው በጎም ሆነ አሉታዊ ተፅእኖ በጣም ውሱን እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ጎረቤቶቻችን ባለወደብ እኛ ወደብ አልባ በመሆናችን በኢኮኖሚ እየለማን ስንሄድ በዚያው መጠን ብቃት ያለው አገልግሎት የሚያስፈልገን መሆኑ ሌላው ጉዳይ ነው፡፡ አገሮቹ የወደብ አገልግሎት ለኢትዮጵያ ቢሰጡ ተጠቃሚ የምትሆነው ኢትዮጵያ ብቻ ሳትሆን እነሱም ናቸው፡፡ ይልቁንም አንዳንዶቹ ለኢትዮጵያ የወደብ አገልግሎት ባይሰጡ በኢኮኖሚያቸው ላይ በቀላሉ የማይገመት ችግር የሚፈጠርባቸው ናቸው፡፡ ስለሆነም ከኢኮኖሚና ከጋራ ጥቅም አኳያ ከታየ የወደብ አገልግሎቱ በአስተማማኝ ሁኔታ ሊቀርብ የሚችልና የሚገባው ነው፡፡

በጥቅሉ ሲታይ አገሮቹ በኢኮኖሚያዊ እድገታችን ላይ በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ ግምት ሰላም የሚሰጠው በጎም ሆነ አሉታዊ ተፅእኖ ያላቸው አይደሉም፡፡ በዚህ ረገድ ክብደት የሚሰጠው ጉዳይ ቢኖር የወደብ አገልግሎት ሲሆን አደጋው ሁሉም ተባብረው ለኢትዮጵያ የወደብ አገልግሎት የከለከሉ እንደሆነ ወይም አገልግሎቱ በተለያየ ምክንያት ቀልጣፋ ሳይሆን የቀረ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ እንደዚህ አይነቱ አደጋ ሊከሰት የሚችለውም በኢኮኖሚያዊ አዋጭነት መርህ ሳይሆን በፖለቲካ ግጭቶችና ቅራኔዎች ምክንያት ነው፡፡ ይህ የአሁኑን ነባራዊ ሁኔታ የሚገልፅ ሲሆን ከረጅም ጊዜ አኳያና ጎረቤት አገሮች በልማት እየገሰገሱ

ሲሄዱ ግን ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ገበያ ሊፈጥሩ ይችላሉ፡፡

### (ለ) ጎረቤት አገሮች ከዴሞክራሲያችን ማበብ አኳያ ያላቸው ፋይዳ፣

በአገራችን የዴሞክራሲ ስርአት ስር እንዲሰድ ከማድረግ አኳያ ወሳኙ የውስጥ ሁኔታችንና ትግላችን ቢሆንም የውጭው አለም በጎም ሆነ አሉታዊ አስተዋፅኦ ሊኖረው ይችላል፡፡ ጎረቤቶቻችን ከዴሞክራሲ አኳያ ብዙዎቹ እንደኛው ጀማሪዎች በመሆናቸው፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ገና ወደ ዴሞክራሲ ጎራ ያልተቀላቀሉ በመሆናቸው ለዴሞክራሲ ስርአታችን የሚበጅ የቴክኒክ ድጋፍ በመስጠትም ሆነ የፋይናንስ ድጋፍ በመስጠት ክብደት የሚሰጠው ሚና ይጫወታሉ ተብሎ አይገመትም፡፡

በአሉታዊ ጎኑ ሊጫወቱ የሚችሉት ሚና ግን በቀላሉ የሚገመት አይደለም፡፡ የሃይማኖት አክራሪነትን በማራመድ ወይም የሃይማኖት አክራሪነትን ለሚያራምዱ ክፍሎች መንደርደሪያ በመሆን መንግስትን ከሃይማኖት በመለየትና በሃይማኖቶች መካከል መቻቻልን በመፍጠር ላይ የተመሰረተውን ታዳጊ ዴሞክራሲያችንን ሊፈታተኑት ይችላሉ፡፡ ህዝቦች ተሰባጥረው የሚገኙበት አካባቢ በመሆኑ ከተለያየ አላማ በመነሳት በህዝቦች መፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ ዴሞክራሲያዊ አንድነትን በመፍጠር ላይ የተመሰረተውን ታዳጊ ዴሞክራሲያችንን ሊፈታተኑት ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም ለአደጋ ተጋላጭነታችንን ታሳቢ በማድረግ ከአገራችን ተገቢ ያልሆነ ጥቅምን ለማግኘት፣ ወይም በሌሎች ሃይሎች ተፅእኖ



ስር በመውደቅ ሰላማችንን በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ሊፈታተኑት ይችላሉ፡፡

በጥቅሉ ሲታይ ከረጅም ጊዜ አኳያ አካባቢው ሲለማ ሰፊ የንግድ ዕድል ሊፈጥሩ ቢችሉም ከአጭርና ከመካከለኛ ጊዜ አኳያ ጎረቤት አገሮች በልማታችን ላይ ያላቸው በጎም ሆነ አሉታዊ ተፅእኖ ውሱንና በዋነኛነትም ከወደብ አገልግሎት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ለዴሞክራሲ ስርአት ግንባታችን የሚያበረክቱት በጎ አስተዋፅኦም ውሱን ነው፡፡ በአሉታዊ ገፁ ግን የሃይማኖት አክራሪነትን ጠባብ ብሄርተኝነትን በመጠቀም፣ ለአደጋ ተጋላጭነታችንን ታሳቢ በማድረግ ሰላማችንን ለማወክ ብሎም የልማት የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታችንን በማወክ ከፍተኛ ጉዳት ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡

### (ሐ) የልማትና የዴሞክራሲ አጀንዳችን በአገሮቹ ላይ ያለው ተፅእኖ፣

ሁሉም ነገር ወደ ልማትና ወደ ዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ብለን፣ ከዚህ የሚያዘናጋንን ነገር በሙሉ ወደጎን ትተን፣ ከእብሪትና ከጀብደኝነት ነፃ ሆነን ኑሯችንን በማሻሻል ላይ ለመረባረብ ቆርጠን ተነስተናል፡፡ መላው ህዝባችንም በዚህ ጉዳይ ላይ የጋራ እምነት ይዞ ይረባረባል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ይህንኑ አላማ ለማሳካት የሚያስችለን ትክክለኛ አቅጣጫ ቀይሰናል ብለንም እናምናለን፡፡ ይህ አገራችን ይዛው የምትጓዘው አቅጣጫ አገራችን

በአፍሪካ ቀንድ ከሚኖረው ህዝብ ውስጥ ግማሽ ያህሉን የያዘችና ማዕከላዊ አቀማመጥ ያላት አገር ከመሆንዋ አኳያ በጎረቤት አገሮች ላይ የሚኖረው ፋይዳ በቀላሉ የሚገመት እንደማይሆን ገሀድ ነው፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ አገራችን ሁሉን ነገር ትታ በልማትና በዴሞክራሲ ላይ ስታተኩር በህዝብ ብዛትና በመሬት ቆዳ ስፋት በመተማመን የጀብደኝነት ሰላማቸውን የሚነካ ምንም ነገር ከኢትዮጵያ እንደማይመጣባቸው እርግጠኛ መሆን ይችላሉ፡፡ ይልቁንም ልዩነቶች ሲፈጠሩ በመቻቻል፣ በመደራደርና ሰጥቶ በመቀበል መርህ ለመስራት ኢትዮጵያን ከመቼውም ጊዜ በላይ ዝግጁ ሆና ያገኟታል፡፡ የልማትና የዴሞክራሲ ራዕያችን እውን ሲሆን አገራችን ከውጭም (ከጎረቤት አገሮች ጭምር) ከውስጥም ለሚመጣ ግጭት ተጋላጭነትዋ እንደሚወገድ፣ ግጭቶችን የመግታት ጠንካራ እምነትና ብቃት እንደሚኖራት እርግጠኛ መሆን ይችላሉ፡፡ በሌላ አነጋገር አገራችን በውስጧና በአካባቢዋ ጠንካራ የሰላም መሰረት እንደምትሆን፣ ይህንንም ለማንም ብላ ሳይሆን ለራስዋ፣ ለህዝቧ ጥቅምና ለአላማዋ መሳካት ብላ የምትፈፅመው እንደሚሆን እርግጠኛ መሆን ይችላሉ፡፡ ስለዚህም ኢትዮጵያ የሰላም መሰረትና መናኸሪያ መሆንዋ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ጎረቤት አገሮች ከፍተኛ ጥቅም የሚሰጥ ጉዳይ ነው፡፡

ኢትዮጵያ የያዘችው የልማት አላማ ከተሳካ ብንፈልግም ባንፈልግም ጎረቤት አገሮች ተጠቃሚ መሆናቸው አይቀርም፡፡



ይህ በወደብ አገልግሎት መልኩ ብቻ የሚገለፅ አይሆንም፡፡ የኢኮኖሚያችን እድገት ሲፈጥን ሰፋ ያለ የወደብ አገልግሎት ስለምንገዛ ይህንን የወደብ አገልግሎት የሚሰጡን አገሮች ሁሉ ተጠቃሚ መሆናቸው የማይቀር ነው፡፡ እድገታችን ሲፋጠን ገበያችን መስፋቱ፣ ገበያችን ሲሰፋ ለጎረቤት አገሮች የገበያ ዕድል መፍጠሩ በዚህም ሁላችንም ተጠቃሚ መሆናችን አይቀርም፡፡ በሌላ አነጋገር ለራሳችን ህዝብ ብለን የምናካሂደው የፈጣን ልማት፣ የዴሞክራሲና የሰላም ፖሊሲ ከተሳካ ኢትዮጵያ በአካባቢው ካላት ቦታ አኳያ ሲታይ ሁሉንም የአፍሪካ ቀንድ አገሮች በከፍተኛ ደረጃ መጥቀሙና አካባቢውን በመቀየር ረገድ ከፍተኛ ሚና መጫወቱ አይቀርም፡፡ ይህንኑ ተገንዝበን በአካባቢው መጫወት የሚገባንን በጎ አስተዋፅኦ ለማበርከት የሚያስችል ፖሊሲ ቀርፀን ከተንቀሳቀስን የሚገኘው ውጤት በዚያው መጠን የላቀ ይሆናል፡፡

ከላይ ከተዘረዘሩት ነባራዊ ሃቆች በመነሳትና አጠቃላይ ስትራተጅያችንን መሰረት በማድረግ በአፍሪካ ቀንድ ሊኖረን የሚገባውን አጠቃላይ ፖሊሲ እንደሚከተለው ማስቀመጥ ይቻላል፡፡

በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ የሚኖረንን ፖሊሲ እንደሌሎቹ ፖሊሲዎቻችን ሁሉ በተለያዩ ስሜቶች የሚነዳ ሳይሆንና ከልማትና ዴሞክራሲ አጀንዳችን አይናችንን ለአንድ አፍታም ሳንነቅል በሰከነ አእምሮ ሁኔታዎችን በመተንተን የምንፈፅመው መሆን አለበት፡፡ በዚህ መሰረት የልማትና የዴሞክራሲ አጀንዳችን መሳካቱ አገራችን በአካባቢው ካላት ቦታ አኳያ ሲታይ ለአገራችን ብቻ ሳይሆን

ለሁሉም ጎረቤቶቻችን ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን፣ ይህንኑ ከእብሪትና ከስስት ነፃ በሆነ መንፈስ ከተጠቀምንበት አካባቢውን በሙሉ ለመቀየር ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚያበረክት ታሳቢ ያደረገ ፖሊሲ፣ ይህንኑ ለበጎ አላማ፣ ለልማትና ዴሞክራሲ አላማችን መሳካት በብቃት የሚጠቀም ፖሊሲ መቅረፅ ይኖርብናል:: በሌላ በኩል አገሮቹ በልማታችን ላይ በቀጥታ የሚጫወቱት ከፍተኛ ሚና ባይኖርም፣ በሂደት ሚናቸው እየጨመረ ስለሚሄድና በተለይም ሰላማችንን በማወክ መልኩ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ሚና ሊኖራቸው ስለሚችል ቅራኔዎችን በውይይትና በድርድር የመፍታት ባህል በማዳበርና ተግባራዊ በማድረግ፣ ለአደጋ ተጋላጭነታችንን በማስወገድ በዚህ ረገድ ሊከሰት የሚችለውን ችግር በአስተማማኝ መልኩ ለመቅረፍ የሚያስችለን ፖሊሲ መቅረፅና ተግባራዊ ማድረግ ይኖርብናል::

## 1.2. ኤርትራን በሚመለከት ልንከተለው የሚገባን ፖሊሲ፣

ከጎረቤት አገሮች ሁሉ በታሪክና በባህል ትስስር የጠበቀ ግንኙነት ያለን ከኤርትራ ጋር ነው:: በተመሳሳይ መልኩ በቅርብ አመታት ሁለት ጊዜ የከፋ ጦርነት የተካሄደውም ከኤርትራ ጋር ነው:: ከዚህ በመነሳት የተለያዩ ስሜቶች ከሚጠናወቷቸው ፖሊሲዎች ውስጥ በዋነኛነት ሊጠቀስ የሚችለው በኤርትራ ላይ ያለን ፖሊሲ ነው:: በአንድ በኩል በተለይም ከወደብ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የኤርትራ ነፃነት ያልተዋጠላቸው ወገኖች አሉ:: አንድ ህዝብ ነበርን፣ አንድ ህዝብ መሆን አለብን የሚል ስሜት እየገፋቸው ነገሮችን ከስሜት ነፃ በሆነ አኳኋን ለመመርመር የሚቸገሩ



ወገኖችም አሉ:: ጦርነቶቹ የተውት ጠባሳ እየቆረቆራቸው ህዝቡንና በስልጣን ላይ ያለውን መንግስት መለየት አቅቷቸው ለዘልአለሙ መቆራረጥን የሚመርጡ ወገኖችም ብዙዎች ናቸው:: ሁሉም ኤርትራ በኢኮኖሚ ልማታችንና በዴሞክራሲ ስርአት ግንባታችን ላይ ያላትን ፋይዳ በከፍተኛ ደረጃ ያጋንናሉ:: ነገር ግን ጉዳዩ በጥሞና በሰከነ አእምሮ፣ ሁሉም ነገር ወደልማትና ዴሞክራሲ ከሚል መርህ አኳያ ሲመረመር የተለየ ስእል ነው የሚሰጠው::

### (ሀ) የትስስሩ ፋይዳ፣

ከልማት አንፃር ያየነው እንደሆነ የኤርትራ ገበያ ከአጭርና ከመካከለኛ ጊዜ አኳያ ለልማታችን ያለው ፋይዳ አንፃራዊ በሆነ ሁኔታ ሲታይ ዝቅተኛ ነው:: በኢንቨስትመንትና በልማት ፋይናንስ ረገድም እንዲሁ:: ይሁን እንጂ የኤርትራ ወደቦች በተለይም ለሰሜኑና ለመካከለኛው የአገራችን ክፍል የተሻለ የወደብ አማራጮች ናቸው:: በተመሳሳይ መልኩ ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ሃይል ዕምቅ አቅማችን በዚህ ፀጋ ላልታደለችው ኤርትራ የርካሽ የሃይል ምንጭ የተሻለ አማራጭ ነው:: በተነፃፃሪ ሲታይ ሰፋ ያለው ገበያችንም ለኤርትራ አንድ የማይናቅ ገበያ ነው:: ከዚህ አኳያ ሲታይ መልካም ትስስር መኖሩ ሁለታችንንም በቀላሉ የማይገመት ጥቅም ቢሰጠንም ይህ ትስስር በአጀንዳችን ላይ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ቦታ ያለው አይደለም::

ከዴሞክራሲ አኳያ ከኤርትራ በበጎ ጎኑ የሚገኝ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለ ብሎ ማሰብ አይቻልም:: በአሉታዊ ገፅታው ግን

ሰላማችንን ከማወክ አኳያ ቀላል ግምት የማይሰጠው አደጋ ሊኖር ይችላል። የዚህ አደጋ ምንጭ የኤርትራ ህዝብ አይደለም፣ ወይም በኤርትራና በኢትዮጵያ መካከል በቀላሉ የማይፈታ የጥቅም ግጭት በመኖሩ አይደለም። ችግሩን የፈጠረው በስልጣን ላይ ያለው ቡድን ነው። በተጨማሪም ለአደጋ ተጋላጭ በመሆናችን የተፈጠረ ነው። ለአደጋ ተጋላጭነታችን ሲወገድ ከዚህ አኳያ ሊመጣ የሚችለው አደጋ አስጊ የማይሆንበት ደረጃ ላይ ሊደርስ ይችላል። እዚህ ደረጃ ላይ ለመድረስም ረጅም ጊዜና ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ አይሆንም። በተጨማሪም በስልጣን ላይ ያለው ቡድን ወይም ፖሊሲው ሲቀየር አደጋው ሊደርቅ የሚችል ነው። ስለሆነም በአሉታዊ ገፁ የሚኖረው ተፅእኖ ከአጭር ጊዜ አኳያ ትኩረት የሚጠይቅ ቢሆንም ከመካከለኛና ከረጅም ጊዜ አኳያ የሚደርቅ ወይም ከፍተኛ ወደማይሆንበት ደረጃ የሚወርድ ነው።

ከዚህ በመነሳት በሁለቱ አገሮች መካከል በጋራ ጥቅምና መልካም ጉርብትና ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ለመመስረት ጂኦግራፊያዊና ታሪካዊ ሁኔታው የሚያመች ቢሆንም፣ በኢትዮጵያ በኩል በዋነኛነት በወደብ አጠቃቀም፣ በኤርትራ በኩል በዋነኛነት በገበያ፣ በኤሌክትሪክ ሃይል ወዘተ. ላይ የተመሰረተ ትስስር ሲፈጠር ለሁለቱም አገሮቸ ህዝቦች የጋራ ልማት ጠቃሚ ይሆናል። ሆኖም ግን ከኢትዮጵያ አኳያ ሲታይ እንደዚህ አይነት ትስስር ሳይፈጠር አገሮቹ በጦርነት ውስጥ ሳይገቡ ረጅም ጊዜ ቢቆዩ በመሰረታዊ አላማችን ላይ ይህ ነው የሚባል አሉታዊ ተፅእኖ አያርፍም።



**(ለ) ለመልካም ወዳጅነት እንቅፋት የሆነው ገዥ ቡድን፣**

ለሰላሳ አመታት የተካሄደው ጦርነት አብቅቶ የኢትዮጵያ መንግስት የኤርትራን ነፃነት አምኖ ከተቀበለ በኋላ በሁለቱ አገሮችና ህዝቦች መካከል ሰላም ሰፍኖ፣ ለጋራ ጥቅም ጠንካራ ትስስር መፍጠር ይቻላል የሚል ተስፋ የፈነጠቀበት ወቅት እንደነበር ይታወሳል። ይሁንና ይህ ተስፋ ሻዕቢያ ባካሄደው የእብሪት ወረራና ባስከተለው እልቂት ምክንያት ደብዝዟል። ወረራው ለምን እንደተፈፀመ መረዳት ለቀጣይ ፖሊሲያችን ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ነገር ነው።

በስልጣን ላይ ያለው ቡድን እጅግ ስር የሰደደና የራሱ ታሪካዊ አመጣጥ ያለው ጥገኝነት የተጠናወተው ቡድን ነው። በህገ-ወጥ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ላይ የተንጠለጠለ የኢኮኖሚ አጀንዳ ያለው ቡድን ነው። ይህንኑ ስራ በጎረቤት አገሮች (ኢትዮጵያ፣ ሱዳን፣ ሱኡዲ አረብያ ወዘተ.) ብቻ ሳይወሰን ከምስራቅ አውሮ- እስከ ኮንጎ ድረስ በዘረጋው መረብ አማካኝነት የሚፈፅም ነው። በስልጣን ላይ ያለው ቡድን ይህንን አጀንዳውን በኢትዮጵያ ተግባራዊ ማድረግ እንደማይችል፣ በጋራ ጥቅም ላይ ከተመሰረተና ህጋዊ የኢኮኖሚ ትስስር ውጭ አማራጭ እንደማይኖር ስለተገነዘበ አግባብ ያለሆነ ጥቅም በመፈለግ ነው ጥገኛ አጀንዳውን በኢትዮጵያ ላይ ለመጫን ወረራውን የፈፀመው።

በስልጣን ላይ ያለው ቡድን በትምክህት የታወረ፣ ጀብደኝነት የተጠናወተው ፀረ-ዴሞክራሲ ቡድን መሆኑም

ለወረራው አንድ ምክንያት ሆኗል። ምንም አይነት ግልፅነትና ተጠያቂነት የሌለበት ስርአት በመሆኑ እንደ መንግስት የተደራጀ የኢኮኖሚ ወንጀለኛ ቡድን ሆኖ በመስራት ጥገኛ አጀንዳውንና መረቡን ለማስፋፋት ችሏል። ፀረ-ዴሞክራሲ ባህሪውና ጀብደኝነቱ ተጣምረው የአካባቢው ፖሊስ ነኝ ብሎ እንዲንጠራራ፣ አገሪቱን በሙሉ ወደ ወታደራዊ ካምፕ እንዲቀይር፣ ጎረቤቶችን ሁሉ በሃይል አንበርክካለሁ ብሎ እንዲያምንና እንዳሻው ግጭት እንዲቀሰቅስ አድርጎታል። ትምክህቱ የጎረቤት አገሮች ህዝቦችን በንቀት እንዲመለከታቸውና በጀብደኝነት ተግባር እንዲሰማራ አድርጎታል።

ሻዕቢያ በአገራችን ላይ ወረራ እንዲፈፅም (በሌሎች ጎረቤት አገሮችም ተመሳሳይ ወንጀል እንዲፈፅም) የገፋፋው ጥገኛ አጀንዳው፣ ትምክህቱና ጀብደኝነት ቢሆንም አገራችን በወቅቱ ለአደጋ ተጋላጭ የነበረች መሆንዋም በሃይል ፍላጎቴን ማርካት እችላለሁ የሚል እምነት እንዲያድርበት፣ ስለሆነም ሻዕቢያ ግጭትን ከመቀስቀስ እንዳይገታ ምክንያት ሆኗል። አገራችን በወቅቱ የነበራት የመከላከል አቅም በጣም ደካማ ስለነበረ ሻዕቢያም የኢትዮጵያ ህዝብ በአንድ የጋራ አገራዊ አመለካከት ዙሪያ የተሰባሰበ ስላልሆነ በቀላሉ ይበታተናል የሚል ግምት እንዲያድርበት እነዚህ ሁኔታዎች በር ስለከፈቱለት ወረራውን ለመፈፀም ተደፋፍሯል።

በተግባር እንደታየው ሻዕቢያ በዚህ ረገድ ከፍተኛ የግምገማ ስህተት ፈፅሟል። ይሁንና የሻዕቢያን ወረራ ለመቀልበስም



የከፈልነው ዋጋ በቀላሉ የሚገመት አይደለም። የልማትና የዴሞክራሲ አጀንዳችን ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን በከፍተኛ ደረጃ ተስተጓጉሏል፣ የተከፈለው የህይወት መስዋእትም ቀላል አልነበረም። ለአደጋ ተጋላጭነታችን መቀነስ በምንችለውና በሚገባን ደረጃ ቀንሰን ቢሆን ኑሮ ምናልባት ሻዕቢያ ወረራውን ከመፈፀሙ በፊት ከአንዴም ሁለቴ እንዲያስብ በተገደደ ነበር። ከዚህ አልፎ ወረራውን ቢፈፅምም በልማትና ዴሞክራሲ አጀንዳችን ላይ ያስከተለውን ያህል አደጋ ሳያስከትል መቋቋም በተቻለ ነበር።

የሻዕቢያ ጥገኝነት ትምክህትና ጀብደኝነት በጎረቤት አገሮች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያስከተለ ቢሆንም የነዚህ በሽታዎች ዋነኛው ሰለባ የኤርትራ ህዝብ ነው። የሻዕቢያ ጥገኛ አላማ የኤርትራ ህዝብ ጉልበቱንና እውቀቱን አስተባብሮ አገሩን እንዳያለማ ቀስፎ ይዞታል። በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ከዚህ ይልቅ በተስፈኝነትና በህገ-ወጥ የኢኮኖሚ ተግባር ላይ አተኩሮ የራሱን ካዝና በመሙላት ላይ በማተኮሩ ህዝቡ ከዚሁ ምንም ሳይጠቀም የራሱን የልማት አቅም የሚያጎለብት መንግስት አጥቶ ለችግር ተጋልጧል። ሻዕቢያ በኤርትራም ውስጥ ገቢ የምታስገኘውን ማንኛዋንም ቀዳዳ ራሱ ተቆጣጥሮ እየመጠጠ የኤርትራን ህዝብ እርቃኑን አስቀርቶታል።

የሻዕቢያ ጀብደኝነት የኤርትራን ህዝብ ለማያባራ ጦርነትና እልቂት ዳርጎታል። ሻዕቢያ ኤርትራ ውስጥ በወታደራዊ ዕድሜ ክልል የሚገኝ ዜጋ በሙሉ በውትድርና እንዲጠመድ በማድረግ

ከፍተኛ ማህበራዊ ቀውስ ፈጥሯል፡፡ ከዚህ ለመሸሽ የሚደረግን ሙከራ ሁሉ ሻዕቢያ እያነፈነፈ በመድፈን ህዝቡን እያፈሰ በውትድርና እያሰማራው ነው፡፡ በፀረ-ዴሞክራሲ አገዛዙ ቀጥቅጦ እያሰረው፣ እየገደለውና እያጋዘው ነው፡፡ መብቶቹን ሁሉ ረግጦና አፍኖ ተሸማቆ እንዲኖር አድርጎታል፡፡ የሻዕቢያ ትምክህት ደገኛውን ከቆለኛው፣ ቆለኛውና ደገኛው እርስ በርሳቸው፣ በትጥቅ ትግሎ የተሳተፈውና ያልተሳተፈው እርስ በርሳቸው እንዲናናቁ በመካከላቸው ቁርሾ እንዲፈጠር እያደረገ ነው፡፡

## (ሐ) በኤርትራ ላይ ሊኖረን የሚገባው ፖሊሲ፣

በኤርትራ ላይ የሚኖረን ፖሊሲ መለስተኛና ከፍተኛ ግቦችን ታሳቢ ያደረገና አገራዊ ጥቅማችንን በሰከነ መንፈስ በመመርመር ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት፡፡ መለስተኛው አላማችን ግጭትን ማስወገድ መሆን ይኖርበታል፡፡ ግጭት መፈጠሩ ከዋነኛው አላማችን ያዘናጋናል፡፡ ኤርትራ በዋናው አጀንዳችን ላይ ያላት በጎም ሆነ አሉታዊ ተፅእኖ እጅግ መለስተኛ ሆኖ ሳለ በኤርትራ ምክንያት ከዋናው አላማችን የምንዘናጋበት ምንም ምክንያት ሊኖር አይችልም፡፡ ከኤርትራ ጋር ግጭት ለማስወገድ የሚቻለው በሁለት መልክ ነው፡፡ በአንድ በኩል ለአደጋ ተጋላጭነታችንን ከቀነስንና ይህንኑ ሁሉም እንዲገነዘበው ካደረግን ሻዕቢያ ምንም ፍላጎት ቢኖረው እንደገና ግጭት ቢቀሰቀስ የባሰውን እንደሚላላጥ ተገንዝቦ እጁን እንዲሰበስብ ማድረግ ይቻላል፡፡ ይህ በቁጥጥራችን ስር ያለ ጉዳይ ነው፡፡ ሁለተኛው አማራጭ በስልጣን ላይ ያለው ቡድን ወይም ፖሊሲው ተቀይሮ አደጋው ከምንጩ



የደረቀ እንደሆነ ነው፡፡ ይህ በቁጥጥራችን ስር ያለ ጉዳይ አይደለም፡፡

ከዚህም አኳያ ዋናውን ትኩረታችን ለአደጋ ተጋላጭነታችንን በመቀነስ ግጭትን በማስወገድ ላይ ማድረግ ተገቢ ይሆናል፡፡ በዚህ ረገድ ጠንካራ ቋሚ ሰራዊትና በቂ ተጠባባቂ ሃይል ለመገንባት የተያያዝነውን ስራ በተሳካ ሁኔታ መፈፀም ይኖርብናል፡፡ መላው ህዝብ በጋራ አገራዊ እምነትና አመለካከት እንዲሰባሰብ ለማድረግ የተያያዝነውን ጥረት በተጠናከረ መልኩ መቀጠል ይኖርብናል፡፡ አልጀርስ ላይ የተፈረመው የሰላም ስምምነት በተሟላ አኳኋንና በጥብቅ ተግባራዊ እንዲሆን አበክረን መስራት ይገባናል፡፡ ሻዕቢያ በእብሪት ተወጣጥሮ ጉረቤቶቹን ሁሉ ከመናከስ እንዲቆጠብ የሚያስገድድ አለም አቀፋዊና የአካባቢ የፖለቲካ፣ የዲፕሎማሲና የኢኮኖሚ ተፅእኖ እንዲያርፍበት ማድረግ ይጠበቅበናል፡፡

በዚህ መልኩ ግጭትን አስወግደን በልማትና በዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ላይ አተኩረን ከተረባረብን ከኤርትራ ጋር ጥብቅ የኢኮኖሚ ትስስር ባለመፈጠሩ በአጀንዳችን ላይ የሚያስከትለው ከፍተኛ ተፅእኖ ስለማይኖር ወሳኝ አገራዊ ጥቅማችን ተጠብቆ ለረጅም ጊዜ መቆየት ይቻላል፡፡ ዴሞክራሲያችን ስር እየሰደደ እድገታችን እየተፋጠነ በሄደ ቁጥር ደግሞ ለአደጋ ተጋላጭነታችን ከሻዕቢያም ሆነ ከሌላ አኳያ በከፍተኛ ደረጃ መቀነሱ የማይቀር ነው፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮች መኖራቸው ግን መታሰብ ይኖርበታል። አንዱ ችግር ሻዕቢያ እያስታጠቀና እያሰለጠነ የሚልካቸውን ምንደኞች በተመለከተ ሊነሳ የሚችለው ችግር ነው። ይህ ችግር ወደ ሁለቱ አገሮች ግጭት ቢያመራ በሻዕቢያ ላይ ምንም ያህል ጉዳት ቢደርስ ከአላማችን ለተወሰነም ጊዜ ቢሆን ማዘናጋቱ የማይቀር ነው። ለልማትና ዴሞክራሲያችን የማይታለፍ ማነቆ ባልሆነ ጉዳይ ላይ ከያዝነው መንገድ ወጥተን ወደግጭት በመግባት ከፍተኛ ጉዳት ካልሆነ በስተቀር የምናገኘው ጥቅም የለም። ስለሆነም በኛ ተነሳሽነት ይህ ጉዳይ ወደ ሁለቱ አገሮች ግጭት እንዲያመራ የማድረግ ፖሊሲም ሆነ ተግባር ሊኖረን አይገባም። ከዚያ በመለስ ምንደኞችን ተከታትሎ በመምታት በሻዕቢያ ላይ በአለም አቀፉ ህብረተሰብና በአካባቢው አገሮች ተፅእኖ እንዲያርፍበት በማድረግና የተመጠነ አፀፋዊ መልስ በመስጠት ራሳችንን የመከላከል ፖሊሲና ተግባር ነው ሊኖረን የሚገባው።

በኤርትራ ጉዳይ ላይ የምንከተለው ከፍተኛው ፖሊሲ በስልጣን ላይ ያለው ቡድን ወይም ፖሊሲው ከተቀየረ የምንከተለው ፖሊሲ ነው። ጥገኛ አጀንዳ ተወግዶ የጋራ ጥቅምን በህጋዊ መንገድ በማራመድ ፖሊሲ ከተተካ እብሪት፣ ጀብደኝነትና ትምክህት ተጠያቂነትና ግልፅነት በሰፈነበት ዴሞክራሲ ከተተካ ግጭት ከምንጩ ስለሚደርቅ በእኩልነትና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ መልካም ትብብር መፍጠር ይቻላል፣ ይገባልም። በመጀመሪያ ደረጃ ኢትዮጵያ ከእንደዚህ አይነት ትብብር ተጠቃሚ ስለምትሆን ከዘላቂ ሰላምም ስለምትጠቀም ካስቀመጥነው



አገራዊ ጥቅምና ወሳኝ አገራዊ አጀንዳ ጋር አብሮ የሚሄድና የሚያራምድ በመሆኑ ልንከተለው የሚገባ ነው። በሁለተኛ ደረጃ በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል እንደዚህ አይነት ትስስር መፈጠሩ ለአካባቢው ሰላምና መረጋጋት ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚያበረክት ብሎም መሰረታዊ አገራዊ ጥቅማችንን የሚያራምድ በመሆኑ ልንከተለው የሚገባ ነው። በሶስተኛ ደረጃ ከመሰረታዊ አገራዊ ጥቅማችን ጋር በማይጋጭ አኳኋን ጎረቤት የሆነውን የኤርትራ ህዝብ የሚጠቅም፣ በአካባቢያችን ህዝቦች መካከል ፍቅርና መተሳሰብን የሚፈጥር በመሆኑ ልንከተለው የሚገባ ነው።

እንደዚህ አይነቱ ሁኔታ ሲፈጠር በኛ በኩል ዋናው ጥቅም የወደብ አገልግሎት ነው። ካለፈው ልምድ በመነሳት በሁለቱ አገሮች ብቻ በሚፈፀም ስምምነት ተማምነን ወደቦቹን ልንጠቀምባቸው አንችልም፣ አይገባም። አለም አቀፍ ዋስትና ያለውና የሁለቱን አገሮች ጥቅም በትክክል የሚያስጠብቅ ዘላቂና ለየት ያለ የወደብ አጠቃቀም ስምምነት መፈረም ይኖርብናል። ይህንኑ ለማረጋገጥ የማያስችል የኢኮኖሚ ትስስር መሰረታዊ አገራዊ ጥቅማችንን የማያስጠብቅ ስለሆነ የምንፈልገውም የምንገባበትም አይሆንም። እንደዚህ አይነቱ ስምምነት ባለበት በሁለቱ አገሮች ሰፉ ያለ የንግድ ትስስር እንዲኖር ማድረግ የሁለቱ አገሮች መሰረተ-ልማቶች እንዲተሳሰሩ ማድረግ (መንገድ፣ ስልክ፣ የኤሌክትሪክ ሃይል ወዘተ.) በህዝቦች መካከል ህግን የተከተለ ዝውውርና ትስስር እንዲኖር ማድረግ ተገቢ ይሆናል።

ይህ ሁኔታ ግጭትን በማስወገድ ብቻ ከታጠረ ሁኔታ

ይበልጥ የሁለቱን አገሮች ጥቅም እንደሚያስጠብቅ ስለምናውቅ የምንመርጠው ሁኔታ ነው:: ይሁንና ይህ አማራጭ ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው በኤርትራ ውስጥ መሰረታዊ ፖለቲካዊ ለውጥ ሲመጣ ብቻ ነው:: ይህን የመሰለውን ለውጥ የማምጣት ስራ የኛ አይደለም:: አንደኛ የጎረቤት አገሮችን መንግስታት የመገልበጥ መብት የለንም:: ሁለተኛ ብንፈልግም ወዳልሆነ ቀውስ ያመራን እንደሆነ እንጅ የሚሳካልን አይሆንም:: በመሆኑም ከቁጥጥራችን ውጭ የሆነና በኤርትራ ህዝብ እጅ ያለ ጉዳይ ነው::

የኤርትራ ህዝብ ራሱም ከሻዕቢያ አገዛዝ ተላቆ አካባቢውንም ሻዕቢያ ከሚፈጥረው ትርምስ እንዲያድን እንመኝለታለን:: ከዚያ አልፈን ህዝቡን ተክተን የምንሰራው ጉዳይ ግን የለም፣ ሊኖርም አይችልም:: በመሆኑም ለኤርትራ ሕዝብ መልካሙን ሁሉ እየተመኘን፣ በህዝቦች መካከል መቃቃር ሊፈጥሩ የሚችሉ ነገሮችን እያስወገድን፣ ከዚህ በላይ ለመሄድ የሚያስችል ሁኔታ እስኪፈጠር ድረስ ግጭት በማስወገድ ላይ ያተኮረ ፖሊሲያችንን ተግባራዊ እናደርጋለን:: የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር እንደዚህ አይነቱ ሁኔታ እንደሚፈጠርም እርግጠኛ መሆን እንችላለን::

## 1.3. በሶማሊያ ላይ የሚኖረን ፖሊሲ፣

### (ሀ) የግንኙነቱ ታሪካዊ አመጣጥ፣

ሶማሊያ ነፃ ከወጣችበት ጊዜ ጀምሮ ከአገራችን ጋር



የነበራት ግንኙነት ጤናማ እንዳልነበረ የሚታወቅ ነው፣ በመካከላችን አንድ ጊዜ መለስተኛ ሌላ ጊዜ ደግሞ ከፍተኛ ጦርነት እንደተካሄደ ይታወቃል:: በሶማሊያ በኩል የታላቋ ሶማሊያ መፈክር ከሁሉም ጎረቤቶችዋ ጋር በተለይም ከኢትዮጵያ ጋር ሲያቃቅራት የነበረ ጉዳይ ነው:: ከዚህ ጋር በተያያዘ ሁኔታም ሶማሊያ ሁሉጊዜም ፀረ-ኢትዮጵያ ናቸው ከምትላቸው ወገኖች ጋር ስትሰለፍና የኢትዮጵያን ሰላም ስታውክ ቆይታለች:: በሌላ በኩል ኢትዮጵያ ውስጥ በነበረው የጭቆና ስርአት ምክንያት ኢትዮጵያውያን ሶማሌዎች የሚደርስባቸውን አድልዎና ጭቆና ሲቃወሙ ኖረዋል:: ከዚህ ጋር በተያያዘም ቀላል ቁጥር የሌላቸው ኢትዮጵያውያን ሶማሌዎች የታላቋ ሶማሊያ መፈክር ሰለባ እስከመሆን ደርሰዋል:: ኢትዮጵያ በዚህ ረገድ ከሶማሊያም ሆነ ከሌሎች ለሚመነጭ ስጋት የተጋለጠች ሆና ኖራለች::

ኢትዮጵያ በበኩሏ ይህንን ስጋት ለመቋቋም የተከተለችው አቅጣጫ የኢትዮጵያውያን ሶማሌዎች መብትን በጥብቅ ማክበር፣ በዚህ ላይ በመመስረት ህዝቡ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ወንድሞቹ ጋር በእኩልነትና በመፈቃቀድ እንዲኖር ማድረግ ሳይሆን በተቻለ መጠን ሶማሊያን መበተን ነበር:: በሶማሊያ በተለያዩ ጎሳዎች የነበረውን ቅራኔ ማባባስ ሶማሊያ በኢትዮጵያ ውስጥ እሳት ከለኮሰች እኛም በአፀፋው እንለኩስባት በሚል መርህ የተመራ አካሄድ ነው የነበረው::

በአሁኑ ሰአት ሁኔታዎች በመሰረቱ ተቀያይረዋል:: የታላቋ ሶማሊያ ርዕዮተ-አለም ከስሯል:: ሶማሊያ ከአስር አመት በላይ መንግስት አልባ ሆናለች:: በኢትዮጵያ የህዝቦችን መብት

የሚያስከብር ህገ-መንግስት ተግባራዊ እየሆነ ነው። ኢትዮጵያውያን ሶማሌዎች የእኩልነት መብታቸው ተከብሮላቸው እንደሌላው ህዝብ ሁሉ በመፈቃቀድ ላይ ለተመሰረተ የኢትዮጵያ ህዝቦች አንድነት የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እያደረጉ አዲስ የኢትዮጵያዊነት አመለካከት መንፈስ እየፈጠሩ ነው። በእኩልነት፣ በዴሞክራሲና በጋራ ልማት እንዲሁም በጠንካራ መሰረት ላይ የተመሰረተ ኢትዮጵያዊነትን ከሌላው ህዝብ ጋር በመሆን በመገንባት ላይ ናቸው። በመሆኑም ኢትዮጵያ በታላቋ ሶማሊያ ርዕዮተ-አለም ምክንያት ለአደጋ ያላት ተጋላጭነት በከፍተኛ ደረጃ ቀንሷል፣ ከስሟል።

በሌላ በኩል ደግሞ ሶማሊያ መበታተንዋ ራሱ የፈጠረው ስጋት እየተጠናከረ መጥቷል። በተፈጠረው ቀውስ ምክንያት በሶማሊያ ውስጥ አክራሪነት እየተጠናከረ መጥቷል። ለአክራሪዎችና ሽብርተኞች በመናሃሪያነት ልታገለግል የምትችልበት ሁኔታ ፈጥሯል። የተለያዩ ፀረ-ሰላም ሃይሎች ሶማሊያን እንደመነሻና መመላለሻ ማዕከል እየተጠቀሙ የኢትዮጵያን ሰላም ለማወክ የሚጣጣሩበት ሁኔታ ተፈጥሯል። የሶማሊያ መበታተንና ቀውስ በአገራችን ሰላም ላይ ቀጥተኛ አደጋ ሆኖ ተገኝቷል።

**(ለ) የግንኙነቱ ፋይዳ፣**

ሶማሊያ ለኢትዮጵያ በኢንቨስትመንትና የልማት ፋይናንስ ምንጭነት፣ ወይም ሰፋ ባለ ገበያ መልክ አስተዋፅኦ የምታበረክትበት ሁኔታ አልነበረም፣ አሁንም የለም። በተራዘመ



ሂደት በሶማሊያ ሰላምና መረጋጋት ተፈጥሮ፣ ልማት ተፋጥኖ ቀላል ግምት የማይሰጠው ገበያ የምትሆንበት ዕድል ያለ ቢሆንም ይህ ጉዳይ በአጭርና በመካከለኛ ጊዜ የሚታሰብ አይደለም። ከተፈጥሮ ሃብት አኳያ በሶማሊያ ውስጥ ያሉት ታላላቅ ወንዞች ሁሉም ከኢትዮጵያ የሚፈሱ ናቸው። በሶማሊያ ውስጥ በነዚህ ወንዞች ዙሪያ ቀላል ግምት የማይሰጠው የመስኖ ልማት ስራ ተሰርቶ የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ክፉኛ ተዳክሟል። በሌላ በኩል ደግሞ የአገራችን ልማት እየተፋጠነ ሲሄድ ወንዞቻችንን መገደባችን ለመስኖ ልማት ስራም ማዋላችን የማይቀር ነው። ወንዞች መገደባቸው በሶማሊያ በተደጋጋሚ የሚከሰተውን የጎርፍ መጥለቅለቅ አደጋ የሚያስወግድ በመሆኑ ሁለቱም አገሮች ይጠቀማሉ። በሌላ በኩል እነዚህ ወንዞች በአገራችን በተለይም በሶማሌ ክልል ለመስኖ ልማት ስራ ሊውል የሚችሉና የሚገባቸው በመሆኑ በውሃ አጠቃቀም ረገድ የተወሰነ ቅራኔ ሊፈጥር ይችላል። ይሁንና ይህ ችግር የሁለቱን አገሮችና ህዝቦች ጥቅም በሚያስጠብቅ አኳኋን በማቻቻልና ሰጥቶ በመቀበል መርህ በቀላሉ ሊወገድ የሚችል ነው።

ከላይ ከተጠቀሰው ጉዳይ መገንዘብ እንደምንችለው ሶማሊያ በአገራችን ልማት ላይ ከአጭርና ከመካከለኛ ጊዜ አኳያ ይህ ነው የሚባል በጐም ሆነ መጥፎ ተፅእኖ የላትም። ይሁንና በሶማሊያ ለአገራችን የወደብ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ እጅግ በርካታ ወደቦች አሉ። በታሪክ ለረጅም ጊዜ ለአገራችን የወደብ አገልግሎት ሲሰጥ ከነበረው ከዜይላ ጀምሮ እስከ ኪሲማዩ ድረስ ከሰባት የማያንሱ ለአገራችን የተለያዩ ክፍሎች የወደብ

አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ወደቦች በሶማሊያ ይገኛሉ፡፡ ይህ ለልማታችን ቀላል ያልሆነ አስተዋፅኦ ሊያበርከት የሚችል ሆኖ ሳለ ቀደም ባሉት ጊዜያት በታላቋ ሶማሊያ አባዜና በኢትዮጵያ በነበረው ብሄራዊ ጭቆና ምክንያት ሳይታሰብ የቆየ ሲሆን (በወቅቱ ኢትዮጵያ ወደቦች የነበሯት በመሆኑ ጭምር) በአሁኑ ወቅት ደግሞ ሶማሊያ በመበታተንዋ በወደቦቹ የመጠቀም እድል መንምኖ ይታያል፡፡

ምንም እንኳ በወደቦች የመጠቀም ዕድል ቢፈጠር ሶማሊያ በልማታችን ላይ የሚኖራት ፋይዳ የሚጨምር ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ከዚህ አኳያ የምትጫወተው በጎ ሚና የለም፡፡ በአሉታዊ ገፁ በሶማሊያ መበታተን ምክንያት በአገራችን ሰላምና መረጋጋት ላይ የተፈጠረው ስጋት የሚጠቀስ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ የአካባቢያችንን ገፅታ በማበላሸት የአፍሪካ ቀንድ የብጥብጥ አካባቢ ሆኖ እንዲታይና የውጭ ኢንቨስትመንት የመሳብ ዕድላችን እንዲቀንስ አድርጓል፡፡ በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ አስተማማኝ ሰላምና ጠንካራ ኢኮኖሚያዊ ትስስርም እንዳይኖር አንድ ምክንያት ሆኗል፡፡

### (ሐ) ሶማሊያን በሚመለከት ልንከተለው የሚገባን ፖሊሲ፣

ከሶማሊያ ጋር ያለን ጉርብትና ለልማታችን የተሻለ አስተዋፅኦ ሊያደርግ የሚችለው በሶማሊያ ሰላምና መረጋጋት ሲኖር ነው፡፡ ብጥብጥን፣ ሽብርተኝነትንና አክራሪነትን በመዋጋት በአካባቢያችን ሰላም ሊኖር የሚችለው በዚሁ መስክ ከጎረቤት አገሮች ጋር በአጋርነት የሚሰለፍ መንግስት በሶማሊያ ሲቋቋም



ነው፡፡ እንደዚህ አይነት መንግስት በሶማሊያ መቋቋሙ የታላቋ ሶማሊያን አመለካከት እንደገና ሊቀሰቅስ ይችላል የሚሉ ወገኖች አሉ፡፡ ከዚህ ተነስተው በሶማሊያ ሰላም፣ ዴሞክራሲና ልማት መስፈኑ ኢትዮጵያን ላይጠቅም ይችላል ይላሉ፡፡ ይህ አመለካከት በመሰረቱ እጅግ የተሳሳተና አደገኛ አመለካከት ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ከእንግዲህ አገራችን የህዝቦችዋን አንድነት የምታስጠብቀው፣ ህዝቦች የተለየ አማራጭ እንዳይኖራችው በማድረግ ሳይሆን፣ በእኩልነት ላይ የተመሰረተ የጋራ ልማትንና ዴሞክራሲን ማዕከል ያደረገ አማራጭ፣ ከሁሉም ሌሎች አማራጮች የላቀ መሆኑን እንዲገነዘቡና በተግባርም እንዲያረጋግጡት በማድረግ ነው፡፡

በመሆኑም የኢትዮጵያ ሶማሊዎች የታላቋ ሶማሊያ መፈክር እንደገና ቢነሳም ባይነሳም ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ወንድሞቻቸው ጋር በእኩልነትና በአንድነት መኖርን የሚመርጡበትን ሁኔታ ፈጥረናል፡፡ የያዝነው የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ እየተጠናከረ ሲሄድ ለዚሁ መፈክርም ሆነ ለሌላ ተመሳሳይ መፈክር ተጋላጭነታችን ይከስማል፡፡ በተጨማሪም ይህ መፈክር በቅድሚያ በሶማሊያ ህዝብ ላይ ያስከተለው መዘዝ እጅግ ከፍተኛ ስለሆነ እጅግ የከሰረና እንደገና የማንሰራራቱም ዕድል በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ሊሰመርበት ይገባል፡፡ በአገራችን እየተፈጠረ ባለው ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ሶማሊዎች በሁለቱም አገሮች የመኖራቸው ሃቅ በሁለቱ አገሮች መካከል ጠንካራ ትስስር ለመፍጠር የሚያስችል ድልድይ ከመሆን ውጭ ሁለቱ አገሮች በጥርጣሬ እንዲተያዩ ምክንያት ሊሆን አይችልም፣ አይገባምም፡፡

በአንፃሩ በሶማሊያ ሰላምና ዴሞክራሲ ቢሰፍን በሶማሊያ ወደቦች በሰፊውና በቀጣይነት የመጠቀም ዕድል እናገኛለን። ይህም ለልማታችን በቀላሉ የማይገመት አስተዋፅኦ ይኖረዋል። ከሚቋቋመው መንግስት ጋር በመተባበር ከሶማሊያ የሚመነጩ ፀረ-ሰላም ተግባራትን ለማስወገድ በር ይከፍታል። የወንዞች አጠቃቀም ላይ በጋራ በመስራት ለሁለቱም አገሮች የሚጠቅም የጋራ ልማት ስራ መስራት ይቻላል። በአገራችን የሶማሊ ክልል በሶማሊኛ ቋንቋ የሚካሄዱ የትምህርትና ሌሎች ተግባራትን በመጠቀም በትምህርትና በባህል ጠንካራ ትስስርና መደጋገፍ ለመፍጠር ይቻላል። በሁለቱ አገሮች በወደብና ወንዞች አጠቃቀም፣ በንግድ፣ በባህል ወዘተ. ጠንካራ ትስስር በመፍጠር፣ የሁለቱ አገሮች ህዝቦች ከዚሁ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ ህዝቦቹ ለጥቅማቸው ሲሉ ትስስርን የሚጎዳ ነገር እንዳይኖር በጥብቅ የሚከላከሉበትና የሚቆጣጠሩበት ደረጃ ላይ ማድረስ ይችላል። በዚህም ኢትዮጵያ በቀጥታ ከምታገኘው የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ባሻገር የምስራቅ ድንበርዋ ለመጀመሪያ ጊዜ የስጋት ምንጭ መሆኑ እንዲያቋርጥ በማድረግ በአጠቃላይ ልማቷ በተዘዋዋሪ መንገድ ከፍተኛ ጥቅም ታገኛለች። በመሆኑም በአሁኑ ወቅት በሶማሊያ የሚኖረን ትልቁ አላማ በአገሪቱ መንግሥት እንዲመሠረት፣ የሕግ ልዕልና እንዲረጋገጥና ሰላምና ዴሞክራሲ እንዲሰፍን፣ በዚህ ላይ በመመስረት በሁለቱ አገሮች መካከል ጥብቅ የኢኮኖሚ፣ የባህልና፣ የፖለቲካ ትስስር እንዲኖር ማድረግ ነው።

የኛ ፍላጎትና ፖሊሲ ይህ ቢሆንም በሶማሊያ ሰላምና



ዴሞክራሲ በኛ ጥረት ብቻ እውን ሊሆን አይችልም። በሶማሊያ ሰላምና ዴሞክራሲ ሲሰፍን ተጠቃሚ በመሆናችንና በአካባቢያችን ሰላምና መረጋጋት እንዲሰፍን የበኩላችንን አስተዋፅኦ ማበርከት ስላለብን ባለን አቅም ሁሉ ለሰላም የምንረባረብ ቢሆንም፣ በሶማሊያ ሰላምን የማስፈን ሃላፊነት በዋነኛነት የሶማሊያ ህዝብና የሶማሊያ የፖለቲካ ሃይሎች ነው። ከዚህ በተጨማሪ በሶማሊያ ላይ ተፅእኖ ማሳረፍ የሚችሉ የውጭ ሃይሎችም ተፅእኗቸው በርግጥም በሶማሊያ ሰላምና ዴሞክራሲን ለማስፈን የሚያግዝ እንዲሆን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

ምንም እንኳን በሶማሊያ ሰላምና ዴሞክራሲ አይሰፍንም ብለን ተስፋ መቁረጥ የሚገባን ባይሆንም ባለፉት አስር አመታት የታየው ሂደት አበረታች እንዳልሆነ መገንዘብ ይኖርብናል። አገሪቱ በተለያዩ አካባቢዎች የተከፋፈለች ስትሆን አንዳንዶቹ አካባቢዎች በተነፃፃሪነት የተረጋጉ ሲሆኑ ሌሎቹ በቀጣይ ትርምስ ውስጥ የሚገኙ ናቸው። ከትርምሱ ተጠቃሚ የሆኑ አንዳንድ የሶማሊያ ቡድኖች፣ አንዳንድ ነጋዴዎች፣ አክራሪዎችና ከነዚህ ጋር የተሳሰሩ የውጭ ሃይሎች በሶማሊያ የሚደረጉ የሰላም ሙከራዎችን ሁሉ በአንድ ወይም በሌላ መልክ ለማክሸፍ ቆርጠው የተነሱ ሆነው ይታያሉ። ህዝቡ ሰላምን የሚናፍቅ ቢሆንም የፀረ-ሰላም ሃይሎችን መረብ በጥሶ ለመውጣት የሚችልበት ደረጃ ላይ የደረሰ አይደለም። አለም አቀፉ ማህበረሰብ በሶማሊያ ሰላምን ለማስፈን መልካም ምኞት ቢኖረውም ይህንኑ እውን ለማድረግ መላ አቅሙን ለማረባረብ ዝግጁ ሆኖ አይታይም። እነዚህን በማገናዘብ ሁኔታውን በምንቃኝበት ወቅት በሶማሊያ ያለው አለመረጋጋት አጭር ላልሆነ

ጊዜ ሊቀጥል እንደሚችል መገንዘብ ይኖርብናል፡፡ ስለሆነም ፖሊሲያችን ሰላምና ዴሞክራሲ እንዲሰፍንና በዚያ ላይ የተመሰረተ ትስስር እንዲጠናከር ማድረግን ብቻ ሳይሆን አለመረጋጋቱ ቢቀጥል ልንከተለው የሚገባንን ፖሊሲም የሚያካትት መሆን አለበት፡፡

ምንጊዜም በሶማሊያ ሰላምና ዴሞክራሲ እንዲሰፍን አበክረን መንቀሳቀስ ዋነኛው ፖሊሲያችን ሆኖ ከዚሁ ጋር ተያይዞ አለመረጋጋቱ ቢቀጥል የምንከተለው ፖሊሲ፣ አለመረጋጋቱ በአገራችን፣ በአካባቢያችንና በሶማሊያ ህዝብም ላይ ጭምር የሚያስከትለውን ጉዳት የመቀነስ (ዳሜጅ ሊሚቴሽን) ፖሊሲ መሆን ይኖርበታል፡፡ አለመረጋጋቱን ማስቆም ካልተቻለ የሚኖረን ብቸኛ አማራጭ ጉዳት መቀነስ ብቻ ነው፡፡ ጉዳቱን ለመቀነስ የሚኖሩን ሶስት ዋና ዋና አማራጮች ናቸው፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ በተነፃፃሪ የተረጋጉ፣ ለአክራሪዎችና ለሽብርተኞች መናኸሪያ ያልሆኑ አካባቢዎች ተነፃፃሪ መረጋጋታቸው እንዲቀጥል፣ ስር እንዲሰድ፣ ለከፋ አለመረጋጋት እንዳይጋለጡ ጥረት ማድረግ ይኖርብናል፡፡ በዚህ ረገድ የሚጠቀሱት ሶማሊ-ላንድና ፑንትላንድ በሚል ስም የሚጠሩት አካባቢዎች ናቸው፡፡ ጉዳት በመቀነስ ፖሊሲ ረገድ እነዚህ አካባቢዎች ተረጋግተው እንዲቀጥሉ በኢኮኖሚ፣ በንግድ፣ በትራንስፖርት ወዘተ. ያለው ትስስር የአገራችንና የአካባቢውን ህዝብ ጥቅም በሚያስጠብቅ አኳኋን እንዲቀጥል ማድረግ ይገባል፡፡ በተለይም ሶማሊላንድን በነፃ መንግስትነት የመቀበል ጉዳይ የሚነሳ ቢሆንም በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ ጀማሪ ብትሆን በሌሎቹ የሶማሊያ



ህዝቦች ላይ የሚፈጥረው ስሜት መጥፎ ሊሆን ስለሚችልና የኢትዮጵያ አላማ በጥርጣሬ አይን መታየቱ ስለማይቀር የሚመረጥ አይሆንም፡፡ ስለሆነም ከነዚህ አካባቢዎች ጋር የሚኖረን ትብብር መስተዳድሮቹን በነፃ መንግስትነት ከመቀበል በመለስ ባለ ደረጃ መገደብ ይኖርበታል፡፡ ይህ ሆኖ ግን በአካባቢዎቹ መረጋጋቱ እንዲቀጥልና ስር እንዲሰድ ማድረግ ጥቅማችንና የአካባቢውን ህዝቦች ጥቅም የሚያስጠብቅ ስለሆነ አጠንክረን ልንገፋበት ይገባናል፡፡

በመላ ሶማሊያ ሰላምና ዴሞክራሲ እስካልሰፈነ ድረስ ለተለያዩ አደጋዎች መጋለጣችን አይቀርም፡፡ ስለሆነም ይህንኑ ተገንዝበን ከሶማሊያ የሚመነጩ የአክራሪዎችን የሽብርተኞችንና የተለያዩ ፀረ-ሰላም ሃይሎችን ጥቃት ለመከላከልና ለማምከን የሚያስችለንን ብቃት መፍጠር አለብን፡፡ ከዚህ አኳያም ሁሉጊዜም በተጠንቀቅ ሆነን መጠባበቅ አለብን፡፡

በሶስተኛ ደረጃ ከየትኛውም የሶማሊያ አካባቢ እየተነሱ በአገራችን ላይ ጥቃት የሚፈፅሙ ክፍሎችን ለማዳከምና ለመቆጣጠር ከአካባቢው የሶማሊያ ህዝብ ጋርና ከአለም ህብረተሰብ ጋር በመተባበር መስራት ይኖርብናል፡፡ የዚሁ ሁሉ መፍትሄ ሰላምና ዴሞክራሲ መሆኑን ተገንዝበን ያለመታከት ከምናደርገው ጥረት ጎን ለጎን የሶማሊያ ህዝብና የአለም ህብረተሰብ በዚህ ረገድ እያጋጠመን ያለውን ችግር እንዲገነዘብልንና ችግሩን በመቋቋም ረገድ እንዲተባበረን ጥረት ማድረግ ይኖርብናል፡፡ በሶማሊያ የውስጥ ጉዳይ ላይ ጣልቃ ያለመግባት መርህ

እንደተጠበቀ ሆኖ ሰላማችንን የማስከበርና ጥቃት የመከላከል መብታችን ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ ይኖርብናል፡፡

## 1.4. ሱዳንን በሚመለከት ልንከተለው የሚገባን ፖሊሲ፣

### (ሀ) የግንኙነቱ ታሪካዊ አመጣጥ፣

ከሱዳን ጋር በአክሱምና ከመርዌ ነገስታት ጀምሮ ለብዙ አመታት የቆየ ታሪካዊ ትስስር እንዳለን ይታወቃል፡፡ የቆየ የህዝቦች ትስስር እንዳለንና በሁለቱም አገሮች ተሰባጥረው የሚኖሩ ህዝቦች እንዳሉም ይታወቃል፡፡ ይህ የረጅም ጊዜ ግንኙነት የራሱ በጎም ሆነ አሉታዊ ገፅታዎች እንደነበሩት ግልፅ ነው፡፡ በተለይም ከሁለተኛው አለም ጦርነት በኋላ ሱዳን ነፃ ከወጣች ጀምሮ ግንኙነቱ መዳበር በሚገባው ደረጃ ሳይዳብር ቆይቷል፡፡

ለዚህ ችግር አንዱ ምክንያት የሃይማኖት አክራሪነት ነው፡፡ በሱዳን አልፎ አልፎ የሚከሰቱ የሃይማኖት አክራሪነት አዝማሚያዎች የሚጎዱት በዋነኛነት የሱዳንን ህዝብ ቢሆንም በኢትዮጵያና በሱዳን መካከል ያለውን ግንኙነት ሲያሻክሩም ኖረዋል፡፡ በአገራችን የሃይማኖት አክራሪነት እንዲስፋፋ የተለያዩ ጥረቶች ከማድረግ አልፈው በሱዳን ድጋፍ አገራችን የአሸባሪዎች ሰለባ እንድትሆን እስከማድረግ የደረሰ ሁኔታም ተከስቷል፡፡

ምንም እንኳ በአገራችን ለረጅም ጊዜ የሃይማኖት መቻቻል ሰፍኖ የነበረ በመሆኑና ከዚህም አኳያ ለአክራሪነት የሚሆን ፖለቲካዊ መሰረት ባለመኖሩና በሱዳን በኩል ከሃይማኖት



አኳያ የተቃጡ ሙከራዎች ያስከተሉት ጉዳት መለስተኛ ቢሆንም በዚህ ረገድ በኢትዮጵያ የነበረው ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለአደጋ ሊያጋልጠን የሚችልና በተወሰነ ደረጃም ያጋለጠን እንደነበር እሙን ነው፡፡ ድህነቱ፣ የሃይማኖት እኩልነት በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ አለመሆኑ አገራችንን ለአደጋ እንደሚያጋልጣት የሚካድ አይደለም፡፡ የሃይማኖት እኩልነት በተሟላ አኳኋን ተግባራዊ ለማድረግ፣ ትምህርትና ስልጣኔን ለማስፋፋት ድህነትን ለመቅረፍ የምናደርገው ርብርብ አገራችንን ከዚሁ አደጋ በአስተማማኝ ሁኔታ ነፃ እንደሚያደርጋት የሚታመን ቢሆንም አሁን በዚሁ ደረጃ ላይ እንገኛለን ማለት አይቻልም፡፡ በመሆኑም በከፍተኛ ደረጃ የቀነሰ ግን ሙሉ በሙሉ ያልተወገደ ተጋላጭነት እንዳለን ሊሰመርበት ይገባል፡፡

ለግንኙነት መሻከር አንድ ትልቅ ምክንያት የነበረው የአባይ ወንዝ ውሃ አጠቃቀም ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ሱዳን ከግብፅ ጋር በመሆን እንደ አውሮ-ውያን አቆጣጠር በ1959 አ.ም የተፈራረመችውና ኢትዮጵያን ከተጠቃሚነት የሚያገል ስምምነት በምሳሌነት የሚጠቀስ ነው፡፡ የአባይን ውሃ ከማመንጨት አኳያ ከዋናው ኢትዮጵያ ብትሆንም ከኢትዮጵያ ቀጥሎ የምታመነጨው ሱዳን ነች፡፡ ውሃውን በማመንጨት ረገድ ምንም ሚና የሌላት ግብፅ ነች፡፡ የአባይን ውሃ ለመስኖ ልማት ከመጠቀም አኳያ ኢትዮጵያ ያላት ዕድል ውሱን ነው፡፡ በአባይ ተፋሰስ ያሉትን በመስኖ ሊለሙ የሚችሉትን መሬቶች በሙሉ ብናለማም የመሬቱ አቀማመጥና ስፋት ራሱ ውሱን በመሆኑ ይህን ያህል ከፍተኛ የውሃ መጠን የሚጠይቅ አይደለም፡፡ በአንፃሩ ሱዳን

እጅግ በጣም ሰፊ ለምና በመስኖ ሊለማ የሚችል የተንጣለለ ሜዳ ያለት በመሆንዋና በዚህ ረገድ ከግብፅም ከኢትዮጵያም የላቀች ስለሆነች ዋነኛ ተጠቃሚ ልትሆን የምትችል ነች፡፡

ግብፅ ምንም ውሃ የማታመነጭ፣ በትክክለኛ የመስኖ ልማት መርህ ብትሄድም ይህን ያህል ሰፊ የሚባል በመስኖ የሚለማ መሬት የሌላት ናት፡፡ እ.ኤ.አ. በ1959 አ.ም ስምምነት ግን እጅግ ወሳኝ የሆነውን የአባይ ውሃ የመጠቀም መብት ወስዳለች፡፡ ኢትዮጵያ ዋናዋ የውሃው ምንጭ ሆና ነገር ግን በዚሁ ሊለማ የሚችል ሰፊ የመስኖ መሬት የሌላት ናት፡፡ የላቀ ስፋት ያለው የመስኖ መሬት ያላት ሱዳን ስትሆን ከግብፅ ጋር ባደረገችው ስምምነት የሚሰጣት ውሱን ነው፡፡ ስለሆነም የሱዳን ብሄራዊ ጥቅም በ1959 አ.ም ስምምነት አይጠበቅም፡፡ የሱዳን ጥቅም የሚጠበቀው በሱዳን፣ በግብፅና በኢትዮጵያ መካከል ፍትሃዊ የውሃ አጠቃቀም ስምምነት ሲኖር ነው፡፡ በዚህ ረገድ ፍትሃዊ ክፍፍል ከመጣም አስቸጋሪ የሚሆነው የኢትዮጵያንና የሱዳንን ጥቅም ማጣጣም ሳይሆን የግብፅንና የሱዳንን ጥቅም ማጣጣም ነው፡፡ ሃቁ ይህ ሆኖ ሳለ በተግባር ግን ሱዳን የግብፅን አቋም ደግፋ ኖራለች፡፡ በስህተት ጥቅሟ በኢትዮጵያ የሚነካ አድርጋ ስትቆጥር ኖራለች፡፡ ይህ አስተሳሰብ በአሁኑ ወቅት በከፍተኛ ደረጃ እየተቀየረ ቢመጣም ሙሉ በሙሉ ተወግዷል ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ለረጅም ጊዜም ለግንኙነቶች አለመጠናከር ምክንያት ሆኖ ቆይቷል፡፡

ሌላው ለግንኙነታችን መሻከር ምክንያት ሆኖ የቆየው



በአንድ በኩል ሱዳን ከራስዋ ምክንያት በመነሳትና በሌሎች ወገኖች በመገፋፋት የኢትዮጵያን ሰላም የሚያውኩ የተለያዩ ተቃዋሚ ሃይሎችን ስትደግፍ የነበረች ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ኢትዮጵያም አፀፋውን በመመለስ መርህ የሱዳን ተቃዋሚዎችን በተለይም በደቡብ ሱዳን የተፈጠረ ተቃዋሚዎችን ስትደግፍ ቆይታለች፡፡ ሁለቱ አገሮች የየራሳቸውን ችግር ከምንጩ ባላደረቁበት ሁኔታ አንዱ ሌላውን በአይነ ቁራኛ የሚመለከትበት ሁኔታ ሲፈጥር ቆይቷል፡፡

**(ለ) የግንኙነት ፋይዳ፣**

ሱዳን ከኢትዮጵያ ቀጥሎ በአፍሪካ ቀንድ የበዛ ህዝብ ያላት አገር ናት፡፡ ከፍተኛ የተፈጥሮ ሃብት ያላትና በይበልጥ ለመልማት የምትችል አገር ከመሆንዋም ባሻገር በአሁኑ ወቅትም የነፍስ-ወከፍ ገቢዋ ከኢትዮጵያ የላቀ ነው፡፡ ስለሆነም አሁንም ቀላል ግምት የማይሰጠው ስፋት ያለው ገበያ ያላት ስትሆን በቀጣይም ከገበያ አንፃር በአፍሪካ ቀንድ ካሉት አገሮች ሁሉ የላቀ ትርጉም የሚኖራት አገር ነች፡፡ በዚህ መልኩ ሲታይ ሱዳን ከገበያ አኳያ ለልማታችን ቀላል ግምት የማይሰጠው ፋይዳ ያላት አገር ነች፡፡ ይህንን የገበያ ዕድል መጠቀም ለእድገታችን መፋጠን የሚኖረው አስተዋፅኦ በቀላሉ የሚገመት አይደለም፡፡ ይህን ያህል ከፍተኛ ነው ባይባልም በኢንቨስትመንት ረገድም የተወሰነ አስተዋፅኦ ሊኖር ይችላል፡፡

የሱዳን ወደብ ለተወሰኑ የአገራችን ክፍሎች በአማራጭነት ሊያገለግል ይችላል። በተመሳሳይ መልኩ በአባይ ውሃ አጠቃቀም ረገድ ሱዳን ገንቢ ሚና ልትጫወት ትችላለች፣ በዚህ ሂደት ኢትዮጵያ ያላትን ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ሃይል እምቅ ሃብት ጥቅም ላይ በማዋል ይህንኑ አገልግሎት ለሱዳን በመስጠት በከፍተኛ ደረጃ ተጠቃሚ መሆን ትችላለች። በድምር ሲታይ ከኢኮኖሚያዊ ልማታችን አኳያ ሲታይ በአፍሪካ ቀንድ ካሉት አገሮች ሁሉ የበለጠ ሚና ከአጭር ከመካከለኛና ከረጅም ጊዜ አኳያ መጫወት የምትችለው ሱዳን ነች። አገራዊ ጥቅማችንን ከማስጠበቅ አኳያ ሲታይ ለዚሁ ግንኙነት መዳበር የላቀ ትኩረት መስጠት ይኖርብናል።

የአፍሪካ ቀንድ ሰላምና መረጋጋት ከማረጋገጥም አኳያ በሱዳን አስተማማኝና ዘላቂ ሰላም መኖሩ፣ ሁለቱ አገሮች በአይነ ቁራኛ መተያየታቸው ቀርቶ በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካዊና በዲፕሎማሲያዊ መስክ ጠንካራ ትስስር መፈጠሩ እጅግ በጣም ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ነው። በኢትዮጵያና በሱዳን መካከል ጠንካራ ትስስር ቢፈጠር የመላውን የአፍሪካ ቀንድ ትስስርና ሰላም ለማጠናከር ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል።

### (ሐ) ሱዳንን በሚመለከት ልንከተለው የሚገባን ፖሊሲ፣

ከራሳችን ኢኮኖሚያዊ ልማት አጀንዳ፣ ከአካባቢያችን ሰላምና መረጋጋት፣ በአጭሩ ከልማታችንና ከደህንነታችን መሰረታዊ አገራዊ ጥቅም አኳያ ሲታይ በአፍሪካ ቀንድ የላቀ ትኩረት ልንሰጠው የሚገባን በኢትዮጵያና በሱዳን መካከል ላለው



ግንኙነት ነው። ይሁንና በሁለቱ አገሮች መካከል ጠንካራ ትስስር እንዳይፈጠር እንቅፋት ሆነው የነበሩ ጉዳዮች በከፍተኛ ደረጃ ቢቃለሉም ሙሉ በሙሉ ያልተወገዱ መሆናቸውና በቀጣይም ይብዛም ይነስም እንቅፋት ሊሆኑ እንደሚችሉ ታሳቢ መሆን አለበት።

አንዱ ችግር ኢትዮጵያ ከሱዳንም ሆነ ከሌሎች ጎረቤቶች ሊመጡ ለሚችሉ ስጋቶች የተጋለጠች ሆኖ መቆየቷና ከዚህ ጋር ተያይዞም ሱዳንንና ሌሎች ጎረቤቶቿን በጥርጣሬ ስትመለከት መቆየቷ ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞም በብዙ ኢትዮጵያውያን ዘንድ ስለግንኙነቱ ያለው አመለካከት የተዛባና ጥርጣሬ የተቀላቀለበት መሆኑ ነው። ከሱዳን ጋር ያለንን ግንኙነት ለማሻሻል ብለን ሳይሆን የልማትና የዴሞክራሲ አጀንዳችንን እውን ለማድረግ ብለን በውስጣችን ሰፊ ስራ እየሰራን ነው፣ ከወዲሁም አበረታች ውጤቶች እየታዩ ነው። የውስጣችን ሁኔታ እየተጠናከረ ሲሄድ በሃይማኖትም ሆነ በሌላ ሰበብ በአገራችን ላይ የሚቃጣ ጥቃትን የሚያስተናግድ የውስጥ ሁኔታ ስለማይኖር ስጋቱ በመሰረቱ ሊወገድ ይችላል። ዋናውን ትኩረታችን በዚህ ላይ በማድረግ ለአደጋ ተጋላጭነታችንን ለማስወገድ በራሳችን በመተማመን ከጎረቤት አገሮች ጋር በተለይም ከሱዳን ጋር ጠንካራ ግንኙነትን የመመስረት ፖሊሲ ልንከተል ይገባል።

ሌላው ችግር የሱዳን የውስጧ ችግር ነው። በሱዳን የሚኖር አክራሪነትና ፀረ-ዴሞክራሲ ራስዋን ሱዳንን ለከፍተኛ ብጥብጥና ቀውስ እንደሚዳርጋት በተግባር ተረጋግጧል። በአሁኑ

ወቅት የሱዳን ህዝብ ይህንኑ ሃቅ በሚገባ የሚገነዘብበት ደረጃ ላይ እየደረሰ ነው፡፡ አክራሪነትና ፀረ-ዴሞክራሲ ከጥፋትና ብጥብጥ ውጭ የሚፈይደው ነገር እንደሌለ ህዝቡ እየተገነዘበ በሱዳን ዴሞክራሲን በማስፈን፣ የሱዳን ህዝቦች በመፈቃቀድና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አንድነት እንዲፈጠር ጥረት እያደረገ ነው፡፡ የደቡብ ሱዳንን ችግር ከላይ በተጠቀሱት መርሆዎች መሰረት ለመፍታት እየተደረገ ያለው ጥረት የዚሁ አዝማሚያ ውጤት ነው፡፡

በሱዳን ሰላምና በዴሞክራሲ ላይ የተመሰረተ አንድነት መስፈኑ ለኢትዮጵያና ለአካባቢያችን ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ነው፡፡ በሱዳን ውስጥ ዴሞክራሲና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አንድነት ሲፈጠር ሱዳን የአክራሪነትና የፀረ-ሰላም መናኸሪያ መሆንዋ አብሮ ማክተሙ ስለሆነም ከሱዳን የሚመነጨው የአገራችን ስጋት ከምንጩ መድረቁ የማይቀር ነው፡፡ በሱዳን ሰላም፣ ዴሞክራሲና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አንድነት ማስፈኑ የሱዳን ህዝብ ተልዕኮ ቢሆንም እኛም ከዚሁ ተጠቃሚ በመሆናችን በሱዳን ጉዳይ ላይ ጣልቃ ያለመግባት መርህ እንደተጠበቀ ሆኖ አላማውን ባለን አቅም ሁሉ የመደገፍ ፖሊሲ መከተል አለብን፡፡

በአባይ ውሃ አጠቃቀም ጉዳይ ላይ ሱዳን አሁንም ከነበረው አስተሳሰብ ሙሉ በሙሉ ተላቃ ፍትሃዊ የውሃ ክፍፍል እንዲኖር አጠንክራ የምትገፋበት ደረጃ ላይ ደርሳለች ማለት አይቻልም፡፡ ይህም በሁለቱ አገሮች ግንኙነት ላይ የራሱ ተፅእኖ እንደሚኖረው የሚካድ አይሆንም፡፡ ይሁንና ሱዳን ኢትዮጵያ



በአባይ ውሃ ፍትሃዊ በሆነ አኳኋን እንዳትጠቀም ከፍተኛ እንቅፋት ሆና የቆየችም አልነበረችም፣ በዚህ ረገድም የተወሰነ መሻሻል ከመታየቱ በስተቀር የታየ ለውጥ የለም፡፡ ስለሆነም የአባይ ጉዳይ በሁለቱ አገሮች ጠንካራ ትስስር እንዳይፈጠር የማይታለፍ ማነቆ ነው ብሎ መውሰድ አይቻልም፡፡ በመሆኑም በአንድ በኩል ሱዳን በአባይ ውሃ ጉዳይ ላይ ፍትሃዊ የክፍፍል ስርአትን እንድትደግፍ ጥረት እያደረግን በሌላ በኩል ደግሞ ይህ እስኪሆን ሳንጠብቅ በሁለቱ አገሮች ጠንካራ ትስስር እንዲኖር የመደገፍ ፖሊሲ መከተል አለብን፡፡

ከዚህ በመነሳት በሁለቱ አገሮች መካከል ጠንካራ የኢኮኖሚ ትስስር ለመፍጠር የሚያስችል የመሰረተ-ልማት ትስስር (መንገድ፣ በሂደትም የባቡር መንገድ፣ የስልክ፣ የኤሌክትሪክ ሃይልና የመሳሰሉት አውታሮች እንዲዘረጉ) እንዲጠናከር በዚህ ላይ ተመስርቶ ጠንካራ የንግድ ትስስር እንዲፈጠር መረባረብ አለብን፡፡ በህዝቦቹና በመንግስታቱ መካከል የጋራ ጥቅምን ለማራመድና የጋራ ራዕይን ለመፍጠር አበርትተን መስራት አለብን፡፡

የግንኙነቱን በጎ ገፅታ አይተን ይህንኑ ለማጠናከር ቅድሚያ ሰጥተን መረባረብ ያለብን ቢሆንም እኛ በፈለግነውና በምንመኘው መልክ ይፈፀማል ብለን እርግጠኛ መሆን አንችልም፡፡ ግንኙነቱ ባስቀመጥነው አቅጣጫ እንዳይሄድ እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ወገኖች በሱዳንም በውጭም እንደሚኖሩ መገንዘብ አለብን፡፡ ከዚህ በመነሳትም ለአደጋ ተጋላጭነታችንን እያስወገድን ፖሊሲያችን ከሱዳን ሁኔታና ከሱዳን መንግስት ምላሽ ጋር ተጣጥሞ እንዲሄድ

ማድረግ ይኖርብናል::

## 1.5. በጅቡቲ ላይ የሚኖረን ፖሊሲ፣

### (ሀ) የግንኙነቱ ታሪካዊ አመጣጥ፣

ጅቡቲ በፈረንሳይ ቅኝ አገዛዝ ስር ከገባችበትና ዘመናዊ ወደብ ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ በኢትዮጵያና ጅቡቲ መካከል ጠንካራ የኢኮኖሚ ትስስር ለመፍጠር ጥረት ተደርጓል:: በአገራችን ብቸኛው የባቡር መስመር አዲስ አበባን ከጅቡቲ ጋር የሚያገናኘው ነው:: መስመሩ የተዘረጋው በወቅቱ ጅቡቲ ለኢትዮጵያ ዋነኛ መውጫ በር (በወቅቱ ኢትዮጵያ ወደብ አልባ ስለነበረች) ትሆናለች ተብሎ ታስቦ ነው:: የጅቡቲ መቆርቆር ራሱ ለኢትዮጵያ የወደብ አገልግሎት በመስጠት ላይ የተመሰረተ ነው የነበረው:: ከዚህም ባሻገር በሁለቱ አገሮች በቋንቋም በባህልም አንድ የሆኑ ህዝቦች ይገኛሉ:: ገና ከአመሰራረቱ ጀምሮ ሁለቱ አገሮች በጥብቅ እንዲተሳሰሩና እንዲቆራኙ ታሪክ የፈረደላቸው ናቸው ሊባል ይችላል::

በሁለቱ አገሮች መካከል አልፎ አልፎ የሚታዩ መለስተኛ ቅራኔዎች ከመኖራቸው ውጭ ዘላቂ ቁርሾ የሚተው ግጭት ውስጥ ገብተው አያውቁም:: በዚህ ረገድ ችግሩ በሁለቱ አገሮች መካከል ያለው ትስስር አሁን ካለው እጅግ የጠነከረና ጤናማ መሆን ሲችልና ሲገባው በተለያዩ ምክንያቶች መሆን የሚገባው ደረጃ ላይ አለመድረሱ ነው::



### (ለ) የግንኙነቱ ፋይዳ፣

ከኢትዮጵያ አኳያ የግንኙነቱ ዋነኛ ፋይዳ ከወደብ አጠቃቀም ጋር የተያያዘ ነው:: ወደቡ ከአመሰራረቱ ጀምሮ ለኢትዮጵያ አገልግሎት እንዲሰጥ ተብሎ የተመሰረተ በመሆኑ፣ ለብዙዎቹ የአገራችን አካባቢዎች የቀረበ በመሆኑ፣ የወደብ አገልግሎት ሊሰጡት ከሚችሉት ጎረቤቶች ሁሉ ወደብ አገልግሎት በመስጠት በበለጠ የሚጠቀም አገር በመሆኑና ከአገራችን ጋር ቁርሾ የሌለው አገር በመሆኑ ዋነኛ የወደብ በራችን መሆን የሚችል ነው:: ይህ በሌሎች ወደቦች የመጠቀም አስፈላጊነትን የማያስቀር ቢሆንም በልማታችን ላይ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ግንኙነት እንዲሆን ያደርገዋል::

ከጅቡቲ አኳያ የወደብ አገልግሎት መስጠቱ ራሱ ለኢኮኖሚው ትልቅ ግምት የሚሰጠው ጉዳይ ነው:: ወደቡ የጅቡቲ ዋነኛ የገቢ ምንጭ ነው:: የአገራችን ልማት እየተፋጠነ ሲሄድ በወደቡ የሚገባውና የሚወጣው እቃ መጨመሩ አይቀርም:: በዚያው መጠንም ጅቡቲ ከወደብ አገልግሎቱ በይበልጥ ተጠቃሚ እየሆነች እንደምትሄድ እሙን ነው:: ከዚህ ባሻገር ኢትዮጵያ ለጅቡቲ ከፍተኛ ገበያ መሆን ትችላለች:: በጅቡቲ የኤሌክትሪክና ሌሎች መሰረታዊ አገልግሎቶችን መስጠት ትችላለች:: በመሆኑም ከጅቡቲ ኢኮኖሚያዊ ጥቅምና ልማት አኳያ ኢትዮጵያ የላቀ ሚና መጫወት ትችላለች::

### (ሐ) የግንኙነቱ ችግሮች፣

በአገሮቹ መካከል መሰረታዊ ቁርሾ የሚፈጥሩ ባይሆኑም ግንኙነቱ በሚፈለገው መጠን እንዳይዳብር እንቅፋት የሚሆኑ ችግሮች እንዳሉ የሚካድ አይደለም፡፡ ችግሮቹ ክብደታቸው የሚለያይ ቢሆንም በሁለቱም አገሮች ያሉ ናቸው፡፡

ከጅቡቲ አኳያ ዋናው ችግር የጋራ ጥቅምን በማስተናገድ፣ የአጭር ጊዜና ዘላቂ ጥቅምን በማጣጣም ረገድ ያሉ ችግሮች ናቸው፡፡ ምንም እንኳ ህዝቡና መሪዎቹ ጅቡቲ ለኢትዮጵያ ዘላቂና አስተማማኝ የወደብ አገልግሎት መስጠት እንዳለበት፣ ይህንን ማድረግ ካልቻለች ዋነኛ የገቢ ምንጯ እንደሚደርቅ የሚገነዘቡና ለኢትዮጵያ በጎ አመለካከት ያላቸው ቢሆንም አልፎ አልፎ የአጭር ጊዜ ጥቅምን የማየት አዝማሚያ በአንዳንድ ሃላፊዎች ይታያል፡፡ የወደብ አገልግሎት በተመጣጣኝ ዋጋ በመስጠት ከኢትዮጵያ ልማት እያደገ የሚሄድ ጥቅም ከማግኘት ይልቅ በአጭር ጊዜ የላቀ ጥቅምን የመፈለግ አዝማሚያ አልፎ አልፎ ይታያል፡፡ በወደብ አጠቃቀም ረገድ ኢትዮጵያ ዘላቂና አስተማማኝ ዋስትና ማግኘት እንደሚገባት ተገንዝቦ ይህንን ከማስተናገድ ይልቅ ሌሎች አማራጮችን የማየት አዝማሚያም ይከሰታል፡፡ ይህ ችግር ወደቡን ለሁለቱም አገሮች የጋራና ዘላቂ ጥቅም የማዋል ዕድልን የሚቀንስና የጥርጣሬ ዘሮችን የሚዘራ ሆኖ ይገኛል፡፡

በሌላ በኩል ተራው የጅቡቲ ህዝብ በወደብ አገልግሎቱ በቀጥታ ተጠቃሚ ስለማይሆን የሚፈጠር ችግር አለ፡፡ በርግጥ መንግስት ከወደብ አገልግሎቱ ጋር በተያያዘ የሚያገኛቸው የተለያዩ ገቢዎች፣ በወደቡ ተቀጥረው የሚሰሩ ሰራተኞች ወዘተ.



በተዘዋዋሪ መንገድ ህዝቡ ከወደቡ ተጠቃሚ እንዲሆን እያደረገው ነው ሊባል ይችላል፡፡ ይሁንና ህዝቡ በኢትዮጵያ ከሚካሄደው ልማት በይበልጥ ተጠቃሚ የሚሆነውና ከዚህ በመነሳትም ለዚሁ ግንኙነት መዳበር ጠንካራ ዘብ የሚሆነው በንግድና ኢንቨስትመንትም ጭምር ተጠቃሚ ሲሆን ነው፡፡ ለምሳሌ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ከኢትዮጵያ በርካሽ ዋጋ ማግኘት ሲችል ይህ አለመሆኑ፣ የመጠጥ ውሃ ችግሩን ለመቅረፍ በኢትዮጵያ በኩል መፍትሄ ሊፈተሽ ሲችል ይህ አለመሆኑ፣ የጅቡቲ ዜጎች በኢትዮጵያ የተለያየ መለስተኛ የንግድና ኢንቨስትመንት ስራ ላይ ሊሳተፉ ሲችሉ ይህ አለመሆኑ ወዘተ. ህዝቡ ከትስስሩ በሚፈለገው ደረጃ ተጠቃሚ ሳይሆን ይቀራል፡፡ በመሆኑም ህዝቡ በሚገባው ደረጃ የትስስሩ ጠንካራ መሰረት ሳይሆን ይቀራል፡፡ ይህንን በተመለከተ በጅቡቲ በኩል ህዝቡን ተጠቃሚ የማድረግ ችግሮች ቢኖሩም ችግሩ በዋነኛነት ከኢትዮጵያ የሚመነጭ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በአሁኑ ወቅት ጎልቶ የሚታይ ችግር ባይሆንም በጅቡቲ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ችግሮች እየተባባሱ ከሄዱ አለመረጋጋት ተፈጥሮ የወደብ አጠቃቀሙን ሊያሰናክል ይችላል፡፡ የተለያዩ ሃይሎች በጅቡቲ ላይ ተፅእኖ አሳርፈው አጠቃቀሙን እንዲያሰናክሉ በሩን ሊከፍትላቸው ይችላል፡፡ በዚህ መልኩ ሲታይ በጁቡቲ ሰላምና መረጋጋት የማስፈን ሃላፊነት የጅቡቲ መንግስትና ህዝብ ቢሆንም ጉዳዩ የእኛንም ጥቅም በቀጥታ የሚነካ መሆኑ አይቀርም፡፡ ይህ አደጋ ሁልጊዜም ታሳቢ መሆን ያለበት አደጋ ነው፡፡

በኢትዮጵያ በኩል ዋናው ችግር ከዚሁ ትስስር የጅቡቲም ህዝብ በአግባቡ ተጠቃሚ እንዲሆን የማድረግ፣ ሰጥቶ የመቀበልን መርህ በጥብቅ ተግባራዊ የማድረግ ችግር ነው:: በጅቡቲ በኩል አልፎ አልፎ የሚታዩ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም የመሻት፣ ለአጭር ጊዜ ጥቅም የማድላት ዝንባሌን መቃወም ተገቢ ቢሆንም ከወደቡ እኛ ብቻ ተጠቃሚ ሆነን ጅቡቲ ፋይዳ ባለው ደረጃ ተጠቃሚ ሳትሆን የምትቀርበት ሁኔታ እንደማይኖር፣ ዘመኑ አገልግሎትና ሸቀጥ የመሸጥና የመግዛት፣ ሰጥቶ የመቀበል ዘመን እንደሆነ ያለመገንዘብ ሁኔታ ይታያል:: አልፎ አልፎም ትምክህትና የማጣጣል አዝማሚያ ይንፀባረቃል:: በጅቡቲና በኢትዮጵያ መካከል ሁለቱንም አገሮችና አካባቢውን የሚጠቅም ጠንካራ ትስስር ሊፈጠር የሚችለው እነዚህ ስህተቶች ሲወገዱና የተስተካከለ የግንኙነት ፖሊሲ ተቀርፆ ተግባራዊ ሲሆን ነው::

**(መ) በጅቡቲ ላይ ልንከተለው የሚገባን ፖሊሲ፣**

ጅቡቲን በተመለከተ ልንከተለው የሚገባን ፖሊሲ በአንድ በኩል የወደብ አገልግሎት በተመጣጣኝ ዋጋ ዘላቂና አስተማማኝ በሆነ መልክ ለማግኘት የምንችልበት ሁኔታ መፍጠር ነው:: የሌሎች አማራጭ ወደቦች መኖርና መጠቀም ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ የጅቡቲና ወደብ ለዘለቄታው መጠቀም ይበልጥ አስተማማኝ ሊሆን እንደሚችል ታሳቢ ያደረገ ፖሊሲ ሊኖረን ይገባል:: ከዚህ በመነሳት በወደብ አጠቃቀም ላይ ዘላቂነትና ዋስትና ያለው ስምምነት እንዲፈረም፣ ተግባራዊ እንዲሆንና



ህዝቦቿ አውቀው እንዲደግፉት ማድረግ ያስፈልጋል:: ስምምነቱ በአንድ በኩል የአገራችንን እድገት የሚያፋጥን፣ በአገራችን እድገት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ የማይፈጥር በሌላ በኩል ደግሞ ጅቡቲም ከዚሁ እድገት ፍትሃዊ በሆነ አኳኋን ተጠቃሚ እንድትሆን የሚያደርግና በዘለቄታዊ የጋራ ጥቅም ላይ ያነጣጠረ መሆን ይኖርበታል:: ይህን በተመለከተ በሁለቱም ወገኖች የሚታዩ አንዳንድ በጎ ያልሆኑ አዝማሚያዎችን የሚቀርፍ ስምምነት መሆን ይኖርበታል::

ኢትዮጵያ በወደቡ በስፋት መጠቀም የምትችለው፣ በሁለቱ አገሮች መካከል ጠንካራ የንግድ ትስስር ሊኖር የሚችለው በሁለቱ አገሮች መካከል ያለው የመሰረተ ልማት አውታር ትስስር በከፍተኛ ደረጃ የተጠናከረ ሲሆን ነው:: በዚህ ረገድ የባቡር መስመሩ መሻሻልና መጠናከር፣ የመኪና መንገድ መሻሻል ልዩ ግምት ሊሰጠው የሚገባ ነው:: የቴሌኮምዩኒኬሽንና የመብራት አገልግሎት በሁለቱ አገሮች መካከል እንዲፈጠርና እንዲጠናከር ማድረግም ልዩ ግምት የሚሰጠው ይሆናል:: ስለሆነም ፖሊሲያችን በሁለቱ አገሮች መካከል ያለውን የመሰረተ ልማት አገልግሎት በተቻለ ፍጥነትና በላቀ ደረጃ ማሻሻልና ማጠናከርን ታሳቢ ያደረገ መሆን ይኖርበታል::

የጅቡቲ ህዝብ ከግንኙነቱ በይበልጥ ተጠቃሚ ሆኖ የትስስሩ ጠንካራ መሰረት እንዲሆን በሁለቱ አገሮች መካከል ያለው የንግድና የኢንቨስትመንት ትስስር ህጋዊ ፈር ተከትሎ እንዲጠናከር መደረግ አለበት:: ከዚህ አኳያ በኢትዮጵያ በኩል

ያሉ ገደቦች ልማታችንን በማይጎዳ ይልቁንም በሚያጠናክር አኳኋን የጅቡቲ ዜጎችን በተመለከተ መሻሻል ይኖርባቸዋል:: ይህ ዕድል ለጅቡቲ ተወላጅ ዜጎች ብቻ እስከተከፈተ ድረስ ልማታችንን ከማፋጠን አልፎ የሚጎዳበት ሁኔታ የለም:: የጅቡቲ ዜጎች ለአገራችን ዜጎች በተከለሉ መለስተኛ ኢንቨስትመንቶች ቢሳተፉ የሚያስከትሉት ጉዳት የለም:: ሌሎች በዚህ ቀዳዳ ገብተው የአገራችን መለስተኛ ባለሃብቶችን እድገት እንዳያሰናክሉ ጥንቃቄ እስከተወሰደ ድረስ ይህ አሰራር የጅቡቲ ህዝብ ጥቅሙን ከኢትዮጵያ ልማት ጋር አስተሳስሮ እንዲመለከትና ጠንካራ ወዳጅና አገር እንዲሆነን በማድረግ ስትራተጅካዊ ጠቀሜታ የሚያስገኝልን ነው:: ስለሆነም ፖሊሲያችን ለዚሁ ተግባር በቂ ትኩረት የሚሰጥና ሁኔታዎችን የሚያመቻች መሆን ይኖርበታል::

የጅቡቲን ሰላምና መረጋጋት የመጠበቅ ጉዳይ የጅቡቲ ህዝብና መንግስት ጉዳይ ነው:: ከዚሁ ዋነኛ ተጠቃሚ የሚሆነውም የጅቡቲ ህዝብ ነው:: እኛም በጅቡቲ ሰላም ላይ ቀጥተኛ ጥቅም አለን:: ስለሆነም ከጁቡቲ ህዝብና መንግስት ጋር በመሆን ለጅቡቲና ለአካባቢያችን ሰላም መሰረት የፖሊሲያችን አንደ መሰረታዊ ገፅታ መሆን ይኖርበታል::

በአጠቃላይ በአገሮች መካከል ሁሉን አቀፍና ጠንካራ የኢኮኖሚ ትስሰር እንዲኖር በማድረግ፣ ህዝቦቹ ከዚሁ ትስስር ተጠቃሚ እንዲሆኑና የትስስሩ ዘብ እንዲሆኑ በማድረግ የአፍሪካ ቀንድን ከብጥብጥና ቁርሾ ወደጋራ ልማትና ሰላም ማሸጋገር ያስፈልጋል:: ይህንን በማድረግ ረገድ አገራችን የተለየና ግንባር



ቀደም ሚና መጫወት ትችላለች:: ይህንን መሳይ ትስስር በመፍጠር ረገድ የቀለለ የሚሆነው በኢትዮጵያና ጅቡቲ መካከል ነው:: ከዚያም ቀጥሎ ቀለል የሚለው በኢትዮጵያና በሱዳን መካከል ነው:: በመሆኑም በኢትዮጵያና በጅቡቲ መካከል የተቻለውን ያህል ፈጣን፣ ሁሉን አቀፍና ጠንካራ የኢኮኖሚ ትስስር በማድረግ ደረጃ በደረጃና ሁኔታዎች በፈቀዱ መጠን ይህንኑ አካሄድ ከሌሎች አገሮችም ጋር ተግባራዊ በማድረግ ኢጋድን በዚሁ አላማ በተቻለ መጠን በመጠቀም አካባቢው የልማትና የሰላም ቀጠና እንዲሆን የማድረግ ፖሊሲ መከተል ይኖርብናል:: የልማትና የዴሞክራሲ ራዕያችንን በተሟላ አኳኋን ተግባራዊ በማድረግ የአፍሪካ ቀንድ በእኩልነትና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ የሰላምና የልማት ቀጠና እንዲሆንና ኢትዮጵያም መሆን በሚችለውና በሚገባው ደረጃ በዚሁ ረገድ ግንባር ቀደም ተዋናይ እንድትሆን የማድረግ ፖሊሲን ለዚሁ ዝግጁ ከሆኑ አገሮች ጋር ቀድሞ በመጀመር ተግባራዊ ማድረግ አለብን:: በዚህ ረገድ ጅቡቲ ከኛ ጋር የምትመሰርተው ጤናማና ጠንካራ ትስስር ለቀጠናው በምሳሌነት የሚያገለግል እንዲሆን ማድረግ ይኖርብናል::

## 1.6. በኬንያ ላይ የሚኖረን ፖሊሲ

### (ሀ) የግንኙነቱ ታሪካዊ አመጣጥ፣

ኬንያ ከቅኝ አገዛዝ ነፃ ከወጣችበት ጊዜ ጀምሮ በኬንያና በኢትዮጵያ መካከል የመልካም ጉርብትና ግንኙነት ሰፍኖ ኖሯል:: ሁለቱም አገሮች አንዱ በሌላው ጉዳይ ላይ ጣልቃ ሳይገባ፣ አንዱ

የሌላው የስጋት ምንጭ ሳይሆን በመከባበር ኖረዋል። ይልቁንም የታላቋ ሶማሊያ መፈክር ለሁለቱም አገሮች የስጋት ምንጭ ስለነበር በዚህ ዙሪያ የሚደጋገፉበትና የጋራ የመከላከያ ስምምነት የተፈራረሙበትም ወቅት ነበር። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በሁለቱ አገሮች ድንበር አካባቢ የከብት ዝርፊያ የሚታይበትና ባለፉት አስር አመታት እየተስፋፋ የመጣበት ሁኔታ አለ። በተጨማሪም በኬንያ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ችግሮች እየተፈጠሩ ሲሄዱ በሰሜን ኬንያ ኦነግና መሰሎቹ መጠጊያ የሚያገኙበት አጋጣሚ ታይቷል። እነዚህ ችግሮች መወገድ የሚገባቸው ቢሆንም የግንኙነቱን መሰረታዊ ባህሪ የሚወስኑ ወይም የሚቀይሩ አይደሉም።

በፖለቲካ መስክ የቆየው ግንኙነት በመሰረቱ ጤናማ ቢሆንም የኢኮኖሚ ግንኙነቱ መሆን ከሚችለውና ከሚገባው አኳያ ሲታይ እጅግ ወደኋላ የቀረ ሆኖ ይታያል። ኬንያ ምንም እንኳ ባለፉት 10 አመታት የተለያዩ የኢኮኖሚ ችግሮች ያጋጠሟትና ኢኮኖሚዋም እየተዳከመ የመጣ ቢሆንም ከአካባቢያችን የተሻለ ልማት የነበራትና አሁንም ያላት አገር ናት። በኢኮኖሚ እየተዳከመች ከመምጣቷ ጋር ተያይዞ የተለያዩ የፖለቲካ ችግሮች ቢያጋጥሟትም በመሰረቱ ሰላም የሰፈነባት አገር ነች። ከህዝብ ብዛትም አኳያ ከኢትዮጵያና ሱዳን ቀጥላ የምትታይ ነች። በድምር ሲታይ በተነፃፃሪ ሰፋ ያለ ገበያ ያላት አገር ነች። ይሁንና በሁለቱ አገሮች መካከል ያለው የንግድ ግንኙነት ደካማና ለኮንትሮባንድ የተጋለጠ ነው።

**(ለ) የግንኙነቱ ፋይዳ፣**



ከላይ እንደተገለፀው ኬንያ ምንም እንኳ አንዳንድ የኢኮኖሚ ችግሮች ልማቷን የገቱ ቢሆንም በአካባቢያችን በተነፃፃሪ ሰፋ ያለ ገበያ ያላት አገር ነች። ያሉባት ችግሮች ተፈተው ልማቷ ከተቀላጠፈም ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ገበያ ሊኖራት ይችላል። ከዚህም ባሻገር ኢትዮጵያን ከምስራቅና ደቡብ አፍሪካ ጋር የምታገናኝ ድልድይ ነች። ስለሆነም ከገበያ አኳያ ሲታይ ከሱዳን ጋር የሚመጣጠን ሚና ልትጫወት የምትችል አገር ነች።

ከተፈጥሮ ሃብት አኳያ የኬንያ ወደቦች ለአገራችን አንዳንድ አካባቢዎች አማራጭ ሊሆኑ ይችላሉ። ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ሃይል እጥረት ያለባት በመሆኗ ከኢትዮጵያ ይህንኑ አገልግሎት በመግዛት ሁለቱም አገሮች በከፍተኛ ደረጃ ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ። ከኢትዮጵያ የሚፈሰውና በሁለቱ አገሮች አዋሳኝ ላይ ወደሚገኘው ቱርካና ሃይቅ የሚገባው የኦሞ ወንዝ አጠቃቀም የተወሰነ ቅራኔ ሊፈጥር ቢችልም በትክክል ከተያዘ ቅራኔው በቀላሉ ሊፈታ የሚችል ነው። በድምር ሲታይ የኢኮኖሚ ትስስሩ በቂ ትኩረት ስላልተሰጠው እጅግ ደካማ በሆነ ደረጃ ላይ የሚገኝ ቢሆንም ኬንያ በኢትዮጵያ ልማት ላይ ቀላል ግምት የማይሰጠው በጎ ሚና መጫወት የምትችል አገር ነች።

ኬንያ እስካሁንም በአካባቢው የሰላም ሃይል የነበረችና የተረጋጋች አገር ስትሆን ለወደፊቱም በዚሁ አቅጣጫ ገንቢ ሚና ልትጫወት የምትችል ነች። በተለይም ባለፉት አመታት የተከሰቱት የኢኮኖሚና የፖለቲካ ችግሮች ከተፈቱ በአፍሪካ ቀንድ ውስጥ ትልቅና ገንቢ ሚና ልትጫወት የምትችል አገር ነች።

### (ሐ) በግንኙነቱ ላይ የታዩ ችግሮች፣

በግንኙነቱ ላይ የታየው ዋነኛ ችግር ለጠንካራና ህጋዊ የኢኮኖሚ ትስስር በቂ ትኩረት ያለመስጠቱ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ሁለቱን አገሮች በመንገድም ሆነ በባቡር ማስተሳሰር ሲቻል እስካሁን ደረስ የረባ የመንገድ ግንኙነትም የለም፡፡ የቴሌኮምዩኒኬሽንና የኤሌክትሪክ አገልግሎት ማስተሳሰርና ማጠናከር ሲቻል በዚህ ረገድ የተሰራ የረባ ስራ የለም፡፡ በአጠቃላይ በሁለቱ አገሮች መካከል ጠንካራ የንግድ ትስስርና ግንኙነት ለመፍጠር የሚያስችል የረባ ስራ አለመሰራቱ መልካም ግንኙነቱ ከልማት ጋር ሳይተሳሰር እንዲቀር አድርጎታል፡፡ ጉዳዩ በሁለቱም አገሮች በቂ ትኩረት ያልተሰጠው በመሆኑ የሁለቱም አገሮች ችግር ተደርጎ ሊቀመጥ የሚችል ነው፡፡

ባለፉት አስር አመታት እየታዩ የመጡት የፖለቲካና የኢኮኖሚ ችግሮች ካልተፈቱ የኬንያን ሰላምና መረጋጋት ሊያውኩ የሚችሉ ናቸው፡፡ ይህ በአካባቢያችን ላይ የሚያስከትለው አሉታዊ ተፅእኖ ከባድ ሊሆን እንደሚችል ሰሜን ኬንያ ባለፉት አመታት በተወሰነ ደረጃ ለፀረ-ሰላም ሃይሎች መናኸሪያ ሆኖ ማገልገሉ ተጨባጭ ምልክት ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ አንዳንድ የጥገኝነት አመለካከት የተጠናወታቸው ኬንያውያን አጎራባች አገሮች ከፊት ከነበረው ሁኔታ በተለየ ሰላምና ዴሞክራሲ ሲሰፍንባቸው፣ ልማታቸው ሲፋጠን ኬንያ በርዳታ ሰጭ አገሮች ዘንድ የነበራት ተሰሚነትና ከዚሁ ስታገኝ የነበረችው ጥቅም የሚቀንስባት መስሎ ይታያቸዋል፡፡ ከዚህ በመነሳትም የኬንያ ጎረቤቶች መረጋጋትና



ልማት ጥቅማቸውን የሚነካ እየመሰላቸው በቅናትና በጥርጣሬ የሚያዩበት ሁኔታ ይስተዋላል፡፡ ይህ አስተሳሰብ በኬንያ ውስጥ የበላይነት እያገኘ ከሄደ ኬንያ ኢትዮጵያን ጨምሮ ከሁሉም ጎረቤቶቿ ጋር ያላት ግንኙነት በሚፈለገው መጠን እንዳይጠናከር እንቅፋት ሊሆን ይችላል፡፡

### (መ) ኬንያን በሚመለከት ልንከተለው የሚገባን ፖሊሲ፣

በኬንያ ላይ የምንከተለው ፖሊሲ ከመሰረታዊ አገራዊ ጥቅማችን ጋር ተያይዞ ኬንያ በልማታችንና በደህንነታችን ላይ ሊኖራት ከሚችል ቀላል ግምት የማይሰጠው ሚና መነሳት አለበት፡፡ በዚህ ረገድ የኬንያ ህዝብና መንግስት የኢትዮጵያ ሰላምና ልማት ለኬንያም ከፍተኛ ጥቅም ከመሆን ውጭ ምንም የሚቀንስባት ነገር እንደሌለ እንዲገነዘቡ መጣጣር ይኖርብናል፡፡ በዚህ ላይ ተመስርተን ከኬንያ ጋር ጠንካራ የንግድ ግንኙነት በመመስረት ብሎም በኬንያ በኩል ከተቀረው የምስራቅ አፍሪካና የደቡብ አፍሪካ ክፍል ጋር ለመተሳሰር መጣጣር ይኖርብናል፡፡ በዚህ ረገድ ወሳኙ የመጀመሪያ ርምጃ የመሰረተ-ልማት አውታሮችን ማገናኘት ስለሆነ ይህንኑ በተቻለ ፍጥነት የመፈፀም ፖሊሲ ልንከተል ይገባናል፡፡ የኮንትሮባንድ ንግድን አጥፍተን ጠንካራ ህጋዊ የንግድ ትስስር እንዲፈጠር መረባረብ የፖሊሲያችን ማዕከል ሊሆን ይገባል፡፡

እስካሁን የነበረው የመልካም ጉርብትናና የሰላም ግንኙነት ለወደፊቱም ፀንቶ እንዲቀጥል የማድረግ ፖሊሲ መከተል አለብን፡፡ በዚህ ረገድ በአንድ በኩል በድንበር አካባቢ የሚታዩትን

አንዳንድ ችግሮች በጋራ ጥረት ለማስወገድ መረባረብ ይኖርብናል። እየተስፋፋ የመጣው የከብት ዝርፊያና ከዚህ ጋር የተያያዙ የአካባቢው ህዝብ ግጭቶችን ማስወገድ ይኖርብናል። ሰሜን ኬንያ የአገራችን ፀረ-ሰላም ሃይሎች አንድ መናኸሪያ እየሆነ የመምጣቱ ጉዳይ በአጭሩ እንዲቀጭ ከኬንያ ጋር ተባብረን መስራት ይኖርብናል። በዚህ ረገድ የሚታዩ ችግሮች ሳይባባሱ በመግባባት እንዲፈቱ ማድረግ ወዳጅነታችን ፀንቶ እንዲቀጥል በማድረግ ረገድ ያለውን ከፍተኛ ፋይዳ የተገነዘበ ፖሊሲና የፖሊሲ አፈፃፀም እንዲኖረን ማድረግ ያስፈልጋል።

በሌላ በኩል ኬንያ የተረጋጋች አገር ሆና መቀጠሏ ለብሄራዊ ጥቅማችንና ለደህንነታችን በጣም ጠቃሚ መሆኑን በመገንዘብ የኬንያ ህዝብና መንግስት የፖለቲካና የኢኮኖሚ ችግራቸውን ለመፍታት የሚያደርጉትን ጥረት ሁሉ ባለን የተወሰነ አቅም የመደገፍ ፖሊሲ መከተል አለብን። በህዝቦች መካከል ትስስር እንዲጠናከር በመንግስታቱም ቀጣይና በጋራ መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ምክክር እንዲኖር ማድረግ አለብን።

### 1.7. ኢጋድን ማጠናከር፣

የቅርብ ጎረቤቶቻችንንና ዩጋንዳን ከኢትዮጵያ ጋር የሚያስተሳስር አካባቢያዊ ድርጅት ኢጋድ እየተባለ የሚጠራው ነው። ኢጋድ በነዚህ አገሮች መካከል የመልካም ጉርብትና ግንኙነት እንዲዳብር፣ አለመግባባቶች በሰላም እንዲፈቱ፣ በአገሮቹ መካከል ጠንካራ የኢኮኖሚ ትስስር እንዲኖር በማድረግ የተቋቋመ ድርጅት



ነው። የድርጅቱ አላማ ከአገራችን አላማ ጋር አንድና ያው ከመሆኑም ባሻገር ኢትዮጵያ በጂኦግራፊያዊ አቀማመጧ፣ በህዝቧ ብዛት ለኢጋድ አላማዎች ካላት ታማኝነት ወዘተ. አኳያ በዚሁ ድርጅት ውስጥ ከፍተኛ ሚና መጫወት ትችላለች፣ ይገባታልም።

ኢጋድ የተለያዩ ችግር እንዳሉበት የሚታወቅ ነው። በቂ የሰው ሃይልና ገንዘብ ያለው ድርጅት አለመሆኑ ለመዳከሙ አንዱ ምክንያት ነው። አባል አገሮች ለድርጅቱ መጠናከር እኩል ተቆርቋሪነት አለማሳየታቸውም ሌላው የድክመቱ ምንጭ ነው። የሶማሊያ መበታተንና በሱዳን ያለው ጦርነትም ለኢጋድ መዳከም የራሳቸውን አስተዋፅኦ አድርገዋል። ሌላውና ምናልባትም ለኢጋድ መዳከም በዋነኛነት ሊጠቀስ የሚችለው ችግር በአባል አገሮች መካከል በተለይም በኤርትራና በበርካታ ሌሎች የኢጋድ አባል አገሮች መካከል ያለው አለመግባባት ነው። እነዚህን ችግሮች ለማቃለል ጥረት በማድረግ ኢጋድን ማጠናከር አንድ መሰረታዊ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲያችን ሊሆን ይገባል።

## 2. ሌሎች የአፍሪካ አገሮች፣

### 2.1. የግንኙነቱ ታሪካዊ አመጣጥ፣

ኢትዮጵያ ከአጎራባች የአፍሪካ ቀንድ አገሮች በተጨማሪ ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች ጋርም በተለይ ነፃነታቸውን ከተቀዳጁ በኋላ በጣም ጤናማ ግንኙነት መስርታ ቆይታለች። የአፍሪካ አንድነት ድርጅት መስራች ከሆኑት አገሮች አንዷ ከመሆኗም

በላይ ለድርጅቱ አላማ በታማኝነትና በግንባር ቀደምትነት ታግላለች፡፡ በቅኝ ግዛት ስር የነበሩ አገሮች ነፃነታቸውን እንዲቀዳጁ በግልፅና በህቡዕ የተቻላትን ሁሉ አድርጋለች፡፡ ያለፉት መንግስታት በዚህ ረገድ የተከተሉት ፖሊሲና ተግባር በበጎ ገፅታው የሚጠቀስ፣ ኢትዮጵያ አፍሪካዊ ግዴታዋን እንድትወጣና በአፍሪካውያን ወንድሞቻችን ዘንድ ትልቅ ከበሬታን እንድታገኝ ያስቻለ ነው፡፡ ይህ ሂደት ባለፉት አስር አመታትም በተመሳሳይ አቅጣጫ የቀጠለና ጤንነቱ የተጠበቀ ግንኙነት እንዲሆን ለማድረግ ያስቻለ ነው፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያ ከአፍሪካ አንድነት ድርጅትና ከአባል አገሮች ሰፊ ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ ድጋፍ ስታገኝ ቆይታለች፡፡ በቅርቡ አገራችን በሻዕቢያ በተወረረችበት ወቅት እንደታየው አፍሪካ የኢትዮጵያን ሰላምና ደህንነት ደግፎ በጥብቅ ቆሟል፣ ከዚያ በፊትም ተመሳሳይ አቋም ይዟል፡፡ በአጭሩ አገራችን ከአፍሪካ ጠይቃ ያጣችው ይህ ነው የሚባል የፖለቲካም ሆነ የዲፕሎማሲ ድጋፍ የለም ማለት ይቻላል፡፡ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና ፅህፈት ቤት መሆኗም የዚሁ ውጤት ከመሆኑም በላይ በአገራችን ላይ ልዩ ሃላፊነት የሚያስቀምጥ ነው፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው ኢትዮጵያ ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች ጋር ያላት ዲፕሎማሲያዊና ፖለቲካዊ ግንኙነትና ጠንካራና ጤናማ ቢሆንም ከአፍሪካ አንድነት አለመጠናከር ጋር የተያያዙ ውሱንነቶች የነበሩት ነው፡፡ በአፍሪካ አገሮች ያለው አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ ትስስር ደካማ በመሆኑ አገራችንም ከአፍሪካ ቀንድ ውጭ ካሉት



የአፍሪካ አገሮች ጋር ይህ ነው የሚባል የኢኮኖሚ ግንኙነት የላትም፡፡ የአፍሪካ ህብረት በግሎባላይዜሽን ማዕቀፍ የአፍሪካን ከዚህ ጋር ተያይዞም የእያንዳንዱን የአፍሪካ አገር ድርሻ ለማሻሻል ጠንካራ የትግልና የድርድር መድረክ መሆን ሲችልና ሲገባው በዚህ ረገድ ጠንካራ ሚና ሳይጫወት ቀርቷል፡፡ ምንም እንኳ በአፍሪካ ሰላም ለማስፈን ከፍተኛ ጥረት ያደረገ ቢሆንም በዚህም ረገድ በቀላሉ የማይገመት ውሱንነት ታይቶበታል፡፡

## 2.2. የግንኙነቱ ፋይዳ፣

ኢትዮጵያ ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች ጋር የምታደርገው ግንኙነት ሰላማችንን ለመጠበቅ የሚያስችለን አለማዊና አካባቢያዊ ሁኔታ በመፍጠር ረገድ እስካሁንም ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ሚና ተጫውቷል ለወደፊቱም የላቀ ሚና ሊጫወት ይችላል፡፡ እኛ ፍላጎታችን ሌላውን ነገር ሁሉ ወደጎን ብለን በልማት ላይ መረባረብ ነው፡፡ በተቻለን መጠን ግጭቶችን ሁሉ ማስወገድ፣ በፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ አኳኋን ልዩነቶችን መፍታት፣ በኛ ላይ ግጭት ለመፍጠር የሚሞክሩትን በድርድር፣ በዲፕሎማሲያዊና ፖለቲካዊ ተፅእኖ ለማስታገስ ነው የምንፈልገው፡፡ በዚህ ረገድ የአፍሪካ አገሮችና የአፍሪካ ህብረት ከፍተኛና ቀጥተኛ ድጋፍ ሊያበረክትልን ይችላል፡፡ በዚህ ረገድ ከአፍሪካ ልናገኝ የምንችለው ድጋፍና ተሰሚነት በሌሎች የአለም ክፍሎች ለምናደርገውም ጥረት በተዘዋዋሪ መንገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ሊያደርግልን ይችላል፡፡ ዲፕሎማሲያችን ግጭቶችን በመግታት ለልማትና ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ የተመቻቸ

ሁኔታ እንዲፈጥርልን ማድረግ አለብን ብለን ያስቀመጥነውን አቅጣጫ ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ የአፍሪካ ህብረት የላቀ ሚና ሊጫወት ይችላል።

የአፍሪካ አገሮች ጠባብና የተበጣጠሰ ገበያን ይዘው በግሎባላይዜሽን ማዕቀፍ በሚፈለገው መጠን ተጠቃሚ መሆን አይችሉም። በመሆኑም በኢኮኖሚ መስክ ከረጅሙ ጊዜ አኳያ በአፍሪካ አገሮች መካከል ጠንካራ ኢኮኖሚያዊ ትስስር መፈጠሩ ለአፍሪካ ልማት ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚያደርግ ይታወቃል። አገራችንም በዚሁ ኢኮኖሚያዊ ትስስር ውስጥ ገብታ ተጠቃሚ መሆን ትችላለች። ይሁንና ከአጭርና ከመካከለኛ ጊዜ አኳያ ሲታይ ከፍተኛ ለውጥ የሚያመጣ የንግድ ትስስር ይኖራል ብሎ መገመት ያስቸግራል።

በሌላ በኩል ግን ግሎባላይዜሽን በአገራችን ላይ የሚያሳድራቸው በጎ ያልሆኑ ተፅእኖዎች በሌሎቹ የአፍሪካ አገሮችም ላይ የሚደርሱ ናቸው። የአለም ገበያ ለአፍሪካ ምርቶች ዝግ የመሆኑ ጉዳይ፣ የርዳታ ፍሰቱ በመጠንና በአይነት በርካታ ጉድለት ያለበት መሆኑ ወዘተ. በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው። እነዚህን ችግሮች ለማስወገድ በተናጠል የምናደርገው ጥረት መኖር ያለበት ቢሆንም ይበልጥ ውጤታማ የሚሆነው ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች ጋር በመሆን በጋራ ስንደራደርና ስንታገል ነው።

በድምር ሲታይ ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች ጋር ያለን የንግድ ግንኙነት መጠናከሩ ከረጅም ጊዜ አኳያ በልማት ዕድላችን



ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ የሚያሳርፍ ቢሆንም ከአጭርና ከመካከለኛ ጊዜ አኳያ ይህን ያህል የጎላ አስተዋፅኦ ይኖረዋል ተብሎ የሚገመት አይደለም። ከኢኮኖሚ ልማት አንፃር ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች ጋር የሚኖረን ግንኙነት ከፍተኛ ግምት ሊሰጠው የሚገባው በአጭርና በመካከለኛ ጊዜ ንግዱ በከፍተኛ ደረጃ ይጨምራል በሚል ግምት ሳይሆን ግሎባላይዜሽን በልማታችን ላይ የሚያስከትለውን አሉታዊ ተፅእኖ ለመቀነስ አመች ሁኔታዎችን በብቃት ለመጠቀም በምናደርገው ድርድርና ርብርብ ዋነኛ መድረክ ሆኖ ስለሚያገለግለንና ሊያገለግለንም ስለሚገባ ነው። በዋነኛነት በሰላማችን ላይ ባለው አስተዋፅኦ ቀጥሎም ለልማታችን ሊያበረክት ከሚችለው አስተዋፅኦ አኳያ ሲታይ ግንኙነቱ ከፍተኛ ፋይዳ ያለው ነው።

## 2.3. ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች ጋር ሊኖረን የሚገባ ግንኙነት፣

ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች ጋር የሚኖረን ግንኙነት ዋነኛ ፋይዳው (በተለይም ከአጭርና ከመካከለኛ ጊዜ አኳያ) ሰላማችን ላይ የሚኖረው ሚና ነው። ፖሊሲያችን ይህንኑ ለማጎልበት ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጥ መሆን አለበት። ለአፍሪካ ህብረት አላማዎች ታማኝ በመሆንና በዚህ ረገድ ግንባር ቀደም ሚና በመጫወት በአፍሪካ ውስጥ ያለን ተሰሚነት እንዲቀጥል ከዚያም አልፎ በይበልጥ እንዲጎለብት ማድረግ አለብን። የአፍሪካ ህብረት ግጭቶችን በማስወገድ ረገድ በይበልጥ ውጤታማ እንዲሆን መጣርና በዚህ ረገድ አገራችን ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራት ማድረግ ይኖርብናል። ከአፍሪካ አገሮች ጋር በተናጠል የሚኖረን ግንኙነትም

ጤናማና ይህንኑ መርህ የተከተለ መሆን አለበት። በዚህ መልክ በአፍሪካ የምናጠናክረውን ተሰሚነት በአካባቢያችን ግጭቶችን ለመግታት በሚያስችል የላቀ ደረጃ ለመጠቀም መረባረብ አለብን። በተጨማሪም በዚህ ረገድ የምናጠናክረው ተሰሚነት በሌላው አለምም ለምናደርገው የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ ደጋፊና መንደርደሪያ እንዲሆን ማድረግ አለብን። ፖሊሲያችን ከላይ የተጠቀሱትን ነገሮች በተሟላ አኳኋን ለመፈፀም የሚያስችለን መሆን አለበት።

በአፍሪካ አገሮች መካከል ጠንካራ ኢኮኖሚያዊ ትስስር እንዲፈጠር የሚደረገውን ጥረት የሚደግፍ ፖሊሲ መከተል አለብን። ትስስሩ ከአጭር ጊዜ አኳያ የሚፈጥረው የልማት ዕድል ምንም ይሁን ምን ከረጅም ጊዜ አኳያ ጠቀሜታው ከፍተኛ ስለሆነ ልንደግፈውና በግንባር ቀደምትነት ልንሰለፍለት የሚገባን ነው። በዚህ ረገድ ኮሜሳን እንደአንድ የትስስር መሳሪያ አጠናክረን ልንገፋበት ይገባል። ከዚህ በተጨማሪ የአፍሪካ ህብረት አፍሪካ በግሎባላይዜሽን ማዕቀፍ ያላትን ቦታ በማሻሻል ረገድ ዋነኛ የትግልና የድርድር መድረክ እንዲሆንና ይህንኑ ተልዕኮ በብቃት እንዲወጣ ባለን አቅም ሁሉ መረባረብ አለብን።

በአሁኑ ወቅት የአፍሪካ ህብረት ከላይ የተጠቀሱትን የልማትና የሰላም አላማዎች ይዞ እንዲጠናከር ጥረት እየተደረገ ነው። ይህንኑ ተገንዝበን ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት አላማዎች ታማኝ ሆነን እንደተረባረብን ሁሉ ለአፍሪካ ህብረት አላማም ታማኝ ሆነን መረባረብ አለብን። ከዚህ ጋር ተያይዞ የአፍሪካን



የኢኮኖሚ ሁኔታ ለማሻሻል የተቀየሰውን ኔ-ድና መሰል ፕሮግራሞች በሙሉ ልብ ደግፈን ግንባር ቀደም ሚና መጫወት አለብን። ከላይ የተጠቀሱትን አላማዎች ለማሳካት ከሁሉም የአፍሪካ አገሮች ጋር የመተባበር ፖሊሲ ሊኖረን ይገባል። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ሁሉም አገሮች ለእነዚህ አላማዎች በእኩልነት አስተዋፅኦ የማድረግ አቅሙም ፍላጎቱም ስለማይኖራቸው በዚህ ረገድ የላቀ ፍላጎትና አቅም ካላቸው ጋር በይበልጥ ተቀራርበን የመስራት ፖሊሲ ልንከተል ይገባል።

## 3. ከመካከለኛው ምስራቅ ጋር የሚኖረን ግንኙነት፣

### 3.1. አጠቃላይ፣

ለመካከለኛው ምስራቅ የቀረብን በመሆናችን መካከለኛው ምስራቅ በታሪካችን ውስጥ በበጎ ሆነም በመጥፎ ከፍተኛ ተፅእኖ አሳድሯል። ይልቁንም ሌሎች የአፍሪካ አገሮች ካሳደሩት ተፅእኖ ይልቅ መካከለኛው ምስራቅ ያሳደረው ተፅእኖ ልቆ ይገኛል።

በመካከለኛው ምስራቅ የመነጩት ታላላቆቹ ሃይማኖቶች በአገራችን ተፅእኗቸውን ቀድመው አሳርፈዋል። ክርስትናን ከአርሜንያና ከኮኒስታቲኖፕል ቀጥሎ የተቀበለችው የፖለቲካ ማህበረሰብ ኢትዮጵያ እንደሆነች ይታወቃል። ክርስትና ወደአገራችን የገባው ከመካከለኛው ምስራቅ ሲሆን ከ1600 አመታት በላይ ለሚሆን ጊዜ የአገሪቱ -ትርያርኮች ከግብፅ የሚመጡ ነበሩ። ክርስትና የብዙ ኢትዮጵያውያን እምነት ከመሆን አልፎ

የታሪካችንና የባህላችን አንድ አካል ሆኗል። አገራችን እስልምናን ከማንም አገር፣ ሃይማኖቱ ከመነጨበት ከሳኡዲ አረብያ ጭምር ቀድማ ያስተናገደች አገር ነች። የነብዩ መሀመድ ተከታዮች በአገራቸው መኖር የማይችሉበት ደረጃ ላይ ሲደርሱ በነብዩ ትእዛዝ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ተጠልለዋል። ከዚያም በኋላ ነብዩ አበሾችን ካልነኳችሁ እንዳትነኩ ብለው እስልምና ለኢትዮጵያ ያለውን ልዩ ከበሬታ አስምረውበታል። ከዚያን ወዲህ እስልምና የብዙ ኢትዮጵያውያን እምነት ብቻ ሳይሆን የታሪካችንና የባህላችንም አንድ አካል ሆኗል። በተመሳሳይ መልኩ እጅግ ጥንታዊ የሆነ የይሁዲ ሃይማኖት በአገራችን በርካታ አማኞች እንደነበሩትና በታሪክና ባህላችንም ላይ የራሱ ተፅእኖ እንደነበረው ይታወቃል። በቋንቋ፣ በታሪክ፣ በባህል ከመካከለኛው ምስራቅ ጋር የረጅም ጊዜ ትስስር ፈጥረናል።

በሌላ በኩል ደግሞ በአሉታዊ ገፅታቸው የሚጠቀሱ ጉዳዮችም ነበሩ። በኢትዮጵያና በመካከለኛው ምስራቅ መካከል ያለውን ግንኙነት ያሻክሩ ከነበሩት ጉዳዮች አንዱ የአባይ ወንዝ ጉዳይ ነው። አባይ በኢትዮጵያና በግብፅ መካካል በነበረው የሺ አመታት ትስስር የራሱ ቦታ ነበረው። ግብፃውያን የአባይን ውሃ ማንም እንዳይነካባቸው ተፅእኖ ሲያሳርፉ ኖረዋል። በሌላ በኩልም ኢትዮጵያ በአባይ ውሃ ላይ ያላት መብት እንዲከበርላት ያለማሰለስ ታግላለች። በሂደት ግብፅ የአረቡ አለም መሪ እየሆነች ስትመጣ የአባይ ጉዳይ ከኢትዮጵያና ከግብፅ አልፎ በኢትዮጵያና በሌሎች የአረብ አገሮችም ላይ ተፅእኖውን እያሳረፈ መጥቷል፣ አሁንም ያሳርፋል።



ሃይማኖትም የበኩሉን አሉታዊ ተፅእኖ ከማሳረፍ ወደኋላ አላለም። ለዚህም ሁለት ዋና ዋና ምንጮች ነበሩ። እነሱም የእስልምና አክራሪነትና የኢትዮጵያ ለአደጋ ተጋላጭነት ናቸው። በአክራሪ እስላምናና በለዘብተኛ እስላም መካከል ካሉት ልዩነቶች አንዱ በኢትዮጵያ ላይ ያለው አመለካከት ነው። ለዘብተኛው እስላም ኢትዮጵያ የነብዩን የመጀመሪያ ተከታዮች ያስተናገደች፣ የመጀመሪያው ሂጅራ አገር፣ የተከበረችና ማንም የሃይማኖቱ ተከታይ ሳትነካው ሊነካት የማትገባ አገር ነች ብሎ ያምናል። በዚህም ረገድ ከሌሎች አገሮች ሁሉ ለየት ያለ ቦታ ሊሰጣት እንደሚገባ ያምናል። አክራሪው እስላም ደግሞ የነብዮን ተከታዮች መጠለያ የሰጡት ንጉሱ ብቻ ናቸው፣ እሳቸውም ህዝቡን ፈርተው ይፋ አላወጡትም እንጅ የእስልምና አማኝ ሆነው ነበር፣ ስለሆነም ህዝቡ ጠላት ነው፣ ኢትዮጵያም እስልምናን የካደች የመጀመሪያዋ አንዳሉሲያ ተብላ ልትፈረጅ የሚገባት አገር ነች ይላሉ። በዚህ ምክንያት አክራሪነት ሲጠናከር ኢትዮጵያ ለጥቃትና ጥላቻ ስትጋለጥ፣ ለዘብተኛነት ሲጠናከር ግንኙነቷ ሲሻሻል ኖራለች።

በሌላ በኩል ደግሞ ምንም እንኳ በሃይማኖቶች መካከል መቻቻል መኖሩ የታሪካችንና የባህላችን ዋነኛ መገለጫ ሆኖ የቆየ ቢሆንም አልፎ አልፎ በሁለቱ ሃይማኖቶች ተከታዮች መካከል ግጭት መፈጠሩ አልቀረም። በተለያዩ ወቅቶች በተለያዩ አካባቢዎች በአገራችን ተመስርተው የነበሩ የእስልምና ስልጣኔዎችና በክርስትና ነገስታት መካከል የበላይነትን በማረጋገጥ ዙሪያ የተለያዩ ጦርነቶች ተካሂደዋል። በሂደትም የሃይማኖት እኩልነት ተግባራዊ የማይሆንባቸው ስርአቶች

በአገራችን የበላይነት አግኝተው ለረጅም ጊዜ ቆይተዋል፡፡ ይህ በአንድ በኩል የሃይማኖት እኩልነትን ለማረጋገጥ የሚካሄድ የውስጥ ትግልን ሲቀሰቅስ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ይህንን ቀዳዳ በመጠቀም ኢትዮጵያን ለመጉዳት ለሚቃጡ የውጭ ጥቃቶችም በር ከፍቷል፡፡

በኢትዮጵያና መካከለኛው ምስራቅ መካከል ባለው ግንኙነት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ያሳረፈው ሌላው ጉዳይ ድንቁርና፣ (Ignorance) አለማወቅ ነው፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው በኢትዮጵያና በመካከለኛው ምስራቅ መካከል ለሺ አመታት የዘለቀ ግንኙነት የነበረ ቢሆንም በዚያው መጠን አንዱ ሌላውን በትክክል የሚያውቅበት ሁኔታ አልተፈጠረም፡፡ ኢትዮጵያውያን መካከለኛውን ምስራቅ በተለይም የአረቡን አለም ከሩቁ በጥርጣሬ ከመመለከት አልፈው አገሮቹን በሚገባ አጥንተውና አውቀው፣ በተሟላ እውቀት ላይ የተመሰረተ አቋም የሚወስዱበት ሁኔታ አልነበረም፡፡ ይህ እስከዛሬም የዘለቀ ጉዳይ ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩም በመካከለኛው ምስራቅ በተለይም በአረቡ አለም ያሉ ህዝቦች ኢትዮጵያን በጥርጣሬና በንቃት ከመመልከት አልፈው በሚገባ ለማወቅ ያደረጉት ጥረት የለም፡፡ ስለሆነም ግንኙነቱ በአለማወቅ ላይ የተመሰረተ ጥርጣሬ፣ ጥላቻና ንቀት ሲሰቃይ የነበረና ያለም ነው ማለት ይቻላል፡፡ የተለያዩ ሃይሎች በአለማወቁ ላይ ተመስርተው የጥላቻና ጥርጣሬ ዘር በመዝራት ቀጣይ ስራ ስለተሰሩበት ችግሩ እንዲባባስ አድርጎታል፡፡

በአረቦችና በእስራኤል መካከል ቅራኔ ከተፈጠረ ወዲህ



ይህ ቅራኔ ኢትዮጵያ ከመካከለኛው ምስራቅ ጋር ባላት ግንኙነት ላይ የበኩሉን አሉታዊ ተፅእኖ ሲያሳርፍ ቆይቷል፡፡ በአንድ በኩል አረቦቹም ሆኑ እስራኤላውያኑ ኢትዮጵያ የራሷን ጥቅም በሚያስጠብቅ አኳኋን ግንኙነቶችን እንድትመሰረት ሳይሆን ከአንዱ ጋር ወግና በሌላው ላይ በጠላትነት እንድትሰለፍ የሚጠይቁ ነበሩ፡፡ ኢትዮጵያም ይህንኑ ስትቀበል የራስዋን ነፃ አቋም ከመውሰድ ይልቅ ከአንዱ ወይም ከሌላው ጋር በመወገን ስትላጋ ኖራለች፡፡

መካከለኛው ምስራቅ በደህንነታችን ላይ እጅግ የላቀ ተፅእኖ የሚያሳድር አካባቢ ነው፡፡ በኢኮኖሚያዊ ልማታችን ላይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የላቀ ተፅእኖ ያለው ነው፡፡ በመሆኑም የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲያችን ልዩ ትኩረት ሊሰጣቸው ከሚገቡ አካባቢዎች አንዱ የመካከለኛው ምስራቅ መሆን አለበት፡፡

በመካከለኛው ምስራቅም የምንከተለው ፖሊሲ ሁሉም ነገር ወደ ልማትና ዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ከሚለው መርህ መነሳት አለበት፡፡ ለልማታችንና ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ እንቅፋት የሆኑትን ነገሮች ግጭትን በማስወገድ መርህ፣ በድርድርና በመቻቻል መርህ፣ በፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ አኳኋን በማስወገድና ለልማታችን በጎ አስተዋፅኦ ያላቸውን ነገሮች ለማበራከትና አሟጦ ለመጠቀም የሚያስችል መሆን አለበት፡፡ በመካከለኛው ምስራቅ የምንከተለው ፖሊሲ ከዚህ በተጨማሪ ብቃት ባለው ጥናትና ምርምር፣ በእውቀት ላይ በተመሰረተና

በተለያዩ ስሜቶች የማይነዳ መሆን አለበት፡፡ ለግንኙነቱ መዳበር እንቅፋት የሚሆኑትን ነገሮች ለማርገብ፣ ከተቻለም ለማስወገድ የሚጣጣር መሆን አለበት፡፡ እነዚህን መሰረታዊ አቅጣጫዎች መነሻ በማድረግ ከየአገሩ የተለያየ ሁኔታ ጋር አብሮ የሚሄድ ዝርዝር ፖሊሲ በመንደፍ የሚፈፀም መሆን አለበት፡፡

## 3.2. ከግብፅ አኳያ የምንከተለው ፖሊሲ፣

### (ሀ) የግንኙነቱ ታሪካዊ አመጣጥና ችግሮች፣

የግብፅ ስልጣኔ ከመጀመሪያው ጀምሮ በአባይ ውሃ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ወደግብፅ ከሚገባው የአባይ ውሃ ውስጥ ከ85% የማያንሰው ከኢትዮጵያ የሚመነጭ ነው፡፡ ስለሆነም ከመጀመሪያው ጀምሮ ሁለቱ አገሮች በተፈጥሮ በጥብቅ የተሳሰሩና የተቆራኙ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ የአባይ ውሃ አጠቃቀምን በሚመለከት ኢትዮጵያ ያለባት ችግር በዋነኛነት ከግብፅ ጋር ነው፡፡ ግብፅ በአረቡ አለም ባላት ተሰሚነት ምክንያት የአባይን ጉዳይ ከግብፅና ከኢትዮጵያ አልፎ፣ ኢትዮጵያ ከሌሎች አገሮች ጋር ባላት ግንኙነትም ላይ ተፅእኖውን አሳርፏል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ አክራሪነት በግብፅ ሲጠናከር ግንኙነቱ በይበልጥ የሚሻክርበት ሁኔታ ሲፈጠር ቆይቷል፡፡ አለማወቅም ለግንኙነቱ መሻከር ከፍተኛ አስተዋፅኦ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

የአባይ ውሃን አጠቃቀም በተመለከተ ግብፃውያን ለረጅም ጊዜ ኢትዮጵያ በውሃው በተለይም ለመስኖ ልማት



እንዳትጠቀም ባለ በሌለ አቅማቸው ሲረባረቡ ቆይተዋል፡፡ ኢትዮጵያ በአባይ ውሃ መጠቀም ከጀመረች ግብፅ ለከፍተኛ አደጋ ትጋለጣለች ብለው ሲሰጉ ኖረዋል፡፡ እንደአውሮ-ውያን አቆጣጠር በ1959 እ.ም ግብፅ ከሱዳን ጋር ያደረገችው ስምምነት ውሃው ለሱዳንና ለግብፅ ተከፋፍሎ ለኢትዮጵያ አንድም ሊትር የማያስቀር ነበር፡፡ በግብፃውያን አመለካከት ውሃውን ኢትዮጵያ ከተጠቀመች ግብፅ ትጎዳለች፣ ግብፅ መጠቀም ካለባት ኢትዮጵያ እጅዋን ከውሃው ማንሳት አለባት፡፡ ሁለቱ ሊጣጣሙ የማይችሉ እርስ በርሳቸው የሚጣፉ ጥቅሞች እንደሆኑ (ዜሮ-ሳም ጌም) አድርገው ሲመለከቱ ኖረዋል፡፡

በአንድ በኩል ግብፆች የአባይን ውሃ ለሁሉም የማይበቃ አድርገው ሲያዩ በሌላ በኩል ግን እጅግ አባካኝ በሆነ መንገድ ሲጠቀሙበት ይታያሉ፡፡ በአስዋን ላይ የተገነባው ግድብ፣ በምድረ በዳ ላይ የተገነባና ለትነት በጣም የተጋለጠ በመሆኑ በየአመቱ ከ10 ቢልዮን ሜትር ውሃ በላይ በትነት ይጠፋል፡፡ ይህ በተከዜ ወንዝ ላይ ለአመት ከሚፈሰው የውሃ መጠን የላቀ ነው፡፡ የመስኖ ውሃ አጠቃቀማቸው እጅግ አባካኝ ከመሆኑ ባሻገር የአባይን ውሃ ከወንዙ ተፋሰስ አሳልፈው ወደ ሳይናይ በረሃና ተሽካ ካናል በሚባለው መስመር ወደግብፅ ምዕራባዊ በረሃ እያሸጋገሩት ነው፡፡

ጉዳዩን በዝርዝር ያጠኑ ሰዎች ግን በአባይ ውሃ ላይ ያሉ ጥቅሞች፣ በተለይም የኢትዮጵያና የግብፅ ጥቅሞች ሊጣጣሙ የማይችሉ አይደሉም ይላሉ፡፡ ለምሳሌ ኢትዮጵያ በአባይ ተፋሰስ ያለውን የተፈጥሮ መመናመን ብታስወግድ በዝናብ እየታጠበ

በመሄድ በግብፅና ሱዳን ግድቦች ላይ ደለል እየሞላ ከፍተኛ ችግር የሚፈጥረውን አፈር መቆጣጠር ትችላለች፡፡ ከዚህም ኢትዮጵያና ግብፅ ቢያንስ እኩል ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ የአባይ ወንዝ በኢትዮጵያ ቢገደብ ሱዳን በየአመቱ የሚደርስባትን የጎርፍ መጥለቅለቅ ታስወግዳለች፣ ሁሉም አገሮች ርካሽ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ፣ ውሃው ለትነት በከፍተኛ ደረጃ ስለማይጋለጥ ቢያንስ 3 ቢልዮን ኪዩቢክ ውሃ ሊቆጠብና ለተፋሰስ አገሮች ጥቅም ሊውል ይችላል፡፡ ኢትዮጵያ በአባይ ተፋሰስ ላይ ያላት በመስኖ ሊለማ የሚችል መሬት በተነፃፃሪ እጅግ ውሱን ነው፡፡ ወንዙን በኢትዮጵያ በመገደብ የሚቆጠበው ውሃና በግብፅ አለአግባብ የሚባክነው ውሃ የኢትዮጵያን የመስኖ ልማት ፍላጎት በትክክል ሊያሟላ የሚችል ነው፡፡ የግብፅ ኢኮኖሚ በግብርና ላይ የተመሰረተ መሆኑ እየቀረ ሲሄድ ግብፅ በአንድ በኩል ውሃውን በቁጠባ ለመጠቀም የምትችልበት አቅም ይኖራታል፣ በሌላ በኩል ደግሞ የመስኖ ልማት በህዝቡ ኑሮ ላይ ወሳኝ ተፅእኖ የሌለው ይሆናል፡፡ በዚህ መልኩ በአሁኑ ወቅት ግብፅ እጅግ አባካኝ በሆነ አኳኋን እየተጠቀመችበት ያለችውን ውሃ ለማዳን ዕድሉ ይኖራሉ፡፡ በሌላ አነጋገር በሁለቱ አገሮች በአባይ ውሃ አጠቃቀም ዙሪያ ያሉት ጥቅሞች ሊጣጣሙ የሚችሉ ናቸው፡፡

ጥቅሞቹ ሊጣጣሙ የሚችሉ ሆነው ሳለ ግብፅ በጉዳዩ ላይ ስትከተል የቆየችው ፖሊሲ የውሃው ምንጭ የሆኑት አገሮች በተለይም ኢትዮጵያ በውሃው እንዳይጠቀሙ በተቀናጀ አኳኋን መስራት ነው፡፡ በዚህ ረገድ ዋነኛው መሳሪያ ሆኖ የቆየው በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ አለመረጋጋት እንዲሰፍን ማድረግ



ነው፡፡ በአካባቢያችን የነበረው አለመረጋጋት ምንጭ ግብፅ ነች ባይባልም ከዚሁ አለመረጋጋት ተጠቃሚ ሆና ስለሚታያት ግጭቶቹን በማቀጣጠልና በማባባስ ረገድ የበኩሏዋን አስተዋፅኦ አድርጋለች፡፡ ግምቷ ኢትዮጵያ በማያባራ ጦርነት ከተናጠች በልማት ላይ ማተኮር አትችልም፣ በድህነት ስለምትሰቃይ ለማልማት ብትፈልግም አትችልም፣ ስለሆነም በውሃው ሳትጠቀም ትቀራለች የሚል ነው፡፡

ግብፆች የተጠቀሙበት ሌላው ስልት ኢትዮጵያ የአባይን ውሃ ለመጠቀም የሚያስችላት ብድርና ርዳታ እንዳታገኝ ባላቸው አቅም ሁሉ መረባረብ ነው፡፡ በአረቡ አለም ባላት ተሰሚነት ማንኛውም የአረብ አገር በአባይ ውሃ ልማት ላይ ለኢትዮጵያ ምንም አይነት ብድርና ርዳታ እንዳይሰጥ ለማድረግ ችላለች፡፡ የጥላቻና የጥርጣሬ መንፈስ እንዲጠናከርም ጥረት አድርጋለች፡፡ በአረቡ አለም መሪ ተብላ መወሰዷ በሌላውም አለም ተሰሚነት ስላተረፈላት ኢትዮጵያ ከሌሎች ምንጮችም የአባይን ውሃ ለማልማት የሚያስችል ብድርና ርዳታ እንዳታገኝ ከሞላ ጎደል የተሳካ ስራ ሰርታለች፡፡ ግብፅ ስትከተል የቆየችው ፖሊሲ ኢትዮጵያ የአባይን ውሃ በራሷ እንዳታለማ በድህነትና በማያባራ ጦርነት ተጠፍራለች፣ ብድርና ርዳታ አግኝታ እንዳታለማም በሩ ተቆልፎባታል፣ ስለሆነም ኢትዮጵያ የአባይን ውሃ አይን አይኑን እያየች ከማሳለፍ በስተቀር አማራጭ አይኖራትም የሚል ነው፡፡

በተግባር ባይገለፅም ግብፅ ማንም አገር ከርስዋ ፈቃድ ውጭ በውሃው እጠቀማለሁ ካለ ወታደራዊ ርምጃ እወስዳለሁ

የምትልበት አጋጣሚም ነበር። ምድረ-በዳ የሆነችው ግብፅ በጫካ ውጊያ የሰለጠነ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ወታደራዊ ሃይል ማዘጋጀቷ ከዚህ ጋር የተያያዘ ነው የሚሉ ወገኖችም አሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ከማስፈራራት ያለፈ ስራ፣ በቀጥተኛ ወረራ መልኩ የሚገለፅ ስራ አይኖርም ብለው የሚገምቱም አሉ።

ከላይ ከተጠቀሰው አመለካከት የተለየ ሃሳብ ያላቸው ግብፃውያን እንዳሉ ግን ሊካድ አይገባውም። ኢትዮጵያ ለዘልአለሙ በአባይ ውሃ እንዳትጠቀም ቀስፎ መያዝ እንደማይቻል፣ የአባይ ውሃ ዋነኛ ምንጭ የሆነችው ኢትዮጵያ ህዝቧ ለዘልአለሙ በድርቅና በረሃብ ይርገፍ ብሎ መሄድ ተቀባይነት አይኖረውም የሚሉ አሉ። የአባይ ውሃ አጠቃቀምን በተመለከተ ያሉ ጥቅሞች ሊጣጣሙ እንደሚችሉ የሚገነዘቡ አሉ። ከዚህ በመነሳትም በቅርቡ በግብፅ፣ በሱዳንና በኢትዮጵያ መካከል በአባይ ተፋሰስ የሚካሄዱ የልማት እንቅስቃሴዎችን የሚመለከት የጋራ መግባባት ተደርሷል። ፕሮጄክቶቹ የተፈጥሮ እንክብካቤን፣ አባይ ወንዝ ላይ የተለያዩ ግድቦች ተሰርተው የሚመነጨው የኤሌክትሪክ ሃይል በኢትዮጵያ በጥቅም ላይ ሊውል ከሚችለው በላይ ሲሆን ለሱዳንና ግብፅ የሚሸጥበትንና የተለያዩ ሰፋፊ የመስኖ ስራዎችን ያካተተ ነው። ለነዚህ ፕሮጄክቶች በጋራ ብድር ርዳታና የግል ኢንቨስትመንት ማፈላለግን ያካተተ ነው።

ይህ ስምምነት በአባይ ውሃ አጠቃቀም ረገድ ልዩ ታሪካዊ ርምጃ ነው ማለት ይቻላል። በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ግብፅ የአባይ ውሃ ጥቅሞች ሊጣጣሙ እንደሚችሉ ያረጋገጠችበት



ስምምነት ነው። በአባይ ተፋሰስ ላይ የሚደረግ የአፈር ጥበቃና የተፈጥሮ እንክብካቤ፣ በአባይ ላይ የሚገነቡ የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ግድቦች ግብፅንና ሱዳንን ከኢትዮጵያ ባላነሰ ሁኔታ እንደሚጠቅሙ ያረጋገጠችበት ስምምነት ነው። ቀላል ግምት የማይሰጠው የመስኖ ልማት በኢትዮጵያ እንዲካሄድ የተስማማችበትና አልፎም ለዚሁ የሚሆን ፋይናንስ በማፈላለግ ረገድ ከኢትዮጵያ ጋር አብራ ለመሰለፍ ቃል የገባችበት ነው። ከዚህ አኳያ ሲታይ ስምምነቱ አበረታችና ልዩ ታሪካዊ ስምምነት ነው ማለት ይቻላል።

ከላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በአባይ ውሃ አጠቃቀም ጉዳይ ላይ ያለው ችግር ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተወግዷል የሚባል አይደለም። በመጀመሪያ ደረጃ ስምምነቱ ገና ተግባር ላይ የዋለ ስላልሆነ በተግባር የሚታየው ነገር ምን እንደሆነ እስኪታወቅ ድረስ እርግጠኛ ሆኖ መናገር አይቻልም። በተጨማሪም ግብፅ ያላትን አባካኝ የውሃ አጠቃቀም ለማስተካከልና፣ የአባይ ውሃ ክፍፍልን በተመለከተ ዘላቂና ፍትሃዊ ክፍፍል ለማድረግ እስካሁን በተጨባጭ የታየ ዝግጁነት የለም። በርካታ የግብፅ ፖለቲከኞች አሁንም በቆየው አስተሳሰብ ሆነው የሚዳክሩ ናቸው። ጥቅሞችን በማጣጣም ችግሩን ለመፍታት በጣም አበረታች የሆነ የመጀመሪያው ታሪካዊ ርምጃ ተወስዷል ከማለት ውጭ፣ ለዘለቄታው የሚሆን የመፍትሄ አቅጣጫ ተጠቁሟል ከማለት ውጭ ጉዳዩ አስተማማኝ መፍትሄ ተቀምጦለታል ማለት አይቻልም።

የግብፅ ኢኮኖሚ እየተጠናከረ ዴሞክራሲ ስር እየሰደደ በሄደ ቁጥር የእስልምና አክራሪነት እየተዳከመ ለዘብተኝነት እየተጠናከረ እንደሚመጣ እሙን ነው፡፡ የአክራሪነት መዳከምና የለዘብተኝነት መጠናከር በኢትዮጵያና በመካከለኛው ምስራቅ ያለውን ግንኙነት የሚያሻክረውን አንድ ችግር እንደሚቀርፍና በግብፅና በኢትዮጵያ መካከል ያለውን ግንኙነትም አዎንታዊ ተፅእኖ እንደሚያሳርፍበት ይገመታል፡፡ በተጨማሪም የግብፅ ኢኮኖሚ ሲሻሻል የአባይን ውሃ በቁጠባ ለመጠቀም የሚያስችል አቅም እንደሚፈጠርና ግብፅ በአባይና በግብርና ላይ ያላትን ጥገኝነት እንደሚቀንስ ይገመታል፡፡ ይህም በአባይ ውሃ ላይ ያሉ ጥቅሞችን ለማጣጣም ዕድል እንደሚሰጥ መገመት ይቻላል፡፡ ከዚህ አኳያ ሲታይ የግብፅ ኢኮኖሚ መሻሻሉና ለዘብተኝነትና ዴሞክራሲ በግብፅ መጠናከሩ የኢትዮጵያንም ጥቅም ይደግፋል ማለት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በአንዳንድ ግብፃውያን ዘንድ ነገሮችን በጉልበት የመፍታት ፍላጎትንም ሊያጠናክር ይችላል፡፡ በድምሩ ሲታይ ግን ለዘብተኝነት የሰፈነበትና፣ በአባይ ላይ ያላት ጥገኝነት የቀነሰ ግብፅ፣ በአክራሪነት ከምትሰቃይና በአባይ ውሃ ላይ በከፍተኛ ደረጃ ጥገኛ ከሆነች ግብፅ ይልቅ ለኢትዮጵያ የተሻለች ትሆናለች ብሎ መገመት ይቻላል፡፡

**(ለ) የግንኙነቱ ፋይዳ፣**

ኢትዮጵያ ፈጣን ልማት ማረጋገጥ ካለባት የተፈጥሮ ሃብቷን በአግባቡ መጠቀምና መንከባከብ አለባት፡፡ የኤሌክትሪክ ሃይል በማመንጨት የራስዋን ፍላጎት ከማሟላት አልፋ ሱዳንና



ግብፅን ጨምሮ ለጎረቤት አገሮች በመሸጥ የውጭ ምንዛሪ በማግኘት በአፍሪካ ቀንድ ጠንካራ ኢኮኖሚያዊ ትስስር እንዲኖር ማድረግ አለባት፡፡ በመስኖ ሊለማ የሚችለውን መሬት ማልማት፣ አፈርዋንና የተፈጥሮ ሃብቷን መንከባከብ አለባት፡፡ ቁጥሩ እየጨመረ ለሚሄድ ህዝቧና ለኢንዱስትሪ ልማትዋ በቂ ውሃ ማቅረብ አለባት፡፡ በአባይ ተፋሰስ ላይ እነዚህን ግቦች ለማሳካት የሚያስችል ስራ ካልተሰራ የተባሉት የልማት ስራዎች ሊከናወኑ አይችሉም፡፡ ስለሆነም ኢትዮጵያ ፈጣን ልማትን ማረጋገጥ የምትችለው በወንዞቿዋ፣ በአባይ ተፋሰስ ወንዞች ጭምር መጠቀም ስትችል ብቻ ነው፡፡ ይህን የግብፅን መሰረታዊ ጥቅም በማይነካ፣ ጥቅሞችን በሚያጣጥም አኳኋን ማድረግ ይቻላል፣ ይገባልም፡፡ ይህን ማድረግ ካልተቻለ ግን በልማታችንና በአገራዊ ደህንነታችን ላይ ከፍተኛ ማነቆ መሆኑ አይቀርም፡፡

ግብፅ በአንድ በኩል በአባይ ላይ በፍትሃዊ አኳኋን ጥቅሞችን አጣጥሞ የመሄድ ፍላጎት ካደረባት፣ ለልማታችን የሚሆን ፋይናንስ በማሰባሰብ ረገድ የነበራትን እንቅፋትነት ልታስቀር ከዚያም አልፎ ደጋፊ ልትሆን ትችላለች፡፡ በአፍሪካ ቀንድ ሰላምና መረጋጋት እንዲሰፍን በጎ አስተዋፅኦ ማድረግ ትችላለች፡፡ በተነፃፃሪ ሰፊ ገበያ ያላት ለመሆኗ በዚህም ረገድ ለልማታችን ከፍተኛ አስተዋፅኦ ልታበረክት ትችላለች፡፡ በግብፅ ለዘብተኝነትና ዴሞክራሲ ቢስፋፉ በመካከለኛው ምስራቅ በአጠቃላይ አክራሪነት ይዳከማል፣ ይህም ለደህንነታችን ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡ በአጠቃላይ ከግብፅ ጋር የሚኖረን ግንኙነት

በአገራዊ ደህንነታችን ላይ እጅግ ከፍተኛ ትርጉም ያለው ሲሆን በልማታችን ላይ የሚኖረው ተፅእኖም ከፍተኛ ነው።

**(ሐ) ግብፅን በተመለከተ የምንከተለው ፖሊሲ፣**

ከግብፅ ጋር በሚኖረን ግንኙነት ተወደደም ተጠላም የአባይ ጉዳይ የግንኙነቱ ማዕከል መሆኑ አይቀርም። በዚህም ረገድ የምንከተለው ፖሊሲ የአባይ ጉዳይ ጥቅሞችን በማጣጣም መርህ በሰላምና በድርድር የልማት እንቅስቃሴያችንን በማይጎዳ መልኩ እንዲፈታ፣ በዚህ ዙሪያ የሚነሱ ጉዳዮች በቂ ጊዜ በሚሰጥ አኳኋን እንዲታዩ ማድረግ ይሆናል። ከዚህ ጎን ለጎን በዚህ ጉዳይ ሊከሰቱ ለሚችሉ ስጋቶች ያለንን ተጋላጭነት መቀነስ የሚያስችል ፖሊሲ ሊኖረን ይገባል።

እንደሌላው የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ሁሉ ከግብፅ ጋር ባለን ግንኙነትም ወሳኝ የሚሆነው በውስጣችን የሚሰራ ስራ ነው። ዴሞክራሲንና መቻቻልን እውን በማድረግ የውስጥ ቅራኔዎቻችን በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ ካደረግን፣ ከጎረቤቶቻችን ጋር ያሉን ግንኙነቶች ግጭትን በሚያስወግድ አኳኋን ከፈታንና ጎረቤቶቻችን ከልማታችንና ከዴሞክራሲያችን ከጥቅም በስተቀር የሚደርስባቸው ጉዳት እንደማይኖር ካረጋገጥን፣ ይህንኑ ከስሜትና ከጊዜያዊ ጥቅም ባሻገር ሄደን ከፈፀምን በአባይ ጉዳይ ዙሪያ ለሚነሱ ስጋቶች ያለን ተጋላጭነት በጣም ከፍተኛ በሆነ ደረጃ ይቀንሳል። ከማያባራ ጦርነት ወጥተን በልማት ላይ ማተኮር እንችላለን። በዋነኛነት የህዝባችንን ጉልበት በመጠቀም በሂደትም እያደገ የሚሄድ



ሃብታችንን ተጠቅመን አገራችንን የአባይን ተፋሰስ ጭምር ማልማት እንችላለን። በዚህ ላይ ተመስርተን የመከላከል አቅማችንን ሊመጣ ከሚችል ጥቃት ትይዩ እየዳበረ እንዲሄድ ማድረግ ይኖርብናል።

ከላይ በተጠቀሰው አኳኋን በውስጣችን የምንሰራው ስራ በራሳችን አቅም ልማታችንን ለማፋጠን ልንሄድ በምንችልበት መጠን እንድንራመድ የሚያስችለን ከመሆኑም በላይ የአባይን ጉዳይ ጥቅሞችን ለማጣጣም በሚያስችል አኳኋን ለመፍታት የተመቻቸ ሁኔታን ይፈጥርልናል። ግብፃውያን ኢትዮጵያን በማያባራ ጦርነትና በድህነት በመጥመድ በአባይ ውሃ እንዳትጠቀም ማድረግ እንደማይቻል እርግጠኛ እንዲሆኑ በማድረግ ለዘለቄታዊና ፍትሃዊ መፍትሄ ዝግጁ እንዲሆኑ ሊያደርጋቸው ይችላል። የሃይልና የማስፈራራት አማራጭ ሊሳካ እንደማይችል ተገንዝበው የድርድርና ጥቅሞችን የማጣጣም አቅጣጫ እንዲከተሉ ሊያበረታታቸው ይችላል።

በውስጣችን ከምንሰራው ስራ በተጨማሪ በአባይ ጉዳይ ላይ ፍትሃዊ ክፍፍልን የሚደግፍ ከባቢያዊና አለማዊ ሁኔታ እንዲፈጠር ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል። አላማችን እኛ ተጠቅመን ሌሎችን ለማጥፋት እንዳልሆነ፣ የኛን የልማት ፍላጎት የሚያሟላ፣ ጥቅሞችን የሚያጣጥም መፍትሄ መሻት እንደሆነና ይህም አማራጭ እንዳለ በማሳየት ላይ ያተኮረ መሆን ይኖርበታል። ኢትዮጵያ የአባይ ውሃ ዋነኛ ምንጭ ሆኖ እያለችና፣ ህዝቧ በረሃብና በድርቅ እየተገረፈ ባለበት ሁኔታ የአባይን ውሃ መጠቀም አይገባትም

የሚል አመለካከት ፍፁም ኢ-ፍትሃዊና ተቀባይነት የሌለው እንደሆነ በማሳመን ላይ ያተኮረ መሆን አለበት፡፡ ይህንኑ ለዋና ዋናዎቹ ርዳታ ሰጪና አበዳሪ ድርጅቶችና አገሮች በማስረዳት ለፍትሃዊ የአባይ ውሃ ክፍፍል የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱና፣ ትብብራቸውን እንዳይነፍጉን የማድረግ ፖሊሲ መከተል አለብን፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ይህንኑ አላማ ለአፍሪካውያን ወንድሞቻችን በማስረዳት የፖለቲካና ዲፕሎማሲ ድጋፋቸውን እንዲሰጡን የሚያደርግ ፖሊሲ ሊኖረን ይገባል፡፡ የግብፅ ህዝብና የአረቡ አለምም ይህንኑ አላማችን ተገንዝቦ እንዲደግፈን ቢያንስ ተቃውሞውንና ጥርጣሬውን እንዲያነሳ ጥረት ማድረግ አለብን፡፡

በቅርቡ በሱዳን፣ በኢትዮጵያና በግብፅ መካከል የተደረሰበትን መግባባት በተሟላ አኳኋን ተግባራዊ ማድረግ የፖሊሲያችን አንድ መሰረታዊ ማዕከል መሆን አለበት፡፡ በዚህ ላይ በመመስረት በአገሮቹ መካከል የመተማመን መንፈስ እንዲፈጠር ጥረት ማድረግ አለብን፡፡ ደረጃ በደረጃ የውሃ አጠቃቀም ቁጠባና ፍትሃዊ ክፍፍል ወደሚጨምርበት ደረጃ ማድረስ አለብን፡፡ ይህ ስምምነት የፈጠረው ምቹ ሁኔታ ሳንቸኩልና ሳንጣደፍ የማስፋት ስራ መስራት ይኖርብናል፡፡ የኢትዮጵያና የግብፅ ህዝቦች የአካባቢያችን አገሮችና የአለምም ማህበረሰብ ይህንን ስምምነት በመደገፍ በአባይ ጉዳይ ላይ በጎ ተፅእኖ ማሳረፍ እንዲጀምሩ መረባረብ አለብን፡፡ ጊዜና ፍትህ በኢትዮጵያ የልማት አጀንዳ ጋር የተሰለፉ መሆናቸውን ታሳቢ ያደረገ ፖሊሲና የፖሊሲ አፈፃፀም ሊኖረን ይገባል፡፡



የአባይን ጉዳይ በዚሁ መልኩ በመፍታት ማዕቀፍ ውስጥ በግብፅ ልማትን ለማፋጠንና ለዘብተኝነትንና ዴሞክራሲን ለማስፈን የሚደረገውን ጥረት እንደምንደግፍ ማሳወቅና በተግባርም ማሳየት አለብን፡፡ እያደገ በመሄድ ላይ ካለው የግብፅ ገበያ ተጠቃሚ ለመሆንና አገራዊ ደረጃ በደረጃዎች ደህንነታችንን ታሳቢ ባደረገ አኳኋን ከግብፅ ጋር ጠንካራ የኢኮኖሚ ትስስር መፍጠር አለብን፡፡ በአለማወቅና በጥርጣሬ ላይ የተመሰረተን ፖሊሲ በጥናት በምርምርና በእውቀት ላይ በተመሰረተ ፖሊሲ መተካት አለብን፡፡ ከግብፅ ጋር ያለን ግንኙነት ትእግስት፣ አርቆ አስተዋይነትና ሌላውን ነገር ሁሉ ወደጎን ብሎ በዋናው የአገራዊ ጥቅምና ህልውና የልማት፣ የዴሞክራሲና የሰላም ጉዳዮች ላይ በማተኮር የመፍታት ተክዕሎ የህዝባችንና የመንግስታችን ብቃት ከሚላኩባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች አንዱ መሆኑን የተገነዘበ ፖሊሲና የፖሊሲ አፈፃፀም እንዲኖር ማድረግ አለብን፡፡

## 3.3. ከአረብ ባህረ-ሰላጤ አገሮች ጋር የሚኖረን ግንኙነት፣

### (ሀ) የግንኙነቱ ታሪካዊ አመጣጥና ችግሮች፣

በአረብ ባህረ-ሰላጤ ከሚገኙት አገሮች መካከል ከኢትዮጵያ ጋር ጥብቅ የታሪክ ትስስር ያላት አገር የመን ነች፡፡ የመን በአንድ ወቅት የአክሱም ግዛት አካል እንደነበረች ታሪክ ይዘግባል፡፡ ከዚያም በፊትና በኋላ በሁለቱ አገሮች መካከል ጠንካራ የታሪክ ትስስር እንዳለም ይታወቃል፡፡ የመናውያን በኢትዮጵያ በንግድ ስራ ላይ የመሰማራት ሰፊ ልምድ አላቸው፡፡ ከዚህ ጋር

በተያያዘም በየመን ስለኢትዮጵያ ምናልባትም ከሁሉም የአረብ ባህረ-ሰላጤ አገሮች የተሻለ አዎንታዊ አመለካከት አለ:: ከሳኡዲ አረቢያ ጋር ያለውም ትስስር በተመሳሳይ መልክ የቆየ ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ ከአንዳንድ የአካባቢው አገሮች ጋር በቂ ትውውቅም ሆነ ጠንካራ ታሪካዊ ትስስር አለ ማለት አይቻልም::

በኢትዮጵያና በአረብ ባህረ-ሰላጤ አገሮች መካከል ያለው ትስስር ከአገር አገር የተለያየ ሲሆን ችግሮቹም በዚያው መጠን የተለያዩ ናቸው:: ይሁንና በአጠቃላይ እንደሚከተለው ሊቀመጡ የሚችሉ ችግሮችም አሉ:: ግብፅ በአረብ አገሮች ባላት ተሰሚነት ምክንያት ከኢትዮጵያ ጋር ጠንካራ ግንኙነት ከማድረግ የሚቆጠቡ አገሮች አሉ:: ከእስልምና አክራሪነት ጋር በተያያዘና በኢትዮጵያ ከነበረው የሃይማኖት እኩልነት በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ አለመሆን ጋር በተያያዘ ችግር ያለባቸውም አገሮች አሉ:: በአረቦችና በእስራኤል መካከል ካለው ቅራኔ ጋር ተያይዞም ኢትዮጵያን በጥርጣሬና በጥላቻ የሚመለከቱም አሉ:: ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች ስለኢትዮጵያ ትክክለኛና የተሟላ እውቀት ካለማግኘታቸው ጋር ተዳምሮ ችግር የሚፈጥርባቸው አገሮችም አሉ:: እነዚህ አገሮች ስለአገራችን ያላቸው እውቀት ውሱን መሆኑም በግንኙነቶች አለመጠናከር ላይ ያለው ተፅእኖ በጣም ትልቅ እንደሆነ ሊሰመርበት ይገባል::

### (ለ) የግንኙነቱ ፋይዳ፣

ብዙዎቹ የአረብ ባህረ-ሰላጤ አገሮች በነዳጅ ዘይት የበለፀጉ ናቸው፣ ስለሆነም በአገራችን ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው



የኢንቨስትመንት ምንጭ ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው፣ በልማት ፋይናንስም ረገድም የማይናቅ አስተዋፅኦ ማበርከት ይችላሉ:: እነዚህ አገሮች ለአገራችን የተለያዩ የግብርና ምርቶች ሰፊ ገበያ ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው:: በጥቅሉ እነዚህ አገሮች በልማታችን ላይ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ሊኖራቸው የሚችሉ አገሮች ናቸው::

ከደህንነት አኳያ የአረብ ባህረ-ሰላጤና የአፍሪካ ቀንድ ሰላምና መረጋጋት የተያያዙና ተደጋጋፊ በመሆናቸው የአካባቢውን ሰላምና መረጋጋት በጋራ ማረጋገጥ ለአገራዊ ደህንነታችን ከፍተኛ ፋይዳ ያለው ነገር ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ በአካባቢው የአክራሪነትና የሽብርተኝነት እየተጠናከረ መሄድ ለአገራዊ ደህንነታችን ከፍተኛ የስጋት ምንጭ ሊሆን የሚችል ነው:: በድምር ሲታይ የአረብ ባህረ-ሰላጤ አገሮች ከአገራችን ልማትም ሆነ አገራዊ ደህንነት አኳያ ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ አገሮች በመሆናቸው ከነዚህ አገሮች ጋር ግንኙነታችንን ማሻሻልና ማጠናከር በውጭ ጉዳይ ፖሊሲያችን ከፍተኛ ግምት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው::

### (ሐ) የአረብ ባህረ-ሰላጤ አገሮችን በሚመለከት የምንከተለው ፖሊሲ፣

እነዚህን አገሮች በተመለከተ በውስጣችን ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ለአደጋ ተጋላጭነታችንን ከመቀነስ ባሻገር ስለነዚህ አገሮች ያለንን እውቀት ዝቅተኛነት ማሻሻል ነው:: የነዚህ አገሮች ሁኔታና ፖሊሲ በሚመለከት እንኳን ህዝቡ ሙያተኞችም በቂና የተሟላ እውቀት አላቸው ማለት

አይቻልም። በዚህ ረገድ የሚካሄድ የረባ የምርምርና የጥናት ስራም አለ ለማለት አይቻልም። ስለሆነም ግንኙነቱ በስሜቶችና በእውቀት ላይ ባልተመሰረቱ ድምዳሜዎች ላይ የሚመረኩዝበት ሁኔታ ያጋጥማል። ይህንን በተሟላ ምርምርና ጥናት በተመሰረተ እውቀት መተካት፣ ለዚህም ፖሊሲ አውጭዎችና ፈፃሚዎች ከዚህም አልፎ ህዝቡ በየደረጃው የተሻለ እውቀት እንዲይዙ ጥረት ማድረግ ይኖርበታል።

የአካባቢው አገሮች በልማታችን ላይ ሊጫወቱት የሚችሉትን ከፍተኛ ሚና ግምት ውስጥ በማስገባት በነዚህ አገሮች ገበያዎች ውስጥ በሰፊው ለመግባት፣ ከነዚህ አገሮች ኢንቨስትመንትን በሰፊው ለመሳብና ከተቻለም የልማት ፋይናንስ ትብብር ለማግኘት መጣጣርን ማዕከል ያደረገ ፖሊሲ መከተል አለብን። በአባይ ጉዳይ ላይ ያለንን ፖሊሲ በማስረዳት፣ በሃይማኖት እኩልነት ላይ ያለን ፖሊሲና ተግባር በማስጨበጥና የጋራ የኢኮኖሚና የሰላም ጥቅሞችን በማሳየት ለኢኮኖሚያዊ ትስስራችን ማነቆ የሆኑትን ጉዳዮች በመፍታት ላይ ያተኮረ የዲፕሎማሲ ስራ መስራት አለብን። የአካባቢው መንግስታትና ህዝቦች በኢትዮጵያ ላይ ያላቸውን የተዛባ አመለካከትና ዝቅተኛ እውቀት ለማስተካከል እጅግ ሰፊ ጥረትና ዘመቻ ማካሄድ፣ በዚህ ረገድ የአረብ ሚድያ በዝምታም ሆነ የተዛባ ዘገባን በማቅረብ የሚጫወተውን አሉታዊ ሚና ለማስተካከል መጣጣር ይኖርብናል።

ለአካባቢው ሰላምና መረጋጋት እንቅፋት የሚሆኑትን ነገሮች ለይቶ ለማስወገድ ከአካባቢው አገሮች ጋር በምክክርና



በመደጋገፍ ለመስራት የሚያስችል ፖሊሲ ሊኖረን ይገባል። አካባቢው የአለም ትላልቅ አገሮች በትኩረት የሚከታተሉትና ሰላምና መረጋጋትን ለመፍጠር የሚረባረቡበት በመሆኑና ኢትዮጵያም በዚህ ረገድ የማይናቅ አስተዋፅኦ ልታበረክት የምትችል ስለሆነች፣ ለአካባቢው ሰላምና መረጋጋት እንዲሰፍን በጎ አስተዋፅኦ ማበርከት ከሚችሉ አገሮች ጋር ሁሉ ተባብሮ ለመስራት የሚያስችለን ፖሊሲ መቀየስ አለብን።

## 3.4. ከሰሜን አፍሪካ አገሮች ጋር የሚኖረን ግንኙነት፣

ብዙዎቹ የሰሜን አፍሪካ አገሮች በአፍሪካ መድረኮች ከኢትዮጵያ ጋር በጎ የሆነ የፖለቲካ የዲፕሎማሲ ትስስር ያላቸው ናቸው። በተለይም እንደአልጄሪያ ያሉት በአፍሪካ የፀረ-ቅኝ አገዛዝ ትግል ታሪክ ከፍተኛ ሚና የተጫወቱ በመሆኑ ከኢትዮጵያ ጋር በልዩ ልዩ ጉዳዮች የጋራ አቋም በመያዝ ሲደጋገፉ ቆይተዋል። ምንም እንኳ ከመካከለኛው ምስራቅ ጋር ባለን ግንኙነት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ የሚያሳድሩት ነገሮች በነሱም ላይ የማይናቅ አሉታዊ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ቢሆንም በአጠቃላይ ሲታይ ብዙዎቹ አገሮች ስለአገራችን በጎ አመለካከት ያላቸው ናቸው። በኢኮኖሚ መስክ ለመተባበር ያለው ዕድል በቀላሉ የማይገመት ቢሆንም እስካሁን ፋይዳ ያለው የኢኮኖሚ ትስስር ተፈጥሯል ማለት አይቻልም።

ከነዚህ አገሮች ጋር የሚኖረን ትስስር በዋነኛነት በፖለቲካና በዲፕሎማሲ ላይ ያተኮረና በአፍሪካ ህብረት ማዕቀፍ ውስጥ

የሚከናወን መሆኑ አይቀርም፡፡ ይሁንና ከእነዚህ አገሮች ጋር ያለንና የምናጠናክረው በጎ ግንኙነት በአረቡ አለምም አዎንታዊ ተፅእኖ እንዲያሳርፍ ጥረት ማድረግ ይኖርብናል፡፡ በተጨማሪም ሁኔታዎች በፈቀዱ መጠን በአገራችንና በነዚህ አገሮች መካከል የኢኮኖሚ ትስስርን ለመፍጠርና ለማጠናከር ከፍተኛ ጥረት መደረግ ይኖርበታል፡፡

### 3.5. ከእስራኤል ጋር የሚኖረን ግንኙነት፣

እንደሌሎቹ የመካከለኛ ምስራቅ አገሮች ሁሉ ከእስራኤልም ጋር የቆየ ታሪካዊ ግንኙነት እንዳለንና በርካታ የይሁዲ ሃይማኖት ተከታይ ኢትዮጵያውያን እንደነበሩና ብዙዎቹም በአሁኑ ወቅት በእስራኤል ተቀማጭ እንደሆኑ ይታወቃል፡፡ ከእስራኤል መንግስትም ጋር በመሃል ግንኙነቱ የተቋረጠበት ሁኔታ የነበረ ቢሆንም በአጠቃላይ ጤናማ የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ግንኙነት ተፈጥሮ ቆይቷል ማለት ይቻላል፡፡

ከኢትዮጵያውያን ቤተ-እስራኤሎች ወደ እስራኤል መፍለስ ጋር ተያይዞ በኢትዮጵያና በእስራኤል ግንኙነት ላይ መለስተኛ ቅራኔ ተፈጥሮ የነበረ ቢሆንም ይህ ጉዳይ የኢትዮጵያ ህገ-መንግስትን መሰረት ካደረገው የእያንዳንዱ ዜጋ በተናጠል በነፃ የመንቀሳቀስ መብቱን በሚያስከብር አኳኋን እንዲፈታ በመደረጉ ቅራኔው ተወግዷል፡፡ በእስራኤልና በኢትዮጵያ ግንኙነት ላይ ያለው ዋናው ችግር የእስራኤሎችና የአረቦች ቅራኔ የሚፈጥረበት ችግር ነው፡፡ አንዳንድ የአረብ አገሮች፣ ከእስራኤል ጠንካራ



ዲፕሎማሲያዊ ትስስር ያላቸው አገሮችም ጭምር ኢትዮጵያ ከእስራኤል ጋር ጤናማ ግንኙነት መመስረቷን ይቃወማሉ፡፡ በጭፍን አንደኛውን ደግፈን ሌላውን እንድንቃወም ይፈልጋሉ፡፡ በእስራኤሎችም በኩል ተመሳሳይ አመለካከቶች የሚንፀባረቁበት ሁኔታ አለ፡፡

የእስራኤል ህዝብ ቁጥሩ ትንሽ ቢሆንም አገሪቱ የበለፀገ ኢኮኖሚ የተራቀቀ ቴክኖሎጂ ያላት አገር ነች፡፡ እስራኤል ለምርቶቻችን ገበያ በመሆንና በኢንቨስትመንትና በተለያዩ ቴክኒካዊ ድጋፎች ለልማታችን ከፍተኛ አስተዋፅኦ ልታበረክት የምትችል አገር ነች፡፡ ከደህንነታችንም አኳያ ከእስራኤል የሚመነጭ ይህ ነው የሚባል የደህንነት ስጋት የለብንም፣ ይልቁንም ደህንነታችንን ከማጠናከር አኳያ እስራኤል በጎ አስተዋፅኦ ሊኖራት ይችላል፡፡ በመሆኑም በተለይ ከልማታችን አኳያና በተወሰነ ደረጃም ከደህንነት አኳያ ከእስራኤል ጋር ጤናማና ጠንካራ ግንኙነት ልንመሰርት ይገባናል፡፡

ከእስራኤልም ጋር ያለን ግንኙነት መነሻውና መዳረሻው በግልፅ የተቀመጠው አገራዊ ጥቅማችንና የልማትና የአገራዊ ህልውና አጀንዳችን ሊሆን ይገባዋል፡፡ እስራኤል በዋነኛነት በልማችን ላይ በተወሰነ ደረጃም በደህንነታችን ላይ በጎ አስተዋፅኦ ሊኖራት ስለሚችል ጠንካራ ትስስር መፍጠር አገራዊ ጥቅማችንን ያስጠብቃል፣ ስለሆነም ይህንን ለማድረግ የሚያስችለንን ፖሊሲ ቀርፀን ተግባራዊ ማድረግ አለብን፡፡ እስካሁን በኢኮኖሚው ዘርፍ ይህ ነው የሚባል ስራ ስላልተሰራ፣ በንግድ፣ በኢንቨስትመንትና በቴክኒካዊ ድጋፍ ላይ ያተኮረ ከፍተኛ ርብርብ ማድረግ

ይኖርብናል።

በእስራኤሎችና በአረቦች መካከል ያለው ቅራኔ በዋነኛነት ሁለቱን የሚመለከት ስለሆነ የኢትዮጵያ አላማ አገራዊ ጥቅሟን ለማስጠበቅ ከሁለቱም ወገኖች ጋር ጥቅሟን የሚያስጠብቅ ግንኙነት መመስረት እንጂ አንደኛውን ወይም ሌላኛውን በማስደሰት ወይም በማስቆጣት ላይ የተመሰረተ ፖሊሲ ማስቀመጥ አይገባትም።

ከዚህ በመነሳት የአለም አቀፍ ህግ መከበሩ ቅራኔዎች በሰላም መፈታታቸው ለሰላምና መረጋጋት ብሎም ለአገራዊ ጥቅማችን መከበር መሰረት በመሆኑ በፍልስጥኤም ጉዳይ በነዚህ መርሆዎች መሰረት እንዲፈታ መደገፍ ይኖርብናል። የፍልስጥኤም ህዝብ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን መብቱ እንዲከበርና ጉዳዩም በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ እንዲፈታ መደገፍ አለብን። ይህንን አቋም በመያዛችን ማንንም የሚያስቆጣ መሆን የለበትም፣ ቢያስቆጣም ባያስቆጣም አገራዊ ጥቅማችንን የሚያስጠብቅ ፖሊሲ ስለሆነ ልንከተለው ይገባናል። በሌላ በኩል ደግሞ በአረቦችና በእስራኤል መካከል ያለው ቅራኔ ከፍና ዝቅ ባለ ቁጥር እኛ ከአረቦችና ከእስራኤሎች ጋር ያለን ግንኙነት አብሮ ከፍና ዝቅ ማለት አለበት ማለት አይደለም። የቅራኔውም ከፍና ዝቅ ማለት ቢኖርም ባይኖርም ቀደም ሲል በተዘረዘረው አኳኋን አገራዊ ጥቅማችንን ለማስጠበቅ የቀየስነውን ፖሊሲ፣ ከሁለቱም ጋር መተባበርን ልናጠናክር ይገባል። ትክክለኛና ከነፋስ ጋር ግራና ቀኝ የማይላጋ ፖሊሲ ይዘን መቀጠል አለብን። ሁለቱም ወገኖች



ይህንን እንዲያውቁልንና እንዲቀበሉልን ባለን አቅም ሁሉ ጥረት ማድረግ አለብን።

## 3.6. ከቱርክና ከኢራን ጋር የሚኖረን ግንኙነት፣

ቱርክ በሜዲትራኒያንና በመካከለኛው ምስራቅ አካባቢ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ህዝብና በተነፃፃሪ የዳበረ ኢኮኖሚ ካላቸው አገሮች ውስጥ አንዷ ነች። ዴሞክራሲን እውን ለማድረግ ከሚጣጣሩት አገሮችም አንዷ ነች። ከመካከለኛው ምስራቅና የአውሮ- ድልድይ ተደርጋ የምትወሰድ አገር ነች። በአሁኑ ወቅት በቱርክና በኛ አገር መካከል መልካም ግንኙነትን የሚያደናቅፍ ነገር የለም። ከቱርክ በኩል የሚመጣ የአገራዊ ደህንነት ስጋት የለም። ሰፊ ገበያዋና በተነፃፃሪ የዳበረ ኢኮኖሚዋ ለልማታችን ትልቅ አስተዋፅኦ ሊኖረው የሚችል ነው። በውሃ አጠቃቀም ረገድም ፍትሃዊ አሰራር መኖሩን የምትደግፍ አክራሪነትን አጥብቃ የምትቃወምና ለኢትዮጵያ በጎ አመለካከት ያላት አገር ነች። በዚህ ረገድ ችግር አለ ከተባለ ሰፊ የኢኮኖሚያዊ ትስስር ዕድል እያለ እስከዛሬ ድረስ ጫፍም ያልተነካ መሆኑ ብቻ ነው።

ቱርክ በአቅራቢያችን የሚገኝ ሰፊ ገበያ ያላት፣ በኢኮኖሚ ልማት ረገድ ሰፊና የቅርብ ጊዜ ልምድ፣ በአንዳንድ መስኮችም የኢንቨስትመንትና የቴክኒካዊ ድጋፍ ምንጭ ልትሆን የምትችል፣ ለኢትዮጵያም በጎ አመለካከት ያላት አገር በመሆንዋ በኢኮኖሚ ላይ ያተኮረ ጠንካራ ትስስር መፍጠርን ማዕከል ያደረገ ፖሊሲ

ቀርፀን መረባረብ ይገባናል። የቱርክ ባለሃብቶችን ወደአገራችን ለመሳብ፣ ምርቶቻችንን ለማስተዋወቅና በሁለቱ አገሮች የግል ባለሃብቶች መካከል ጠንካራ ትስስር እንዲፈጠር ለማድረግ ሰፊ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ማካሄድ አለብን። በሁለቱ መንግስታት መካከል ያለውን የዲፕሎማሲና የፖለቲካ ትብብር ለማጠናከርና በተለያዩ መስኮችም የቴክኒክ ድጋፍ ለማግኘት አበርትተን መስራት አለብን። ከቱርክ ጋር ያለን ግንኙነት በከፍተኛ ደረጃ መጠናከር የሚችልና በአግባቡ ያልተዳሰሰ ግንኙነት እንደሆነ አድርገን በመቁጠር በቂ ትኩረት ሰጥተን ልንንቀሳቀስበት ይገባል።

ኢራንም በመካከለኛው ምስራቅ ሰፊ ህዝብና በተነፃፃሪነት የዳበረ ኢኮኖሚ ካላቸው አገሮች አንዷ ናት። ከአክራሪነት ጋር ተያይዞ በተዘዋዋሪ መንገድ ሊነሳ ከሚችል ችግር በስተቀር ከኢራን የሚመነጭ የደህንነት ስጋት የለንም። በሁለቱ አገሮች መካከል የኢኮኖሚ ግንኙነትን ለማጠናከር የሚቻልበትም ዕድል አለ። ይህንኑ በመገንዘብ ከኢራን ጋር የንግድና የኢኮኖሚ ትስስርን በማጎልበት ላይ ያተኮረ ፖሊሲ ቀርፀን ተግባራዊ ማድረግ ይኖርብናል።

# 4. አውሮ-፣



## 4.1.የአውሮ- ህብረት፣

የአውሮ- ህብረት በአሁኑ ወቅት 15 እጅግ የበለፀጉ የአውሮ- አገሮች ያካተተ እጅግ ሰፊ ገበያ ሲሆን በቅርቡ 10 ተጨማሪ የአውሮ- አገሮችን በመጨመር 25 አገሮችን ያካተተ ህብረት እንደሚሆን ይገመታል። ይህ ገበያ በአሁኑ ወቅት በስፋቱና በብልፅግናው ከአሜሪካ ጋር የሚመጣጠን ገበያ ሲሆን በሂደት ሊበልጥም እንደሚችል ይገመታል። የግሎባላይዜሽንን የኢኮኖሚ ህግጋት በመወሰን ረገድ ከአሜሪካ ቀጥሎ ወሳኝ አስተዋፅኦ ያለው ገበያ ነው። ሰላምና ዴሞክራሲን ማስፈን እንደዋነኛ አላማ አድርጎ የተነሳ ህብረት ነው። የህብረቱ አገሮች በተናጠል ከሚሰጡን ርዳታ ጋር ተደምሮ ሲታይ የአገራችን ዋነኛ የርዳታ ምንጭ ይህ ነው። ዋነኛ ገበያችንም ነው። ኢንቨስትመንትን በመሳብ ረገድ ይህ ነው የሚባል ውጤት ባናስገኝም፣ በጣም ቁልፍ የውጭ ኢንቨስትመንት ምንጭ ሆኖ ሊያገለግል የሚችል ነው። ከኢኮኖሚ ልማት አኳያ ሲታይ ለኛ እጅግ ወሳኝ ከሆኑት አካባቢዎችም አንዱ ነው። ከደህንነትም አኳያ በአሁኑ ወቅት ከዚህ አካባቢ የሚመነጭ አንዳችም የደህንነት ስጋት የለብንም። ይልቁንም የአለም አቀፍ ህግ እንዲከበር፣ ሰላምና ዴሞክራሲ እንዲሰፍን የማድረግ አላማ ስላላቸው በዚህም ረገድ ደጋፊና አጋር ሊሆኑን የሚችሉ ናቸው።

ከአውሮ- ጋር ያለን ግንኙነት በተመለከተ ዋናው ችግር ግንኙነቱ ሊፈጥርልን የሚችለውን ዕድል በሚገባ አሟጠን

ያልተጠቀምን መሆናችን ነው። ይህ የልማት ብድርና ርዳታን በማፈላለግና በአግባቡ ጥቅም ላይ በማዋል መልኩም የሚገለፅ ቢሆንም በዋነኛነት ኢንቨስትመንትና ንግድን በማስፋፋት መልኩ የሚገለፅ ነው። ለዚህ ዋነኛው ምክንያት የኢትዮጵያ ገፅታ በአውሮ- እጅግ የተበላሸ፣ ኢትዮጵያን የማያባራ ጦርነትና የአስከፊ ድህነት አገር እንጅ የንግድና ኢንቨስትመንት መዳረሻ አድርጎ የማይመለከት አስተሳሰብ ስላለና ይህንን ገፅታ ለመቀየር ብቃት ያለው ስራ ስላልተሰራ ነው። በተጨማሪም ኢንቨስትመንትን ለመሳብ የሚያስችል የተመቻቸ ሁኔታና በእቅድ የሚመራ የተጠናከረ ስራ አልተሰራም።

የአውሮ- ህብረት የግሎባላይዘሽን ህግጋትን በመቅረፅ ረገድ ወሳኝ ሚና ካላቸው ሃይሎች አንዱ በመሆኑ በዚህ ረገድ የግሎባላይዘሽን ጎጂ ገፅታዎች አንዱ ምንጭ ተደርጎ ሊወሰድም ይችላል። በዚህ ረገድ በቅርቡ የአውሮ- ህብረት ለኢትዮጵያና ሌሎች ድሀ አገሮች ገበያውን ያለአንዳች የታሪፍና የኮታ ገደብ ክፍት እንዲሆን መወሰኑ በበጎ ገፅታው የሚጠቀስ ታላቅ ርምጃ ነው። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በገበያ ልንወዳደር በምንችልባቸው መስኮች ለኩባንያዎቹ የሚሰጠው ድጎማና ሌሎችም የንግድና ኢንቨስትመንት አሰራሮች በድሀ አገሮች ልማት ላይ ጎጂ ተፅእኖ ማሳረፋቸው አልቀረም። በሁለትዮሽ ግንኙነት መስክ እኛ ከሁኔታችን ጋር የሚጣጣም የኢኮኖሚና የፖለቲካ አቅጣጫ በምንቀይስበት ወቅት ከዚህ የተለየ አማራጭ ለማራመድ ተፅእኖ በማሳረፍ መልኩ የሚፈጠር መለስተኛ ቅራኔም ያጋጥማል።



ከአውሮ- ህብረት ጋር ያለንን ግንኙነት ለማጠናከርና ለልማታችንና ለደህንነታችን ያለውን እጅግ የላቀ አስተዋፅኦ አሟጦ ለመጠቀም የሚያስችለን ዋናው ስራ በውስጣችን የሚሰራው ነው። የተስተካከለ የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ስትራተጅ ቀርፀን ባለን አቅም ሁሉ መረባረብ የመጀመሪያውና ወሳኙም ርምጃ ነው። በዚህ ላይ ተመስርተን የሚጎድለንንና ከአውሮ- ልናገኝ የምንችለውን ነገር ለይተን ማስቀመጥ ቀጥሎ የሚመጣው ጉዳይ ነው። በዚህ ላይ ተመስርተን ከአውሮ- መንግስታት ጋር መመካከርና ስትራተጅዎቻችንንም ማስረዳት አለብን። የልማት ስትራተጅያችን በግሎባላይዘሽን ማዕቀፍ የሚፈፀምና ዴሞክራሲን መሰረት ያደረገ በመሆኑ ከአውሮ- ጋር መሰረታዊ የጥቅም ግጭት የሚፈጥር አይሆንም። ይሁንና መለስተኛ ቅራኔዎች መሰረታዊ አላማችንና ስትራተጅያችንን በማያዛባ መልኩ በውይይትና በመግባባት የመፍታት አቅጣጫን ተከትለን መስራት አለብን።

ከአውሮ- መንግስታት የልማት ብድርና ርዳታ እንዲሁም የቴክኒክ ድጋፍ ለማግኘትና የተገኘውንም በላቀ ደረጃ ጥቅም ላይ ለማዋል መስራት አለብን። ይሁንናም በሂደት ዋነኛው ትኩረታችን በንግድና በኢንቨስትመንት ላይ ያተኮረ መሆን አለበት። በዝርዝርና በቀጣይ ጥናት ላይ ተመስርተን ለምርቶቻችን በአውሮፖ ገበያ ለማፈላለግና በአውሮፖ ተፈላጊ የሆኑ ምርቶችን ለማምረት በእቅድ ላይ የተመሰረተ ርብርብ ማድረግ አለብን። ይህንን በማድረግ ረገድ ሊረዱን የሚችሉ የግል ባለሃብቶች፣ የተለያዩ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋሞችና መንግስታት እያፈላለግን ከነዚህ ጋር ጠንካራ

መደጋገፍ ለመፍጠር መረባረብ አለብን፡፡ በአገራችን ተፈላጊ የሆነ ኢንቨስትመንት ለማግኘት እንደዚሁ በበቂና ቀጣይ ጥናት ላይ ተመስርተን በዚህ ረገድ ሊተባበሩን የሚችሉ ሃይሎችን አስተባብረን መስራት አለብን፡፡ የአገራችንን ገፅታ በዋነኛነት በአገራችን ያለውን ሁኔታ በመቀየር ከዚሁ ጋር ተያይዞም ገፅታውን ለመቀየር ሊተባበሩን የሚችሉ ሃይሎችን በማስተባበር በሰፊው መንቀሳቀስ ይኖርብናል፡፡

በአካባቢያችን ሰላም፣ መረጋጋትና ዴሞክራሲ እንዲሰፍን በማድረግ አውሮ- ትልቅ ድጋፍ ሊያበረክት ይችላል፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ያለንን አላማና ተግባር እንዲረዱ፣ በየወቅቱ በሚነሱ ገዳዮች ላይ መመካከርና ዘላቂነት ያለው የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ትብብርና ድጋፍ እንዲኖር መጣር ይኖርብናል፡፡

ከአውሮ- ጋር ባለን ግንኙነት የመንግስት ለመንግስት ግንኙነት ቁልፍ ቢሆንም በዚህ ላይ በታጠረ ግንኙነት የምንፈልገውን ጥቅም ማግኘት በፍፁም የሚቻል አይደለም፡፡ ዋናው ጥቅም በንግድና ኢንቨስትመንት የሚገኝ በመሆኑና በዚህ ረገድ ወሳኝ ሚና የሚጫወቱት የግል ባለሃብቶች በመሆናቸው ጥረታችን መንግስትን፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትንና የግል ባለሃብቶችን ያጣመረ መሆን አለበት፡፡ በአገራችን በኩል በአውሮ-የሚካሄደው ዲፕሎማሲም እነዚህን ሶስት ክፍሎች በሰፊው የሚያሳትፍና የሚያስተባብር መሆን አለበት፡፡ ይህ ሰፊ ርብርብ ሁሉጊዜም በዝርዝርና በቀጣይ ጥናት ላይ የተመሰረተ መሆን ይኖርበታል፡፡ የአውሮ-ን ማህበረሰብ እንደአንድ ማህበረሰብ



መውሰድ ትክክልና ተገቢ ቢሆንም በማህበረሰቡ ውስጥ የተለያዩ አገሮች የሚጫወቱት ሚና ይለያያል፡፡ ከዚህ በመነሳት ከሁሉም አገሮች ጋር መልካም ትስስርን ለመፍጠር መረባረብ የሚገባን ቢሆንም ዋናው ትኩረታችን በዋና ዋናዎቹ የማህበረሰቡ አባል አገሮችና ለኢትዮጵያ የተሻለ ቅርበትና በጎ አመለካከት ባላቸው አገሮች ላይ ያተኮረ መሆን ይኖርበታል፡፡

ከአውሮ- ጋር ሊነሱ የሚችሉት መለስተኛ ቅራኔዎች ለአገራችን ልማትና ለዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ የምናስቀምጣቸው ፖሊሲዎች በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ከአውሮ- ህብረት አመለካከት ሊለዩ በመቻላቸው፣ አልፎ አልፎም የምናስቀምጣቸው የልማት ፖሊሲዎች አንዳንድ የአውሮ- የግል ባለሃብቶችን የማያስደስቱ ሊሆኑ ስለሚችሉ የሚፈጠሩ ናቸው፡፡ ፖሊሲዎቻችንን በጥንቃቄና በጥናት ላይ ተመስርተን መቅረፅ አለብን፡፡ የተሻሉ አማራጮች ሲገኙም ያለማመንታት ማስተካከል አለብን፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ትክክለኛ ናቸው ባልናቸውና ወሳኝ በምንላቸው ፖሊሲዎች ላይ ፀንተን አስፈላጊነታቸውን በማስረዳትና በማሳመን ለመፍታት መጣጣር አለብን፡፡

የግሎባላይዜሽን ጎጂ ገፅታዎችን በመቀነስ ረገድ የአውሮ-ማህበረሰብ አንዳንድ በጎ ርምጃዎችን በመውሰድ ላይ መሆኑ ተገልጿል፡፡ የአውሮ- ህዝብና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋሞችም በዚህ ረገድ ሳልበለፀጉ አገሮች የሚጠቅሙ የተለያዩ አመለካከቶች እንዳሏቸው ይታወቃል፡፡ ይህንን በመጠቀም አውሮ-ለኢትዮጵያና ለአፍሪካ የተመቸ አጠቃላይ ሁኔታ እንዲፈጠር

የበኩሉን አስተዋፅኦ እንዲበረክት መገፋፋትና መደራደር ያስፈልጋል፡፡ ይህ በተናጠል ጥረት ብቻ አመርቂ ውጤት ሊያስገኝ የማይችል በመሆኑ ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች ጋር በመሆንና በአፍሪካ ህብረት ማዕቀፍ መፈፀም ያለበት ይሆናል፡፡

## 4.2. የሩሲያ ፌዴሬሽን፣

ሩሲያ ወደ ነፃ ገበያ ኢኮኖሚና ወደ ዴሞክራሲ በምታደርገው ሽግግር የተለያዩ ችግሮች ቢገጥሟትም አሁንም ታላቅ አገር ነች፣ ለወደፊቱም በአለም መድረክ ታላቅ ሚና መጫወቷን እንደምትቀጥል መገመት ይቻላል፡፡ የሩሲያ ህዝብ ከኢትዮጵያ ጋር የቆየ ባህላዊ ትስስር ያለውና ለኢትዮጵያ በጣም በጎ የሆነ አመለካከት ያለው ህዝብ ነው፡፡ ሩሲያ በኢኮኖሚ ልማታችን ላይ የገበያ፣ የኢንቨስትመንትና የቴክኒካዊ ድጋፍ ምንጭ ሆና ልታገለግል የምትችል አገር ነች፡፡ ለሰላምና መረጋጋት እንዲሁም ዴሞክራሲ የቆመች በመሆኗ ለአገራችንና ለአካባቢያችን ሰላም ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማበርከት ትችላለች፡፡ የአገራችንን የመከላከል ብቃት በማጠናከር ረገድም ሆነ ፍትሃዊ በሆነ አኳኋን ግጭቶችን ለመግታት በምናደርገው ጥረት እስከዛሬም ከፍተኛ ድጋፍ አድርጋለች፡፡ ወደ ፊትም ድጋፍዋን ልትቀጥልና ልታጠናክር የምትችል አገር ነች፡፡

በመሆኑም ከሩሲያ ጋር ያለንን ጥሩ አገራዊ ትስስርና ወዳጅነት ለማጠናከር በርትተን መስራት ይኖርብናል፡፡ በዲፕሎማሲ፣ በፖለቲካና በደህንነት መስኮች የቆዩት መልካም



ትብብሮች እንዲቀጥሉና እንዲጠናከሩ ማድረግ በጣም አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በኢኮኖሚው መስክ እስካሁን ድረስ አጥጋቢ ስራ ያልተሰራ መሆኑን በመገንዘብ በተለይም በንግድና በኢንቨስትመንት መስኩ የላቀ ስራ ለመስራት መረባረብ አለብን፡፡ ለኢትዮጵያ ልዩና በጎ አመለካከት ያላቸው ግለሰቦችና ድርጅቶች የሁለቱን አገሮች ትስስር በማጠናከር ረገድ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ ማበረታታትና ማስተባበር አለብን፡፡

# 5. ከአሜሪካ (ዩናይትድ ስቴትስ) ጋር የሚኖረን ግንኙነት፣

ከአውሮ- ጋር ሊኖረን ይገባል ብለን ያስቀመጥናቸው ጉዳዮች ከሞላ ጎደል ሁሉም ከአሜሪካም ጋር በሚኖረን ግንኙነት ላይ ይሰራሉ፡፡ ስለሆነም እሱን ከመድገም ይልቅ ለየት ባሉ ጉዳዮች ላይ ማተኮሩ ይመረጣል፡፡ ከዚህ አኳያ ዋናው ለየት ያለው ጉዳይ አሜሪካ በአለም ያላት ሚና ነው፡፡ የግሎባላይዜሽን መሰረታዊ ኢኮኖሚያዊ ህግጋትን የምትወስን ዋነኛዋ አገር አሜሪካ ነች፡፡ ከአለም ሰላምና መረጋጋት አኳያም ወሳኝዋ አሜሪካ ነች፡፡ በአለም እጅግ የበለፀገና የሰፋ ገበያ ያላት አገር አሜሪካ ነች፣ ይልቁንም ወደአሜሪካ ገበያ ሰብረው ያልገቡ የኢንዱስትሪ ልማት ፈጣን ለውጥ ያመጡ አገሮች የሉም ማለት ይቻላል፡፡ በመሆኑም የአሜሪካንን ድጋፍና ይሁንታ ማግኘት ለልማታችንም ሆነ ለአገራዊ ደህንነታችን እጅግ የላቀ አስተዋፅኦ እንዳለው ሊሰመርበት ይገባል፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ ለግንኙነታችን መዳበር በጎ አስተዋፅኦ የሚኖራቸው በርካታ ጉዳዮች እንዳሉም ሊሰመርበት ይገባል፡፡ በአሜሪካን አገር በጣም ብዙ ኢትዮጵያውያንና በትውልድ

ኢትዮጵያውያን የሆኑ ሰዎች አሉ። ይህም በአግባቡ ጥቅም ላይ ከዋለ የሁለቱን አገሮች ትስስር ለማጠናከር ልዩ አስተዋፅኦ ሊኖረው የሚችል አቅም ነው። በደርግ ጊዜ የተቋረጠበት ሁኔታ የነበረ ቢሆንም በአሜሪካና በኢትዮጵያ መካከል የቆየ ወዳጅነት አለ፣ ከዚህ ጋር ተያይዞም ለኢትዮጵያ በጎ አመለካከት ያላቸው ብዙ አሜሪካውያን አሉ። እነዚህም የሁለቱን አገሮች ትስስር ለማጠናከር ከፍተኛ አስተዋፅኦ ሊያበረክቱ የሚችሉ ናቸው። ኢትዮጵያ ሁሉን ነገር ወደጎን በማለት በልማትና በዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ላይ ማተኮር መወሰንዋ፣ በአካባቢያችን ሰላምና መረጋጋት እንዲሰፍን ግንባር ቀደም ተዋናይ መሆንዋ አሜሪካ በአካባቢው ከምትከተለው ፖሊሲ ጋር የተጣጣመና ለግንኙነታችን መዳበር አንድ ምክንያት ሊሆን የሚችል ነው።

ከልማት አኳያ የልማት ፋይናንስን ከአሜሪካ ማግኘት፣ አሜሪካ በዚህ ረገድ በቀጥታ ልታደርግ ከምትችለው አስተዋፅኦ በተጨማሪ በተዘዋዋሪ መንገድ የምታበረክተውን አስተዋፅኦ አሟጦ መጠቀም አንድ ሊተኮርበት የሚገባ ጉዳይ ነው። ለአውሮ-ም እንደተቀመጠው በሂደት ዋናው ጉዳይ ንግድና ኢንቨስትመንት መሆን ይኖርበታል። በዚህም ረገድ ለአውሮ- ያስቀመጥነው ፖሊሲ ለአሜሪካም የሚያገለግል ይሆናል።

በዚህ ረገድ ልዩ ትኩረት የሚያሻው ጉዳይ ካለ በአሜሪካ ያሉ ኢትዮጵያውያን በትውልድ ኢትዮጵያ የሆኑ ሰዎች ጉዳይ ነው። ይህ ማህበረሰብ የተለያዩ አመለካከቶች ያሉት ቢሆንም በአጠቃላይ ከፍተኛ የህዝብና የአገር ፍቅር እንዳለውና ለአገሩና



ለህዝቡ መልካሙን ሁሉ እንደሚመኝ በርግጠኝነት መናገር ይቻላል። ይህ አቅም በአገራችንና በአሜሪካ መካከል ጠንካራ የኢኮኖሚ ትስስር እንዲኖረን ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማድረግ ይችላል።

በመጀመሪያ ደረጃ ከነዚህ ውስጥ የተወሰነ ካፒታልና ሻል ያለ ሙያ ያላቸው በርካታ ሰዎች እንዳሉ መገመት ይቻላል። እነዚህ ሰዎች ሙያቸውንና ካፒታላቸውን በማስማራት ራሳቸውን ጠቅመው አገራቸውን እንዲጠቅሙ ማድረግ ይቻላል። በተናጠል በኢትዮጵያ ከሚያደርጉት ኢንቨስትመንት በተጨማሪ ከሌሎች አሜሪካውያን ኢንቨስተሮች ጋር በመሻረክ ኢንቨስት ማድረግም ይችላሉ። ባሉበት ሆነው ለኢትዮጵያ ምርቶች ገበያዎችን በማፈላለግ፣ በአገር ወስጥ ከሚገኙ ኢንቨስተሮች ጋር በመቀናጀት ራሳቸውን ጠቅመው አገራቸውን መጥቀም ይችላሉ። የዚህ ክፍል ዋነኛ አስተዋፅኦም ከላይ የተጠቀሰው ይሆናል። መንግስት ይህንን ተገንዝቦ ይህ ክፍል ራሱን ጠቅሞ አገሩን ለመጥቀም የሚችልበት ተጨባጭ ፕሮግራም ነድፎ በሰፊው መንቀሳቀስ ይኖርበታል። በአሜሪካ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና በትውልድ ኢትዮጵያውያን በአሜሪካና በኢትዮጵያ መካከል የሚኖረውን የንግድ ኢንቨስትመንት ግንኙነት አንድ ጠንካራ ድልድይ የሆነው በማገልገል ራሳቸውን ጠቅመው አገሪቱን እንዲጠቅሙ ማድረግ የትኩረታችን ማዕከል ሊሆን ይገባል። በዚህ ረገድ መንግስት በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንንና በትውልድ ኢትዮጵያውያንን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በማበረታታት ያወጣውን ህግ በጥብቅ ተግባራዊ ማድረግ በጣም አስፈላጊ ይሆናል።

ዋናው ነገር ከላይ የተጠቀሰው ቢሆንም በአሜሪካ የሚኖሩ

ኢትዮጵያውያን፣ በትውልድ ኢትዮጵያውያንና ሌሎችም የአገራችን ወዳጆች ህዝቡ በሚያደርጋቸው የልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ በተለያየ መንገድ ሊሳተፉ ይችላሉ፣ ሊሳተፉም ይገባል፡፡ የገንዘብና የተለያዩ ቁሳቁሶች መዋጮ አድርገው በአገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች በሚካሄዱ የልማት እንቅስቃሴ ውስጥ በመረጡት አኳኋንና በመረጡት አካባቢ ሊሳተፉ ይችላሉ፡፡ በያሉበት ሆነውም ከተለያዩ ምንጮች ተመሳሳይ ድጋፍ ሊያሰባስቡ ይችላሉ፡፡

ፍላጎቱና ፈቃደኝነቱ ያላቸው በአሜሪካ የአገራችንን ገፅታ ለማሻሻል የኢንቨስትመንት ፍሰትና የንግድ ትስስርን ለማጠናከር፣ የአገራችንን ሁኔታ በትክክል በማንፀባረቅ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማበርከት ይችላሉ፡፡ የአሜሪካ ሚድያ፣ ምክር ቤቶችና መንግስት ለኢትዮጵያ በጎ አመለካከት እንዲኖራቸው የበኩላቸውን ጥረት ማበርከትም ይችላሉ፡፡ መንግስት ይህንን ተገንዝቦ ይህ ክፍል ከላይ በተጠቀሰው አኳኋን ለአገራችን ልማት አስተዋፅኦ እንዲያበረክት ማበረታታትና የተመቻቸ ሁኔታን መፍጠር አለበት፡፡ ይህንን አሰራር ከአሜሪካ ጋር አያይዘን አነሳነው እንጅ በሌሎች አገሮች ለሚገኙ ኢትዮጵያውያንና በትውልድ ኢትዮጵያውያን ለሆኑ ሰዎችም የሚያገለግል ነው፡፡

የአካባቢያችንን ሰላምና ደህንነት በተመለከተ ያስቀመጥነው አቅጣጫ ከአሜሪካ ፖሊሲ ጋር የሚጣጣም እንደሆነ ተቀምጧል፡፡ አሜሪካ በአሁኑ ወቅት በአለም የፖለቲካ ሂደት ላይ ወሳኝ ሚና የምትጫወት አገር እንደሆነች፣ በተለይም በመካከለኛው ምስራቅ ከፍተኛ ቦታ ያላት እንደሆነም ይታወቃል፡፡ በሰላምና መረጋጋት አጀንዳችን ላይ የአሜሪካንን የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ድጋፍ ማግኘት



ለአላማችን መሳካት የላቀ አስተዋፅኦ አለው፡፡ ስለሆነም በዚህ ጉዳይ ላይ ከአሜሪካ ጋር እየተመካከሩ መስራት ጠቃሚና አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በዚህ ረገድ አልፎ አልፎ የአመለካከት ልዩነቶች እንደሚከሰቱና ሊከሰቱም እንደሚችሉ ይታወቃል፡፡ እነዚህን ልዩነቶች በግንኙነቱ ስትራተጅካዊ ጠቀሜታ ማዕቀፍ ውስጥ አስገብተን ማየትና ለማጣጣም መሞከር ይኖርብናል፡፡ በአካባቢያችን ግጭቶችን ለመግታት መቻልና በዚህ ረገድ አሜሪካ ልትጫወተው የምትችለው ሚናና አልፎ አልፎ ሊሰከቱ የሚችሉ ልዩነቶችን በማገናዘብ ማየትና መፍታት ወሳኝ ነገሮችን ከመለስተኛ ነገሮች ለይቶ የማየት አሰራር በጥብቅ ተግባራዊ ማድረግ ይኖርብናል፡፡

# 6. ኤስያ፣

## 6.1. አጠቃላይ፣

የሚበዛው የአለም ህዝብ የሚኖረው በኤስያ ነው፡፡ ከአለም በስፋቱና በብልፅግናው በሁለተኛነት የሚጠቀሰው የጃ-ን ኢኮኖሚ የሚገኘው በኤስያ ነው፡፡ ከሁለተኛው የአለም ጦርነት ወዲህ እጅግ የተዋጣለት የልማት ተግባር የተፈፀመው በኤስያ በተለይም በምስራቅ ኤስያ ነው፡፡ ከአንድ ቢልዮን ህዝብ በላይ ያላቸው ሁለት አገሮች የሚገኙት በኤስያ ነው፡፡ ከነዚህ አንዷ የሆነችው ቻይና በታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ፍጥነት እያደገች ትገኛለች፡፡ ሁለተኛዋ ህንድ ለብዙ አስርት አመታት ቀርፋፋ የልማት ሂደት የነበራት ሲሆን ባላፉት አስር አመታት በከፍተኛ ፍጥነት እያደገች ነው፡፡ በያዙት ፍጥነት ከቀጠሉ ሁለቱም አገሮች እጅግ ሰፊ

ኢኮኖሚ እንደሚኖራቸው ይገመታል፡፡ ቻይና በያዘችው ፍጥነት ከቀጠለች ከሰላሳ አመታት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ከአሜሪካና አውሮ- ኢኮኖሚ ድምር የማያንስ ስፋት ያለው ኢኮኖሚ እንደሚኖራት ይገመታል፡፡ በአጭሩ የአለምን የኢኮኖሚ ሚዛን የሚቀይር እድገት እየተከናወነ ያለው በኤስያ ነው፡፡

ኤስያ ከልማታችን አንፃር በጣም ከፍተኛ ሚና ሊጫወት ይችላል፡፡ የተሳካ የልማት ልምድ ማግኘት የምንችለው በዋነኛነት ከኤስያ ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በርካሽ ዋጋ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው የሰለጠነ የሰው ሃይልና ቴክኒካዊ ደጋፍ ማግኘት የምንችለው ከዚሁ ነው፡፡ እጅግ አስገራሚ በሆነ ፍጥነት እያደገ ያለ ገበያ ስለሆነም እኛም ከዚሁ ገበያ ተጠቃሚ መሆን እንችላለን፡፡ ከልማት ደረጃችን ጋር የሚሄድ ትልቅ ግምት የሚሰጠው ኢንቨስትመንትም ከዚህ አካባቢ ማግኘት እንችላለን፡፡ የልማት ፋይናንስን በተመለከተ እስካሁን በዋነኛነት ከጃ-ን በተወሰነ ደረጃ ደግሞ ከቻይና እናገኛለን፣ ይህ ለወደፊቱም ሊቀጥል ምናልባትም ሊጠናከር ይችላል፡፡ በዚህ አካባቢ ያሉ አገሮች ብዙዎቹ ታዳጊ በመሆናቸው ግሎባላይዘሽን በታዳጊ አገሮች ላይ የሚያስከትለውን አሉታዊ ተፅእኖ በመቀነስ ረገድ አጋሮቻችን ሲሆኑ በድምሩም ለልማታችን የላቀና እየጨመረ የሚሄድ አስተዋፅኦ ሊያበረክቱ የሚችሉ ናቸው፡፡

አገራዊ ደህንነታችንን በተመለከተ በዚህ አካባቢ ያሉ አገሮች የአለም አቀፍ ህጎች በጥብቅ እንዲከበሩ፣ አክራሪነትና ሽብረተኝነት እንዲወገድ የሚጥሩ ናቸው፡፡ በመሆኑም ለአገራዊ



ደህንነታችን የተመቻቸ አለማዊ ሁኔታ በመፍጠር ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ሊያበረክቱ ይችላሉ፡፡ አንዳንዶቹ ከዚህም አልፈው ሰላማችንን በማጠናከር ረገድ ከፍተኛ እገዛ ሊያበረክቱ የሚችሉ ናቸው፡፡

በድምር ሲታይ ኤስያ ከልማታችን አኳያ የላቀ አስተዋፅኦ ሊኖረው ስለሚችል፣ ከአገራዊ ደህንነትም አኳያ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው በመሆኑ ከኤስያ አገሮች ጋር ያለን ግንኙነት ልዩ ትኩረት ሰጥተን ማጠናከር አለብን፡፡ በዚህ ረገድ በጎ ሚና ሊጫወቱ ከሚችሉት ሁሉ አገሮች ጋር ግንኙነታችንን ማጠናከር የሚገባ ሲሆን በዋና ዋናዎቹ ላይ ማተኮር በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

## 6.2. ጃ-ን፣

ከጃ-ን ጋር ከሁለተኛው የአለም ጦርነት በፊት ጀምሮ ጤናማ ግንኙነት እንዳለን ይታወቃል፡፡ ለኢትዮጵያ በጎ አመለካከት ያላቸው ጃ-ናውያን በርካታ ሲሆኑ በአሁኑም ወቅት ጃ-ን ትልቅ ግምት የሚሰጠው የልማት ርዳታ ታበረክታለች፡፡ ይህ ጠንካራ የልማት ትብብር ሊቀጥልና ሊጠናከር እንደሚችልም ይገመታል፡፡ የተለያዩ የቴክኒክ ድጋፎችም እናገኛለን፡፡ በንግድና በኢንቨስትመንት ረገድ ግን አጥጋቢ ስራ ተሰርቷል ሊባል አይችልም፡፡ የጃ-ንና ገበያ ትርጉም ባለው ደረጃ ሰብረን የገባንበት ሁኔታ የለም፡፡ ከጃ-ን የምናገኘው ሰፋ ያለ ኢንቨስትመንትም የለም፡፡ ይህ በአንድ በኩል በውስጣችን ለንግድና ኢንቨስትመንት መጠናከር የተመቻቸ ሁኔታ ባለመፈጠሩ የመጣ ሲሆን፣ በሌላ

በኩል ግን ጃ-ን በዋነኛነት በኤስያ በተለይም በምስራቅ ኤስያ ስለምታተኩርና ገበያውም ላልበለፀጉ አገሮች ምርት በሚፈለገው መጠን ክፍት ባለመሆኑ የመጣ ነው::

ከጃ-ን ጋር ያለንን መልካም ግንኙነት ለወደፊቱም አጠናክረን መቀጠል ይኖርብናል:: የምናገኘውን የልማት ፋይናንስና የቴክኒክ ድጋፍ ለመጨመር አጠቃቀሙንም ለማሻሻል በርትተን መስራት፣ ለአውሮ- ባስቀመጥነው መልክም ንግድና ኢንቨስትመንትን ለማስፋት መንቀሳቀስ ይኖርብናል::

## 6.3. ቻይና፣

ቻይና በአሁኑ ወቅት ከአገራችን ጋር በጣም ጤናማ ግንኙነት አላት:: በአገራችን ለሚካሄደው የልማት ስራ ጠንካራ ድጋፍ አላት:: ባላት ውሱን አቅም የልማት ፋይናንስ ድጋፍም የምትሰጥ ስትሆን የልማት ልምድ በማካፈልና በቴክኒክ ድጋፍ ረገድ ያልተቆጠበ ትብብር ታደርግልናለች:: በዲፕሎማሲያዊና ፖለቲካዊ መስኩም አገራችን ሰላምዋን ለማስከበር መብትና ጥቅሟን ለማረጋገጥ በምታደርገው እንቅስቃሴ ሁሉ ጥሩ ወዳጅ ሆና ትሰለፋለች:: ኢንቨስትመንትን ወደ ውጭ በመላክ ረገድ ቻይና ገና ጀማሪ ስለሆነች በዚህ ረገድ የተገኘ ከፍተኛ ውጤት አለ ማለት አይቻልም:: ንግድን በተመለከተም ትርጉም ባለው ደረጃ ወደ ቻይና ገበያ ገብተናል ለማለት አይቻልም:: በቻይና ገበያ ውስጥ በአግባቡ ያልገባንበት ምክንያት ለጃ-ን ካስቀመጥነው ምክንያት ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው::



ከቻይና ጋር ያለንን ግንኙነት የላቀ ትኩረት ሰጥተን ልናጠናክረው ይገባል:: የልማት ልምድን በመቅሰም፣ በሰው ሃይል ስልጠናና በቴክኒካዊ ድጋፍ ረገድ ልናገኝ የምንችለውን ትብብር አሟጠን ለመጠቀም መረባረብ አለብን:: የልማት ፋይናንስ በተመለከተም ከተቻለ እንዲጨምር፣ ካልሆነም አጠቃቀሙ እንዲሻሻል ማድረግ አለብን:: ቻይና በአሁኑ ወቅት በውጭ አገር ኢንቨስት ማድረግ እየጀማመረች ስለሆነ፣ ይህንን የኢንቨስትመንት ዕድል ገና ከመጀመሪያው በይበልጥ ለመጠቀም ከቻይና መንግስት ጋር በመሆን በቅንጅት መስራት አለብን:: ምርቶቻችንን በቻይና ገበያ ለመሸጥም ከቻይና መንግስትና ኩባንያዎች ጋር በመሆን ከፍተኛ ጥረት ማድረግ አለብን::

## 6.4. ህንድ፣

ከህንድ ጋር ለረጅም ጊዜ የቆየ ታሪካዊ ግንኙነት ያለንን ሲሆን በተለይም ህንድ ነፃነትዋን ከተቀዳጀች ወዲህ መልካም ወዳጅነት ለመመስረት ችለናል:: ይህ ግንኙነት ባለፉት አስር አመታት በይበልጥ እየተጠናከረ በመሄድ ላይ ይገኛል:: በተለይም በሰው ሃይል ስልጠና ረገድ ህንድ እጅግ በጣም ከፍተኛ አስተዋፅኦ ልታበረክት የምትችል ሲሆን ይህንን ዕድል በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ልንጠቀምበት ችለናል:: እጅግ የሰለጠኑት እንደአሜሪካ ያሉ አገሮች የህንድ ሙያተኞችን በገፍ ከሚወስዱበት ሁኔታ ጋር ሲተያይ ግን መጠቀም በሚገባን ደረጃ ተጠቅመንበታል ማለት አንችልም:: ከህንድ ብዙ ጠቃሚ የልማት ልምዶችን ማግኘት

ሲቻል በዚህ ረገድም መጠቀም በሚገባን ደረጃ ተጠቅመንበታል ማለት አይቻልም፡፡ በንግድና ኢንቨስትመንት መልካም ሰፊ ዕድል እንዳለ ግልፅ ነው፡፡ ህንድ ግሎበላይዜሽን በታዳጊ አገሮች ላይ የሚያስከትለውን አሉታዊ ተፅእኖ በመቀነስ ረገድ ግንባር ቀደም ተሟጋች ነች፡፡ አክራሪነትን ሽብረተኝነትን በመፋለምም የተመሰከረላት አገር ነች፡፡ በመሆኑም ለአገራዊ ደህንነታችን የተመቻቸ አለማዊ ሁኔታ በመፍጠር ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ልታበረክት ትችላለች፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ሁኔታዎች ታሳቢ በማድረግ ከህንድ ጋር ያለንን ግንኙነት በከፍተኛ ደረጃ ለማጠናከር መረባረብ አለብን፡፡ በሰው ሃይል ስልጠና፣ የልማት ልምዶችን በመቅሰም ረገድ ያሉትን ዕድሎች አሟጠን ለመጠቀም ከመቼውም ጊዜ የላቀ ስራ መስራት አለብን፡፡ የህንድ ኢንቨስትመንት በመሳብም ትኩረት ሰጥተን መንቀሳቀስ ይገባናል፡፡ ህንድ ለምርቶቻችን ትልቅ ገበያ ልትሆን ስለምትችል ይህንን ገበያ ሰብረን ለመግባት ጠንካራና የተደራጀ ስራ መስራት አለብን፡፡ በዲፕሎማሲያዊና ፖለቲካዊ መስኮች ያለውንም ትብብር ማጠናከር ያስፈልገናል፡፡

# 7. አለም አቀፍ ድርጅቶችና መንግስታዊ ያልሆኑ



# ድርጅቶች፣

## 7.1. አለም አቀፍ ድርጅቶች፣

ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግስታትን ጨምሮ የብዙ አለም አቀፍ ድርጅቶች አባል ነች፡፡ የብዙዎቹ ድርጅቶች (የተባበሩት መንግስታትን ጨምሮ) መስራች አባል ነች፡፡ እነዚህ ድርጅቶች የአለም አቀፋዊ ትስስሩን ህጎጋት በመቅረፅና በማስከበር ረገድ በመድረክነት የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ በዚህ ማዕቀፍ ሰላምን፣ የአለም አቀፍ ህግ የበላይነትን በማስከበርና በአገሮች መካከል ትብብርን በማጎልበት ተኪ የሌለው ሚና ይጫወታሉ፡፡

አገራችን የግሎባላይዜሽንን ህጎጋት አክብራ፣ እነዚህ ህጎጋት የአገራችንና የመሰል አገሮችን ጥቅም በተሻለ አኳኋን የሚያስከብር እንዲሆን ለማድረግ የምታደርገው ጥረት የሚፈፀምበት አንዱ መድረክ ይህ የአለም አቀፍ ድርጅቶች መድረክ ነው፡፡ እንደ የተባበሩት መንግስታት ድርጅትና የተለያዩ ተቋሞቹ እንዲሁም የአለም ባንክን የመሳሰሉት ድርጅቶች ለአገራችን ልማት ከፍተኛ እገዛ የሚያበረክቱ ናቸው፡፡ በመሆኑም አገራችን ልማትን ለማፋጠን፣ አገራዊ ደህንነትዋን ለማረጋገጥ ከነዚህ ተቋሞች ጋር ያላት ትብብር ማጠናከር፣ ሰላምና አለም አቀፍ ህግ እንዲከበር አበክራ መንቀሳቀስ ይገባታል፡፡ የተባበሩት መንግስታት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ዋና ፅህፈት ቤቱ አዲስ አበባ መሆኑና በርካታ ሌሎች የተባበሩት መንግስታት ድርጅቶች በአገራችን ውስጥ መገኘታቸው ለትብብሩ ምቹ ሁኔታ የሚጥር

መሆኑን ታሳቢ ያደረገ የትብብር ፖሊሲ ሊኖረን ይገባል፡፡

## 7.2. አለም አቀፍ መንግሥታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣

በአሁኑ ወቅት መንግስታዊ ያልሆኑ አለም አቀፍ ድርጅቶች በልማት ርዳታና በሰብአዊ ርዳታ ረገድ ከፍተኛ